ከለሊቱ አጋማሽ 24 ወይም ዜሮ ሰዓት ላይ ተለኩሰው ብሬመን የጦር ሜዳ መሰለች። ሰማዩ በልዩ ልዩ ቀለማት አሸብርቆ የነጋ መሰለ። የቤተክርስቲያን ደወሎች በየቦታው ተደውለው ድምጻቸውን አስተጋቡ። ሕዝቡ ያመጣውን መጠጥ እየከፈተ ተጐነጫጨ። ለአዲሱ በዓል መልካም ምኞቱን እርስ በእርሱ እየገለጠ ተቃቅፎ ተሳሳመ። ለበዓሉ የተዘጋጀ ሙዚቃ ተከፍቶ ሕዝቡን አስጨፈረው። የባሩዱ ጩኸት የርችቱ ብርሃን ከተማዋን አደበላልቆ ለሊቱ የነጋ መሰለ።

ለምሽቱ ዝግጅት ብሬመን ውስጥ በየቦታው ትልልቅ የሙዚቃ አዳራሽ ተዘጋጅተዋል። ሕዝቡ ከቦታ ቦታ በታክሲ እየተዘዋወረ ከመዝናናት አልፎ ፈነጠዘ። የሰከረውም ወድቆ ተንከባለለ።

በዚህ ወቅት የታክሲዎች ሥራ እጅግ አጣዳፊ ሆነ። ያን አድርሶ ይሄን ወስዶ ከቦታ ቦታ መቅለብለብ ሩጫ ጥድፊያ አንዱ ባንዱ ተደራርቦ ታክሲውን የሙጥኝ ይላል። ከስንቱ ተሟግቶ አንዱን ጭኖ ሌላውን ትቶ ማስተናገዱ ይከብዳል። ዘሎ መኪና ውስጥ ከሚገባም ሰካራም አምልጦ በሕዝብ ትርምስ መሐል ተሽሎክልኮ መንዳት የነቃ አዕምሮና ትእግሥት ይጠይቃል። ለሹፌሩ ዘሎ የሚገባ ተሳፋሪ ቢጠቅመውም ለድርጅቱ ሲል የግድ በፋንክ የሚሰጡትን በሮች ተቀብሎ በቅድሚያ ማገልገል ግዴታው ነውና በጥንቃቄና በፍጥነት በመዟዟር የታክሲ የቀድሞ ደንበኞችን ጥሪ ያሟላል።

የበዓሉ ምሽት በዚሁ ሁኔታ ቀጥሎ ሕዝቡ በየቦታው በታክሲና በአቶቢስ እየተዘዋወረ ደስታውን በመግለጥ እስከ ንጋቱ ድረስ አከበረ።

የታክሲ ሹፌሮችም በዚሁ ድብልቅልቅ በዓል ብዙ ገንዘብ ቢያካብቱም አልፎ አልፎ አደጋም የደረሰባቸው ነበሩ። ሮዚና ጆኒ ፋጡማና ሙራት ይድከማቸው እንጂ በሰላም ሥራቸውን ጨርሰዋል።

በአጠቃላይ በጀርመን ሀገር ውስጥ ለዚህ ታላቅ በዓል ለሚተኮሱ ርችትና ባሩዶች በየዓመቱ ከ16 ሚሊዮን ዶች ማርክ ወጪ ይደረጋል። ገንዘቡ ብቻ ሳይሆን እንዲህ ያለው መጥፎ ልማድ የአካባቢን ማቆሸሽ ብከላን ያስከትላል ተብሎ ቢታመንም ሕዝቡ ይህን ባህል የሙጥኝ ብሎ አጥብቆ ይዟል።

አውሮፓ ዘመን ተለውጦ መስከረም ጠባ። ሰማዩ ግን ካለፈው ዓመት የተለዩ መልክ አላሳየም። ያው የጨፈገገ ክረምት ነው። እንደ ኢትዮጵያ ፀሐይ ተፈንጥቃ አልወጣችም። አደይ አበባ በየቦታ በቅለውና አብበው አልታዩም።





# ክፍል አሥራ ስድስት

አካባቢው እንደሰፊ ባህር ተንጣሎ ሜዳው በኑግ የታሰሰ ምጣድ መስሎ ያብለጨልጫል። አየሩ ሞቃት ወቅቱ ብራማ ነበር። ብዙ አይሮፕላኖች እንደ ታክሲ ተደርድረው ይታያሉ። አንዱ አይሮፕላን ሞተሩን አግሎ ተንደርድሮ ወደላይ ሲከንፍ ሌላው ሞተሩን እያበረደ አፍንጫውን ወደታች ደፍቶ ጐማዎቹን ዘርግቶ ይመጣል።

ከማዶ ለሕዝብ መስተናገጃ በተሠራው ሠገነት ላይ ሆነው ብዙ ሰዎች እጃቸውን ያርገበግባሉ። የሚመጣውን እንግዳ ናፍቀው ለማየት ጓጉተው ይጨነቃሉ። እቅፍ አበባ ይዘው ዘመድና ወዳጃቸውን ይጠብቃሉ። አንዳንዶቹ የፍቅራቸው ብዛት የናፍቆታቸው ጋት ሞልቶ ይርበተበታሉ።

ተለይቶ የሚሄድ ወዳጅ ተሸኝቶ ሲከንፍ ተናፍቆ የሚጠበቅ ዘመድ መጥቶ ይደርሳል። ሁኔታው እንደ ልደትና ሞት ዓይነት የኅብረተሰቡ የፍቅር መግለጫ ባህላዊ ልማድ ሆኖ ቆይቷል።

ቦታው አሜሪካ ካሊፎርኒያ ኬኔዲ አየር ጣቢያ ነው። ሮዚ አሜሪካ ስትገባ የመጀመሪያ ጊዜዋ ነበር። ሰውነቷ በጉዞ አሰልችነት ስለደከመ ከአውሮፕላኑ ፈጥና ለመውረድ አልቻከለችም። ቀስ ብላ የመውረጃውን በረንዳ በእጆቿ ጨብጣ እየተራመደች እመሬቱ መሐል ላይ ደረሰች። ወቅቱ ሞቃት ቢሆንም በአካባቢው ቀዝቃዛ አየር ስለሚነፍስ የሰውነቷን ሙቀት አራገበላት። አዲስ ሀገር የተለየ አካባቢና ሁኔታ እስከሚለመድ ለጊዜው ያደናግራልና ትንሽ ግር ብሏት ሰውነቷ ፈራ።

ሮዚ የፓስፖርቱ ቁጥጥር አልቆ በናፍቆት ከሚጠብቋት ታላቅ እህቷ ከባለቤቷና ከሌላም ሰዎች ጋር ተደባልቃ የናፍቆትና የፍቅር ሰላምታ ተለዋወጠች። በቅርቡ የተወለደችውንም የእህቷን ልጅ ሕፃን ታቅፋ አገላብጣ ሳመቻት። ለእንግድነቷ ክብር የቀረበላትን ስጦታና አበባዎች ተቀብላ በተዘጋጀላት የሾፍሬሌት ሽንጣም የአሜሪካን መኪና ውስጥ ገብታ ሙሽራ መስላ ተጓዘች።

ጆኒ ሮዚን ሸኝቶ ለሊቱን ተኝቶ በማግስቱ ከእንቅልፉ የነቃው እረፋዱ ላይ ነበር። ደህና መድረሷን ለማረጋገጥ የስልክ ጥሪ ተጨንቆ ይጠብቃል። በእለቱ የታክሲ ሥራ የለበትም። የድርሰቱ ሥራ ቢያልቅም የመሐበሩ ጉዳይ ተተክቶ ለግሉ መዝናኛ ፋታ አላገኘም። በኃላፊነት የተመረጠበትን ሙያ የጠበቀ መሠረት ለማስያዝ ይጥራል።

የመሐበሩም መሪ ኢንጂኔር በላቸውም ቢሆን ሥራ ቢበዛበትም ኃላፊነቱን አልዘነጋም። ከጆኒ ጋር ተመካክረው ሁለተኛ አጠቃላይ ስብሰባ ለማድረግ አቅደዋል። በመጀመሪያ መሐበሩ በሕዝብ እንዲታወቅ የኢትዮጵያ ምሽት ማዘጋጀት ወስነው በጉዳዩ ለመነጋገር የተለየ ስብሰባ አደረጉ።

ሮዚ አሜሪካ ከገባች አንድ ሳምንት አለፈ። በዚህ አጭር ጊዜ የታወቁ የአሜሪካን ታላላቅ ከተሞችን ተዘዋውራ ጐብኝታለች። የሕንፃዎችን አሠራር የድልድዮችን ግንባታ የመንገዶችን ስፋት በአጠቃላይ የቴክኒዎሎጅውን የሥልጣኔ ውጤትና እድገት ተመልክታ አድንቃ አበክራለች። የሕዝቡንም ኑሮ የሥራ ውጥረትና ትጋት ድክመትና ሕልውና ገምታ ሰው ሰው አልሸት ብሏት በሁኔታው ተገርማ ታዝባለች።

ሮዚ በአሜሪካና በአውሮፓ ሀብታም ሀገሮች መሐከል እጅግ የተራራቀ ልዩነት መኖሩን ተገነዘበች። እንደ ጀርመን ለዜግነት የሚደረግ የሶሻል ቸርነት አሜሪካን አለመኖሩ ገረማት። የካፒታሊስት ፍልስፍና አውሮፓ የተወለደውን ያህል በአሜሪካ የግለሰብ ብልጽግና ለማምጣት እያንዳንዱ ሰው በደግነት የሚያስንፍ የበጐ አድራጐት ስጦታ የለበትም።

ይህም የሰውን ልጅ ተፈጥሮአዊ ሁኔታ የሚመለከት ነው። የታመመ ተፍጨርጭሮ መዳን ከቻለ ይድናል ካልቻለ ግን ጉንፉንም ቢሆን ይገለዋል። ጠንካራ ጓደኞች ካሉት ተሯሩጠው ያድኑታል። ብቸኛ ከሆነ ግን እዛው ተከንችሮ ይሞታል። ይህ እንግዲህ ተፈጥሮአዊ ሲሆን አሜሪካም የብርቱዎች ሀገር ናት ማለት ነው። ሰዎች ሁሉ አእምሮና አካላቸው እስከፈቀደ ድረስ ተፍጨርጭረው ያድጋሉ። ሁሉም ተፍጨርጫሪ ቢሆንም አንዱ ከሌላው ይበልጣል። ደካማው ተፍጨርጫሪ የብርቱው ታዛዥ ይሆናል ማለት ነው።



በእርግጥ አሜሪካን ውስጥ ብዙ የተማሩና ያልተማሩም ኢትዮጵያውያን አሉ። ገንዘብ ይዞ መክበር እንጂ የሥራ ቦታ ምርጫ ጨርሶ የለም። መኪና ማቆሚያ ቦታ ማገልገል፣ ፒሳ ማመላለስ፣ ታክሲ መንዳት ግርድናና ዘበኝነት ተቀጥሮ ሌት ተቀን በሥራ መወጠር የተለመደ ባህል ነው።

በተለይ ዋሽንግተንና ካሊፎርኒያ የሚገኙት አበሾች ብዙ በመሆናቸው የገበያ አዳራሹ የምግብ ቤቱ ብዛት መርካቶን ያስንቃል። በስደት ከመጣው ይልቅ በዲቪ ሎተሪ የመጣው ይበዛል። እነዚህም ከመማር ይልቅ በየሆቴሉ ተቀጥረው ሌት ተቀን ያገለግላሉ። የሰው ልጅ ፋታ ጨርሶ የለም።

እንግዳ ሽማግሌ እንኳን ከሀገር ቤት ለጉብኝት ወይም ለሕክምና ሲመጡ እንደ አውሮፓ ኑሮ የሞቀ መስተንግዶ አይደረግላቸውም። በስልክ ጥሪ ሰላምታ ተሰጣጥቶ ለሥራ መክነፍ ነው። እንኳን የእንግዳ ጋባዥ ጓደኞች ዋናው የእንግዳው ሁነኛ ዘመድ የመጡትን እንግዳ ባዶ ቤት አስቀምጦ ቴሌቪዥን ከፍቶ ሙሉ ቀን ወና ቤት ያውላቸዋል። ሮዚ ይህንንና ይህን የመሰለውን ሁኔታ ተመልክታ የአሜሪካን አየር ቢስማማትም አውሮፓ ጀርመን በመኖሯ እድሏን አመሰገነች።

ጀርመን ሀገር የምትገኘዋ የብሬመን ትንሽ ከተማ እንደ አሜሪካ ካሊፎርኒያ አልሞቀችም። ክረምቱ ገና ለቆ ስላልወጣ አየሩ ይቀዘቅዛል። ዝናብና በረዶ ግን እንደወትሮ አይጥልም።

እለቱ የኢትዮጵያ የስደተኞች መረዳጃ መሐበር የሚመረቅበት ሆኖ ብዙ ሰዎች ተቃብዘው አዳራሹን ሞልተውታል። ለበዓሉ የተዘጋጁ ልዩ ልዩ የሀገር ቤት ምግቦችና ለብፌ ምርጫ በሰፊው ጠረጴዛ ላይ ሆነው ያስጐመጃሉ።

ጆኒ ነጭ የሀገር ልብስ ለብሶ አዳራሹ ለሚገኘው ሕዝብ በአማርኛና በጀርመንኛ ንግግር አደረገ።

ክብራትና ክቡራን፣

«የዛሬው በዓል በርግጥ የኢትዮጵያን ችግር ወይም የጊዜውን የፖለቲካ ሂደት ለመነጋገር አይደለም። ስብሰባው የሀገሪቱ አስተዳደር አንገፍግፏቸው ከውድ ሀገራቸው ተለይተው እዚህ በስደት የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያን ለማስተባበር የተቋቋመውን መሐበር ለማስመረቅ ነው።

ይህ መሐበር ዋና ዓላማው፣

1ኛ. የጋራ ችግራችንን ለመወጣትና በአሁኑ ጊዜ በጀርመን ጥቂት ዘረኞች በእኛ ላይ ያላቸውን ጥላቻና ጥቃት ለመቋቋም የእርስ በእርስ ኅብረታችንን ለማጠናከር።

2ኛ. የሀገራችን መሠረታዊ ታሪክ ባህልና ሥነ ምግባር እንዳይዘነጋ ማድረግና በተለይ እዚህ ለተወለዱት ለሚወለዱት ሕፃናት የሀገራቸውን ቋንቋ ባህልና ታሪክ እንዲማሩ ማድረግ።

3ኛ. የሀገራችንን የጊዜያዊ የፖለቲካ ሁኔታ በማጥናት ችግሩ የሚፈታበትን ነገሮች ቀይሶ ቢቻል አንድ ዲሞክራሲያዊ የሆነ የፖለቲካ ድርጅት ለማቋቋም መሠረት መጣል ነው።

ክብራትና ክቡራን፣

ምንም እንኳን ይህን መሐበር እኛ ጥቂት ኢትዮጵያውያን ብናቋቁመውም የሕጋዊ አካል አግኝቶ የመንግሥትና የሌላ ድርጅቶች ድጋፍ እንዲያገኝ የደከመልንን ባለሥልጣኖችና ግለሰቦችን በመሐበሩ አባላት ስም ሆኜ ከልብ አመሰግናለሁ» ብሎ ጨረሰ።

ሕዝቡ ደስታውን በጭብጨባ ገለጸለት። ምግብ ቀርቦ ሙዚቃ ተከፍቶ በዓሉ በትልቅ ሥነ ሥርዓት ተከብሮ ዋለ።

ሮዚ አሜሪካ ከወር በላይ ተቀመጠች። የድሮ የትምህርት ቤት ጓደኞቿንም አግኝታ ደስ ብሏት ሰነበተች። እንዳውም አንደኛዋ በቅርቡ ስለምታገባ ሙዜ እንድትሆናት ተለምና ተቀብላለች። ከዚህም ሌላ የመጀመሪያ የት/ቤት ፍቅረኛዋ የሷን ካሊፎርኒያ መምጣት ሰምቶ እህቷ ቤት ደውሎ በስልክ አነጋግሯታል። በኋላም አላስችል ብሎት ከዋሽንግተን ከተማ በአየር በሮ ካሊፎርኒያ መጥቶ እሮዚን አገኛት።

ወጣቱ ናፍቆቱን ጠግቦ ሳይወጣ ጉራውን ደረደረላት። የአሜሪካን ዜግነት እንዳለው ንግድ ከፍቶ በራሱ ድርጅት የሚተዳደር ከበርቴ መሆኑን ነገራት። ሌላ እጮኛ ቢኖረውም ዋሽቶ ለጋብቻ ደፍሮ ጠየቃት።

ሮዚ ጥንት የምታውቀው ያፈቀረችው የነበረ የልጅነት ወዳጅዋ ጨርሶ አልመሰል አላት። ፍላጐትና ያላትን አላማ ሳይጠይቅ ጉራውን ደርድሮ በሀብቱ ደልሎ ለጋብቻ ደፍሮ መጠየቁ አስቀየማት። የወንድነት



ትምክተኝነቱን አስተውላ ናቀችው። በዚህም ምክንያት የሁለቱ ግንኙነት አልሰመረም። ከንፈር ለከንፈር እንኳን ገጥመው የጥንቱን አስታውሰው አልተሳሳሙም። የሆነ የኢትዮጵያ ምግብ ቤት ተገባብዘው የወጣቱ አቀራረብ ሳያምር ቀርቶ በዚሁ ተለያይተዋል።

ሮዚ አሜሪካን ውስጥ በታክሲ ሥራ አገልግሎት የሚተዳደሩትን ኢትዮጵያውያን ተገናኝታ ተወያይታለች። አሜሪካን ውስጥ እንደሷ ደፍረው በለሊት የሚነዱ የሴት ሹፌሮች በማጣቷ አዘነች። «ጥቁሮች በበዙበት ሀገር የምን ፍርሃት ነው። እኔ ልጅቱ የቀለም ልዩነትና ዘረኝነት ባለበት የነጮች ከተማ ደፍሬ እሠራለሁ» ብላ ፎከረች።

የጦር መሣሪያ ለማንም እንደመስቲካ የሚሸጥበትን አሜሪካ ከጀርመን ጋር እያወዳደረች በጀርመን መሣሪያ መያዝ ጨርሶ ክልክል መሆኑን እያወቀች እንዳው አያምጣው ነው እንጂ ለእሷ አንድ ጥፊ መች አነሳት። ያም ሆኖ ሮዚ ያላት ድፍረት የምትጠብቀው የሴትነቷ ክብረት እጅግ የሚያስመሰግን ነው።

ጆኒ በጻፈው ድርሰትና በመሠረተው መሐበር ሰውነቱ ደክሞ አልተጐዳም። ውጤቱ ፍሬአማ የሆነ ማንኛውም በጐ ምግባርን ማከናወን ምን ጊዜም ልብን የሚያበረታ ሰውነትን የሚያበለጽግ የሕይወት ምንጭ በመሆኑ እንዳውም ያረጀ ፊቱ በተስፋ ታድሶ ወጣት መሰለ።

ውጣ ውረድ ያለበት የለሊት የታክሲ ሥራው ግን አስጠላው። በባእድ ሀገር የወንደላጤነት ኑሮው መረረው «ሌላውን ለመርዳት አስቀድሞ የራስን ችግር አስወግዶ በተሟላ ጤንነት ዝግጁ ሆኖ መገኘት ይገባል» ብሎ ኑሮው ይበልጥ የሚስተካከልበት ዘዴዎች መቀየስ ጀመረ።

በቅርቡ በዝና የሚያውቃት የሮዚ የአክስት ልጅ የእመቤት ተሾመ ደብዳቤ ደርሶት ለጻፈላት የመተዋወቂያ መልእክት መልሱን በቶሎ በማግኘቱ ደስ አለው። ለትዳር ያላትን ስሜት ገልጻ ለሁሉም መሠረቱ ግን ፍቅር መሆኑን በደንብ ዘርዝራ ጽፋለታለች። በአስተሳሰቧ ብስለት አድንቆ የላከችለትን ፎቶ ተመልክቶ ወዷታል። ግን የጠየቀችው የፍቅር ምሥረታ ጉዳይ ግራ ገብቶት አሳሰበው።

«ፍቅር ሰዎችን ያዛል እንጂ ሰዎች ፍቅርን እንዴት ማዘዝ ይችላሉ» ብሎ ተመራመረ። በዚሁም በሁለታቸው መሐከል እንዴት ፍቅር ሊመሠረት እንደሚችል እንቆቅልሽ ሆነበት። እዚህ ተቀራርበው ያልሆነላቸው እሩቅ ለሩቅ ማዶ ለማዶ ያሉ ሁለት ሰዎች ምን ዓይነት ፍቅር እንደሚፈጥሩ አስቦ ግራ ገባው።

«ፍቅር እንደድርሰት በፈጠራ ድክመት የሚገኝ ኪነት ሳይሆን ከተፈጥሮ በላይ ያለ እረቂቅ ኃይል ነው» ብሎ እመቤት ያቀረበችው ሀሳብ ቢገባውም ደብዳቤውን ደግሞ ደጋግሞ አነበበው።

ጀኒ ባልገባው ጉዳይ ተንደርድሮ ለእመቤት መልስ ሊጽፍላት ከጀለ። ብእሩን አንስቶ ጥቂት ከጻፈ በኋላ መልሶ ጣለው። «በነጭ ወረቀት ላይ የሰፈሩ ጥቂት ጥቋቁር ፊደላት መልእክትን እንጂ ፍቅርን አያመጡም» ብሎ የጻፈውን ደብዳቤ ቦጫጭቆ ጣለው። ትንሽ አሰብ አድርጎ መልሶ ተመራመረ። ምርምሩ የረቀቀ ሃይማኖታዊ ፈለግ እንጂ የተጨበጠ መፍትሄ አላስገኙለትም። «በመጀመሪያ ቃል ነበር ቃልም...» ብሎ ተወው። «አሁን ማዶ ላለችው እመቤት የቃላት ክምችት ደርድሬ ባቀርብላት ምን ይጠቅማታል?» ብሎ እራሱን መልሶ ጠየቀ። የሆነ ነገር ብልጭ ብሎ ታየው። ከሁሉ የሚበልጠውን ተጨባጭ ዘዴ ድንገት በማግኘቱ ደስ ብሎት ብቻውን እንደ እብድ ከት ብሎ ሳቀ። ውሳኔው ሀገሩ ገብቶ ከእመቤት ጋር ዓይን ለዓይን ተያይቶ በአካል ተገናኝቶ መተዋወቁ ነበር።

ጀኒ ከሀገሩ ከወጣ 15 ዓመታት ሆኖታል። በፖለቲካው ፍራቻ ተመልሶ ሀገሩ ሊገባ አልቻለም። የተወለደበት ሀገር ያደገበት መንደር ይናፍቀዋል። የኢትዮጵያን አየር ባህልና ሥነ ምግባር የበዓላት አከባበርና የኅብረተሰቡ ፍቅር እያደነቀ ዘወትር ያልማል። ግን ውድ ሀገሩን እስካሁን ጨክኖ ለመጎብኘት አልደፈረም። ያለፈውንም ሆነ የአሁኑን የፖለቲካ አስተዳደር ጨርሶ አይደግፍም። ያለበት ቦታ ሆኖ በግልም ሆነ በድርጅት ብዙ ጊዜ ተቃውሞውን በይፋ አልሞቷል። ግን እስከዚህ የሚፈለግ የፖለቲካ ቀንደኛ መሪ ባለመሆኑ ልቡ ተረጋግቶ የዓመት የሥራ እረፍት ወስዶ፣ ኢትዮጵያን ጎብኝቶ፣ ከእመቤት ጋር በደንብ ለመተዋወቅ ወሰነ።

ሮዚ በአሜሪካ ጉብኝቷ መሐል የጓደኛዋ ደንገጡር ሙዜ ሆና የሠርጉ በዓል በታወቀ ሆቴል ሆኖ በዓሉ በታላቅ ሥነ ሥርዓት ተከበረ።

ሮዚ የተፈጥሮ ቁንጅናዋ ከለበሰችው ዘመናዊ ሞድ ጋር በመስማማት ውበቷን ይበልጥ አጉላው። በዚህም በግብዣው ላይ የነበሩ ብዙ ሰዎች ከሙሽራዋ ቁንጅና ይልቅ የሷን ውበት አደነቁ። እሷም ዓይኖቿ ብዙ ሰዎችን ተመለከቱ። ልቧ የደነገጠው ግን በአንድ ጥቁር አሜሪካዊ ወጣት ላይ ነበር። ጨርሶ የማይተዋወቁ በዜግነት የማይገናኙ የሁለት ሰዎች የፍቅር ሰመመን በዚሁ በዓል ድንገት ተፈጥሮ ተዋወቁ። አድራሻ ተለዋውጠው በቅርቡ ለመገናኘት ወስነው ተለያዩ።



የሠርጉ በዓል ባለፈ በሳምንቱ በስልክ ጥሪ ተደዋውለው፣ በአጭር ጊዜ ተነፋፍቀው የሆነ አማካኝ ቦታ ሁለቱም ተገናኙ። ልባቸው ቢፈቃቀድም ስሜታቸው ቢዋሃድም ሲገናኙ ተቃቅፈው አልተሳሳሙም። ፊት ለፊት የሆነ መዝናኛ ቦታ ተቀምጠው እራሳቸውን በራሳቸው መልሶ ለማስተዋወቅ እንደበታቸው ተሳሰረ። ለጥቂት ጊዜ የቀረበላቸውን መጠጥ እየተጎነጩ በዝምታ ተፋጠጡ።

ጥቁሩ አሜሪካዊ አሮን ይባላል። ረዥምና ግዙፍ ቢሆንም እድሜው ገና ለጋ ነው። መልኩ ጠቆረ እንጂ የጀርመኑን ክላውዝ ይመስላል። ከታወቀ ዩኒቨርስቲ በሕግ ትምህርት ተመርቆ በጥብቅና ሥራ ለሆነ የግል ድርጅት ነገረ ፈጅ ሆኖ ይሠራል። ትዳር ያልመሠረተ ወንደላጤ ነው።

ሁለቱም በፍቅር ስሜት በፈገግታ ተያይተው ቢተፋፈሩም ቀስ በቀስ ጫወታ ጀምረው ተወያዩ። ሮዚ የአሮን ውበትና ግርማ ሞገስ ያለውን የአነጋገር ለዛ በዛ ላይ የሕግ አዋቂ በመሆኑ በሙሉ ልቧ ተማርካ ወደደችው። እሱም እንደሷ ሆኖ የሚያባብል ዓይኖቿ ማረኩት። ጫወታዋን ቅርጽና ውበቷን አድንቆ ፈዘዘ። ያ ግዙፍ ሰውነቱ በፍቅሯ ተዝለፈለፈ። ይልኝታ ጠፍቶ ሁለቱም ተቀራርበው በይፋ ተቃቅፈው ተሳሳሙ። የስሜታቸው ሙቀት የሰውነታቸው ግለት ካሉበት ቦታ ገፍትሮ አስነሳቸው። እጅ ለእጅ ተያይዘው አሮን አዲስ ካዲላክ መኪና ውስጥ ገብተው አሁንም ደግመው ተሳሳሙ። በመጨረሻ አሮን መኪናውን አስነስቶ ሮዚን እቤቱ ወስዶ አሳደራት።





# ክፍል አሥራ ሰባት

ክረምት አልፎ የአበባ እንቡጦች ፈነዱ። የደረቁ ዛፎች አቆጠቆጡ። ንቦች ምግባቸውን ቀስመው ጠገቡ። ወፎች በደስታ ዘመሩ። የአዝመራ ተክሎች አፈር ጥሰው ተንጠራርተው በቀሉ። ይህ የፀደይ ዓመታዊ ወቅት ሰዓቱን ጠብቆ መጣ። ሰማዩ ደስ የሚል ፈገግታ ማሳየት ጀመረ። አየሩ ሞቆ የአውሮፓ የጨፈገገ ምድር በአበቦች ቆነጀ።

ጆኒ የአበሻ ቁረስት ሆኖ ውድ እናት ሀገሩን ኢትዮጵያን ለመጐብኘት ወስኖ የዓመት የእረፍት ፍቃዱን ወሰደ። ወዶ ሳይሆን ለመኖር እንቅስቃሴ ያደረገው የዜግነት ለውጥ እያደር ቆጨው። ቦን ለሚገኘው ለኢትዮጵያ ኤንባሲ አመልክቶ የአንድ ወር ቪዛ ተሰጠው። በርግጥ ጆኒ የሀገሩን ጊዜያዊ የፖለቲካ ሁኔታ በመጠኑ ቢያውቅም ለጥንቃቄ ብሎ በቅርቡ ኢትዮጵያ ደርሰው የተመለሱትን ሰዎች በማነጋገር መረጃዎችን መሰብሰብ ፈልጐ የደመቀ ጐበናን የስልክ ቁጥር ተመለከተ።

ደመቀ ጐበና የተባለው ኢትዮጵያዊ ብሬመን ከተማ ለረዥም ጊዜ የኖረ የጆኒ የቅርብ ጓደኛ ነው። ደመቀ አለባበሱ ሽክ ያለ፣ ከረባት የማይለየው ዜንጠኛ በመሆኑ፣ ቅጽል ስሙ ደመቀ ዜንጦ ይባላል። ቀልደኛና ተጫዋች ሰው ነው። ከፍተኛ የሀገር ፍቅር ስሜት ስላለው ማንኛውም ሰው ማለት ደሃም ይሁን ሀብታም «ኢትዮጵያዊ» ከተባለ አቅፎ ይስማል። በስደትና በልዩ ልዩ ጉዳይ ከሀገራቸው የሚመጡትን ኢትዮጵያውያን በእንግድነት ተቀብሎ በደንብ ያስተናግዳል።

የጀርመንን ቢሮክራሲና ቋንቋ በደንብ ስለሚያውቀው በተለይ የኢትዮጵያ ስደተኞችን ሲመጡበት በግል መኪናው ከቢሮ ቢሮ እየወሰደ ጉዳያቸውን የሚያስፈጽም ደምዝ የማይከፈለው ነገረ ፈጅ ነው ቢባል አይከፋም።



ደመቀ ዜንጦ በቅርቡ አዲስ ትሬፍ (Addis Treff) የሚባል ቡና ቤት ከፍቶ እራሱን በራሱ የሚያስተዳድር ቀጭን ጌታ ነው። በልቡ ጥቁሮችን ባይጠላም የካፒታሊስት ስሜት አለበት። ይህ ጠባዩ ንግድ ከከፈተ በኋላ የመጣበት በሽታ ነው። ብዙ ነጮች ጥቁር የበዛበት ቦታ መግባት ስለማይወዱ ለንግዱ ጥንቃቄ ሲል ኢትዮጵያውያንና ሌሎች ጥቁሮች ገንዘብ ቢኖራቸውም ወደ ቡና ቤቱ በየዕለቱ እንዲመጡበት አይፈልግም። ችግሩን የተረዱት በፍቅር እርቀው፣ ያልተረዱት ደግሞ በሀሜትና በጥላቻ ሸሽተው ስለሚሄዱ ንግድ ቤቱ የጥቁሮች ብቻ ሳይሆን ብዙ ነጮች ጥቂት ጥቁሮች የሚገለገሉበትና የሚገናኙበት ቦታ ሆኗል። ግን በቅርቡ ምስጢሩ ባልታወቀ ምክንያት ንግድ ቤቱ ተዘግቷል። ደመቀ በዚሁ ንዴት ይሁን የሀገር ናፍቆቱን ለመወጣት ወደ ኢትዮጵያ ሄዶ ተመልሷል።

ጆኒ ይህን በማወቁ ደመቀን ለማነጋገር ፈልጐ መኖሪያ ቤቱ ስልክ ደውሎ አገኘው።

«ሃሎ ደመቀ ነህ?»

«ነኝ።»

«እንኳን ደህና መጣህ፣ ጆኒ ነኝ።»

«አ! ጆኒ እንኳን ደህና ቆየኸኝ።»

«መቼ መጣህ?»

«ሳምንት አለፈኝ።»

«እንዴት ነው አዲስ አበባ?»

«ደህና፣ ይገርምሀል ሴት በሽበሽ ነው፤ መርጠህ መውሰድ ነው ሃ! ሃ! ሃ! ሃ!»

«የጠየቅሁህ የሴቶችን ጉዳይ ሳይሆን የሕዝቡን ኑሮ የፖለቲካውን የአስተዳደር አወቃቀር ማለቴ ነው።»

«ሕዝቡ ያው ድሃ ነው። በየመንገዱ የራሱን ሥራ ፈጥሮ ሲለምን፣ ሲነግድ ሲደልል ሲቀማ ብርቱው ደካማውን ጥሎ ሲያጉላላ ይሄው ነው»

«ፖለቲካውስ?»

«የምንግርህ እኮ ፖለቲካ ነው፣ ጆኒ። የሕዝቡ ኑሮ እንዲህ ከሆነ የመንግሥቱ አስተዳዳር እንዴት እንደሆነ ለመገመት ቀላል ነው።»

«ይቅርታ ደመቀ እውነትክን ነው። ላጣራ ብዬ እንጂ እኔም አላጣሁትም።»

«ደህና፣ እንደ ፖሊስ ምርምር ስላበዛህብኝ ነው።»

«የቢሮ ክራሲውስ ሁኔታ?»

«እንደ ሁኔታው ሊፈጥንም ሊዘገይም ወይም ጨርሶ ሊዘጋም ይችላል።»

«ምን ማለትህ ነው?»

«ሃ! ሃ! ሃ! ሃ! ጐሳ ክልል ወገን ዘመድ ቋንቋና ገንዘብ ያስፈልጋል። ለመሆኑ ጆኒ የየት ሀገር ሰው ነህ? እስከዛሬ ሳልጠይቅህ? አማራ ነህ ትግሬ?»

«ደመቀ አሁን ይሄን ምን አመጣው? ኢትዮጵያዊ መሆኔን ታውቃለህ፤ እሱ በቂ ነው። የምን ዘር ቆጠራ ነው?»

«ጆኒ ዛሬ ኢትዮጵያዊ መሆን ብቻውን አያዋጣም። ጐሰኛነት የመሪዎቹ ዘረኛ ትውልድ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል። በደንብ ለመዝናናት ደግሞ የድርጅታቸው ደጋፊ መሆን አለብህ።»

«አትለኝም።»

«እያልኩህ እውነቴን ነው።»

«በውጪ ሀገር ያሉ የፖለቲካ ሰዎች ሲገቡ ተይዘው ይገደላሉ የሚባለውስ?»

«ቀንደኛ መሪዎች ከሆኑ አይቀርላቸውም። አንተ ግን እኮ ጆኒ ትግልህ የባህል ግንባታ እንጂ ፖለቲካ አይደለም። ስለዚህ ጨርሶ አትፍራ። የሚነካህ የለም።»

«ደመቀ ስለ ሰጠኸኝ መረጃ ከልብ አመሰግናለሁ» ብሎ ጆኒ ስልኩን ዘግቶ ስጋቱን በድፍረት አባበለው። በእርግጥ ጆኒ «የአበሻ ቱሪስት» ነኝ ቢል ኩነኔ አይሆንበትም። ሀገሩን የሚያውቀው ያልጠወለገች አበባ ሆና ነበር። ሰውም እርጥብ ሰማዩና ምድሩ እርጥብ ነበረና ሀገር እንደ እንጀራ አምሮት በባእድ ሀገር የጠወለገ ሳንባውን የአራስ ትንፋሽ ለመስጠት ወሰነ። ወደ ሀገር ቤት ለመሄድ ቆርጦ ሕልሙን እውን ለማድረግ የአየር ትኬት ገዝቶ አይሮፕላን ላይ ወጣ።

ያ የሰለቸውን የአውሮፖን ሰማይ ጨርሶ እስኪወጣ ጉዞውን ተኝቶ አሳለፈው። የአየር ላይ ምሳ ቀርቦ ተቀሰቀሰ። ትንሽ ጐራርሶ አቃረው። አንገቱን ወደ ጐን ዘንበል አድርጎ በመስኮቱ ቀዳዳ ወደታች አዘንብሎ እምድሩን ተመለከተ።



የዓባይ ወንዝ ከኢትዮጵያ ተነስቶ የሱዳንን ምድረበዳ አቆራርጦ ግብፅ ሀገር ለመድረስ የተጥመለመለ እረዥም ዘንዶ መስሎ ታየው። የሀገሩን ወንዝ ለማየት ያበቃውን አምላክ በልቡ አመሰገነ። በእንባ ጭጋግ መልሶ የዓባይን ወንዝ በርቀት ተመልክቶ «ዓባይ ነበር ዓባይ አለ ይኖራልም ኢትዮጵያ ከሁሉ በፊት ነበረች። ኢትዮጵያ አለች። ትኖራለች» ብሎ ያልተጻፈውን የአየር ላይ ጽሑፍ በሚነድ የበረሃ ፊደል አነበበ። አንድ ሁለት የሞቀ የሀገር ፍቅር ውሃ ጉንጮቹን ገምሰው አለፉ።

አይሮፕላኑ የሱዳንን ክልል አልፎ ኢትዮጵያ ገባ። ጆኒ ጥንት የሚያውቀው የሀገሩ አረንጓዴ መልክ ከሱዳን የበረሃ መልክ ባለመለየቱ አዝኖ እንደገና የእልህ እንባ እየተናነቀው ውድ ሀገሩ አዲስ አበባ በሰላም ገባ።

ጆኒ ያረፈው ሆቴል ሳይሆን አጐቱ ቤት ነበር።

ታዲያ ሲመሻሽ ከቦሌ የአየር ጣቢያ ሲመጣ አጐቱ የቆየ ህመም ስለነ በረባቸው የተኙት በጊዜ ነበር። ጠዋት ቁርስ ቀርቦ ቡና ተፈልቶ አጐትየው ከመኝታ ክፍላቸው ጋቢ ለብሰው ብቅ አሉ። ድሮ የሚያውቃቸው አጐቱ ባይመስሉትም ጆኒ ብድግ ብሎ እጅ ነስቶ ጉንጫቸውን በደንብ ስሞ ደግፎ እፎቴው ላይ አስቀመጣቸው። አጐቱ በጣም ከስተው አርጅተዋል። ዓይናቸውም ደክሞ የብርጭቆ ቂጥ የሚመስል መነጽር አድርገዋል። ጆኒ በልቡ «በ15 ዓመታት እርቀት ይህን የመሰለ ልዩነት» ብሎ አዘነ።

የቀረበለትን የእንጀራ ፍርፍር ቁርስ ከአጐቱ ጋር አብሮ በላ። የናፈቀውን እንጀራ ቁርሶ በፍርፍሩ ከማጣበቁ በፊት አሽቶ ሳመው። እረከቦት ተዘርግቶ ቡና ተፈልቶ እጣን ተጨሰ። ቤቱ ጆኒ የናፈቀውን መአዛ በማሸተቱ ደስ ብሎት የናፈቀውን የሀገሩን የትብቱን መሬት በመርገጡ ሙሉ ነፃነት ተሰማው።

በረንዳ ላይ ቆሞ የሀገሩን ትንፋሽ ተነፈሰ። ዓይኖቹ የአጐቱን ግቢ ዙሪያ ተመለከቱ። አበቦችና ጤናዳም ጥድና ስማቸውን የማያውቃቸው ልዩ ለዩ ተክሎች አካባቢውን አድምቀውታል። አጥሩ በደንብ በተጠረበ ድንጋይ የተገነባ፣ ጫፉ ላይ የጠርሙስ ስብርባሪ የተተከለበት ጥሩ የብረት መዝጊያ ያለበት ነው። እንኳን ሌባ የጦር ብርጌድም ቢሆን የሚደፍረው አይመስልም።

በጠራው ሰማይ ላይ የማለዳዋ ፀሐይ ብቅ ብላ ለብ ያለ ሙቀትን ትለግሳለች። አየሩ ደስ የሚል መአዛ ይዞ ይነፍሳል። ጆኒ የናፈቀውን የሀገሩን ጠረንና ሽታ በመከናነቡ እጆቹን ወደላይ ዘርግቶ የደስታ ትንፋሽ ተነፈሰ።

ያን ያሳለፈውን የ15 ዓመታት የአውሮፓ ጨፍጋጋ አየር ረግሞ የሀገሩን ፍልቅልቅ አየር ሞቅና መርቆ ለዚህ ያበቃውን አምላክ ከልቡ አመሰገነ።

እረፋዱ ላይ ልብሱን ቀያይሮ ከተማውን ለማየት ከግቢው ወጣ። በእርግጥ ከረዥም ዓመታት በኋላ ወደ እናት ሀገር ሲመለሱ ሁሉም ነገር እንደብርቅ እንደ አዲስ ነገር ሆኖ ይታያል። የቆየ ትዝታ ይቀሰቅሳል። የሚያስጨንቀው ግን ከአደጉበት መንደር ከተማሩበት አካባቢ ወይም ይሠሩ ከነበሩበት ቦታ ሲገኙ ነው። ያለፈውን በትዝታ፣ ዓይን እያስታወሱ ከነባሩ ሁኔታ ጋር አገናዝበው ሲመለከቱት በውስጥ የሚፍለቀለቅ ልዩ የታጨቀ የደስታም ይሁን የሀዘን ስሜት ሞቅ ይገነፍላል። ተመልሶ የማይገኝ የልጅነት ወቅት በጣሙን እያማረ ናፍቆ ያስጨንቃል።

ጆኒ በዚሁ ምክንያት ተነሳስቶ ከግቢ ወጣ። መጀመሪያ ድሮ የሚኖርበትን ዛኒጋባ ቤቱን ማየት መረጠ። የሕግ ሚስቱንና ሁለት ልጆቹን ትቶ የኮበለለበትን መኖሪያ ቤት ትንሽ መንደር ከአካባቢው ሲደርስ የሚስቱ ውበት የትዳሩ ሙቀት የልጆቹ ፍቅርና ናፍቆት እፊቱ ተደቀኑበት። የጐረቤቶቹ የወዳጅነት ሰላምታ፣ የመሐበራዊ ኑሮ ጠረን ሸተተው። ስሜቱ በትዝታ ሰመመን ተወጥሮ ፈዘዘ።

ብዙ ዓመታት የኖረበት ቤት ቢያረጅም ፍቅር የተመላበት ስለነበር ታላቅ ሕንፃ መስሎ ታየው። የሚያውቀውን ሰው ጨርሶ ከአካባቢው ፈልጐ አጣ። በገዛ ቤቱ በገዛ መንደሩ አዲስ መጥ ባይተዋር ሆነ። የቤቱን በር ከፍቶ መግባት አልደፈረም። አርሙኝ ከሚባለው መጽሐፍ ውስጥ የአቶ ተማቹ ታሪክ ትዝ አለው። «አልሞትኩም ብዬ አልዋሽም» ብሎ የቤቱን ግድግዳና ጣራ በርና መስኮቶችን የአካባቢውን ዙሪያ እንደ መሐንዲስ በዓይኖቹ ቃኝቶና ተመልክቶ የትዝታ እንባ እያነባ ከስፍራው እራቀ።

የጆኒ የሕግ ባለቤት ወ/ሮ አበባ ባሏ ጆኒ ከሀገር በወጣ በሦስተኛው ዓመት የሆነ ሀብታም የውጪ ሀገር ሰው ትተዋወቃለች። ሁለቱም ስለተስማሙ በስውር ተጋብተው ሁለት ልጆቿን ይዛ ከሀገር ትወጣለች። ያላግባብ ያደረገችው በጋብቻ ላይ ጋብቻ ወንጀል እንዳይታወቅባት በመስጋት ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት ከጆኒም ሆነ ከወላጆቿና ከሌላም ዘመዶቿ ምንም ግንኙነት የላትም። ያለችበትም ሀገር የት መሆኑ ጨርሶ አይታወቅም።

ጆኒ ይህን ወሬ ከሰማ ቆይቷል። ስደት ያመጣው ጣጣ በመሆኑ ድርጊቱን አሜን ብሎ ተቀብሏል። ግን የሚስቱና የልጆቹ ፍቅርና ናፍቆት ዘወትር ስለሚወተውተው ያለችበትን አድራሻ በሰውና በጋዜጣ አጠያይቆና አፈላልጐ ጥረቱ ከንቱ ሆኗል።



ጆኒ አሁንም ተስፋ አልቆረጠም። የሚስቱን ወላጆች ያሉበትን ቦታ አጠያይቆ ቤታቸው ደረሰ። አባትየው ከአዲሲቷ ሚስታቸው ጋር የሆነ ቦታ በመሄዳቸው ሊያገኛቸው አልቻለም። በቤት የነበረችው የባለቤቱ ታናሽ እህት ሊንዳ ገ/ሕይወት ነበረች። አድጋ ትልቅ ኮረዳ ሆናለች። ገና ሲገናኙ ትንሽ ግር ቢላትም ኋላ ጆኒ መሆኑን ስታውቅ በዘመድ ፍቅርና ናፍቆት አቅፋ ጉንጩን አገላብጣ ስማ በደንብ አስተናገደችው።

የባለቤቱ የአበባ እናት መሞታቸውን አባቷ ሌላ ሚስት አግብተው መኖራቸውን ጭምር አጫወተችው። ጆኒ በሁኔታው ሀዘንም ደስታ ተሰማው። የእህቷን ወሬ ማለት የሚስቱን ሁኔታ ቢጠይቅ የሆነ አረብ ሀገር እንደምትኖር መስማታቸውን ብቻ ነገረችው። «የደብዳቤም ሆነ የስልክ ምንም ዓይነት ግንኙነት እስካሁን ባለማድረጓ አባቷና መላ ቤተሰቡ እጅግ አዝኖባታል» ብላ የሷንም ቅሬታ በዓይኖቿ እንባ ጠብታ አሳየችው።

በቤቱ የከፋ ድህነት አይታይም። አባቷ የጡረታ አበልና እሷም በምታገኘው የወር ደሞዝ በጥሩ ሁኔታ ይስተዳደራሉ። ሊንዳ ገ/ሕይወት 12ኛ ክፍል ጨርሳ የሆነ ፋብሪካ ውስጥ ተቀጥራ ትሠራለች። እንዳጋጣሚ በዚሁ መሥሪያ ቤት እንዳለች ለሥራ ጉዳይ ከጀርመን ተልኮ የመጣ አንድ ኢንጂነር ሰው ተዋውቃለች። የተባለው ሰው የተላከበትን ሙያ አከናውኖ ሀገሩ ተመልሷል። ግን ሁለቱም የጠበቀ የደብዳቤ ግንኙነት አላቸው። እንዳውም ሰውየው በሱ አላፊነት ወደ ጀርመን እንደሚወስዳት ቃል መግባቱን ጭምር ለጆኒ አጫወተችው።

ጆኒ የውጪ ሀገር ኑሮ በጣም መራራ መሆኑን አስረድቶ በተለይ በእርጅና ጡረታ የወጡ አባቷን የትም ጥላ እንዳትሄድ የተቻለውን መከሮ፣ በሌላ ቀን ተመልሶ እንደሚጠይቃቸው ቃል ገብቶ ከቤቱ ወጥቶ ከሠፈሩ ርቆ ሄደ።

ጆኒ የሀገር ናፍቆቱን ለመወጣት ሁለተኛ ጉብኝት ያደረገው ብሔራዊ ቴያትር ነበር። የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን እንደጨረሰ የሙዚቃና የቴአትር ስሜትና ችሎታ ያላቸውን ልጆች መደበኛ የኪነት ትምህርት ለማስተማር ጥሪ በመደረጉ የተባለው ቦታ ሄዶ እሱም ውድድሩን አልፎ በዚሁ የኪነት ቤት መጠነኛ ጥበብ ቀስሟል።

በዳዊትና በጐልያድ ድራማ የተመረቀው ትልቁ ብሔራዊ ቴያትር ቤት አጠገቡ ከቆመው የድንጋይ ሐውልት አንበሳ ጋር በሩቅ ሲታይ ድሮ የነበረው ግርማ ሞገሥ አሁንም አልተቀነሰም። እውስጡ ሲገቡ ግን ባለመታደሱና በንጽህናም ጉድለት ጆኒ ድሮ የሚያውቀውን አዳራሽ

አልመስል አለው። አልፎ አልፎ ጥንት የሚያውቃቸውን ሰዎች በማግኘቱ ደስ አለው እነሱም እንደቤቱ ተንሳቁለዋል።

በእለቱ ትርኢት ባይኖርም ጆኒ አስፈቅዶ ብቻውን ከጨለመው አዳራሽ ውስጥ ገባ። የሆነ ቦታ ተቀምጦ በሀሳብ ትዝታ ተውጦ የጥንቱን የጠዋቱን ማለም ጀመረ።

«እንደገና አበራ ጠቅል ያንተ ሥራ» ተብሎ የተዘፈነበት፣ የቁንጅና ውድድር የተደረገበት፣ በርሃቡም ሰሞን «ሸዋላይ ዳመነ መላው ጥጋብ ሆነ» የተባለበትን መድረክ አይቶ አዘነ። እሱም በልጅነቱ የዳዊት ኦርኬስትራ አስተዋዋቂ ስለነበረ ሽክ ያለ ጥቁር ልብስ ለብሶ የተንጎራደደበትን ቦታ አስታውሶ አነባ። በለውጡም ጊዜ መልካሙ ተበጀ ከዘማች መዘምራን ጋር ሆኖ እልል በይ ሀገሬ የኩል ሆንሽ ዛሬ ያለበትን ቦታ በትዝብት ተመለከተ።

ጆኒ «ወይ አንቺ መድረክ ዛሬስ ምን ይቀርብብሽ ይሆን?» ብሎ ከአዳራሹ ወጥቶ በስተጀርባ ያለውን ቦታ ጎበኘ። የሙዚቃና የድራማ ትምህርቶችን የተማረበት ክፍሎች እንዳሉ አሉ። በዚህ ት/ቤት የተማሩ ብዙ ጓደኞቹ የት እንዳሉ ጨርሶ አያውቅም። በሙያቸው በርትተው ታዋቂነት ያገኙት ግን ዳዊት ይፍሩና ጥላዬ ገብሬ ብቻ ናቸው። ሌሎችም ቢኖሩ ሥራቸውና የኪነት የፈጠራ ችሎታቸው እስከዚህም አብቦና ጎልቶ ለሕዝብ አልታየም።

ጆኒ በዚሁ አይነት የእለቱን ጉብኝቱን አገባደደ። ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትም ያጠናቀቀበትን ቦታ ተመለከተ። ሌላም ዘመድና አዝማድ ጓደኛና ወዳጆቹ ቤት ሄዶ ናፍቆትና ፍቅሩን ተወጣ። ከቦታ ቦታ በታክሲ እየተዘዋወረ ብዙ ቦታዎችን ጎብኝቶ ተመልሶ እቤቱ ገባ።

ሮዚ የዓመት እረፍቷ ቢያልቅም አዲስ የፍቅር ጓደኛ በማግኘቷ አሁንም ያለችው አሜሪካ ነው። እሷም እንደ ጆኒ ለአሜሪካ ያላት ትዝታ ባይኖርም ብዙ ቦታዎችን ጎብኝታለች። ሥልጣኔውን አበክራ ቴክኒዎሎጂንም አድንቃለች። በሕዝቡ አስተዳደር ግን ቅሬታ አላት። ስንቶቹ ቬተናም ሄደው የተዋጉ ጥቁሮችና ሌላም ሰዎች ቤት አልባ ሆነው በየስርቻውና ጌቶ በተባለ ቆሻሻ መንደር ሰፍረዋል። ሥራ ፈቱ ስለበዛ በየእለቱ የሚፈጸመው ውንብድናና ወንጀል እጅግ የበዛ ነው። ሮዚ «አሜሪካ እንደዚህ ከሆነ የራሱን ሕዝብ ማስተዳደር ካቃተው ለምንድነው ዲቪ የሚባለውን ሎተሪ ለዓለም የሚያድለው?» ብላ



እራሷን ጠየቀች። በርግጥ ነገሩ እንቆቅልሽ ነው። አሜሪካ ዲሞክራሲ የሰፈነበት ሀገር ቢሆንም ብዙ ድሃና ሥራ ፈት ሕዝቦች አሉበት። ገንዘብ ላለው ግን ለመኖር አመቺ ይመስላል። ብዙም ዩኒቨርስቲዎች ስላሉ ከፍተኛ ትምህርት ለመከታተልም ይቻላል። ለጎበዝ ተማሪዎችም የነፃ ትምህርት ስኮላርሽፕ የሚሰጡም አሉ። ይህን ያወቀች ሮዚ የሕግ ትምህርቷን እዚሁ ለመከታተል ወስና በአዲሱ ጓደኛዋም እርዳታ የሆነ ዩኒቨርስቲ ስኮላርሽፕ እንዲሰጣት አመለከተች። ነገሩ በኮሚቴ ተጠንቶ መልስ እንደሚሰጣት ተነገራት።

ጆኒ ኢትዮጵያ ከገባ ሳምንት አለፈው። ጀርመን ሳለ በዝና ተዋውቆ ደብዳቤ የጻፈላትን እመቤትን እስካሁን አላገኛትም። በሆነ ድርጅት ውስጥ ሥራ ተቀጥራ አንድ ሳምንት ያህል ክፍለ ሀገር ሄዳለች።

ጆኒ በዚህ አጭር ጊዜ ከብዙ ታክሲ ሹፌሮች ጋር በደንብ ተዋውቋል። የሱንም ሙያ እንደነሱ መሆኑን ሳይደብቅ ነግሯቸዋል። ገቢያቸውን ከገቢው ጋራ፣ ችግራቸውን ከችግሩ ጋር እያወዳደረ ብዙ ትምህርቶችን አግኝቷል። ግን በየምሽቱ እንደ ልብ ታክሲ ስለማይገኝ የሆነች አንድ አሮጌ ማርቼዲስ ለወር ያህል ተከራይቷል።

ጆኒ የሆነ ምሽት ውሃ ስለጠማው ቀዝቃዛ ቢራ ለመጠጣት መኪናውን አቁሞ ፒኮክ ከሚባል ባር ገባ። ብዙ ወንበሮች ተይዘዋል። ሴትና ወንዶች ተደባልቀው እርስ በእርሳቸው በሞቀ ስሜት ይወያያሉ። የውጪ ሀገር ለስላሳ ሙዚቃ ጎልቶ ይሰማል። ቤቱ እንደዝናው ሰፊ አይደለም። መሐሉ ላይ የተጋደመ ትልቅ አኩራሪየም አለ። ከውበቱ ይልቅ ስፍራውን አጥብቦታል። ገና ከውጪ ለገባ የታፈነና የምግብ ሽታ ያውዳል። ማዶ ጥግ አንዲት ቆንጆዬ ልጅ ብቻዋን ሆና ሲጃራ እንደ አክርማ በጥርሷ ይዛ በትካዜ ተውጣለች። ከጎኗ ያልተያዘ ትርፍ ወንበር ስላለ ጆኒ ይቅርታ ጠይቆ ተቀመጠ። አሳላፊው ድራፍት እንዲያመጣለት ነግሮ አጠገቡ ያለችውን እየፈራ «ምን ልጋብዝሽ?» አላት በመሽኮርመም «ለስላሳ» አለች። «አይ እንደኔው ሸካራ አይሻልሽም?» ሲላት ከት ብላ ስቃ «እሺ ለኔም ድራፍት» ብላ ሲጃራዋን ሳብ ሳብ አድርጋ ጭሱን ወደላይ አቦለቀችው። ትንሽ ጥርሷ ቢበልዝም ስትስቅ የደስ ደስ ያላት «ልሙትልሽ» የምታሰኝ የቆንጆ ፉንጋ ናት።

ከጥቂት ዝምታ በኋላ ድራፍታቸው መጥቶ ብርጭቆአቸውን አጋጭተው ተጎነጩ። ቅድም በትካዜና በሀዘን የተዋጠችው ወጣት አሁን ደማቅ ጨረቃ መሰለች። «ስምሽ ማን ይባላል?» «ቤቲ» አለችው

«የምን ቤቲ ኢትዮጵያዊ አይደለሽም እንዴ?» «ነኝ» «ታዲያ ስምሽ...» ብሎ ሳይጨርስ «በመሠረቱ ስሜ ቤተልሄም ነው በአጭሩ ሲጠራ ግን ቤቲ እባላለሁ።»

«አንተስ?» አለችው። «ጆኒ» አላት ከት ብላ ስቃ «እባክህን አትቀልድ» አለችው።

«አልቀለድኩም እውነቴን ነው» አላት። «በእርግጥ ስምህን ትመስላለህ» «ምን ማለትሽ ነው?»

«አለባበስህ የጠጉርህ አቆራረጥና ወዝህ በአጠቃላይ ሁኔታህ ልክ የአበሻ ቱሪስት ቁርጥ ነህ ስለዚህ ጆኒ ብትባል አያስገርምም። ለመሆኑ ከየት ነው የመጣሽው? ከDC ወይስ ከሌላ»

«ምንድነው ዲሲ?»

«ዋሽንግተን ዲሲ ነዋ! አሜሪካ!» ብላ ከት ብላ ሳቀች።

«አይ እኔ ከዛ አልመጣሁም ከዚሁ ከባህር ዳር ነው» አላት ዋሽቶ።

«እባክህ የባህር ዳር ልጆች ጆኒ አይባሉም ጆማነህ ወይም ጆንበሬ እንደሆነ ንገረኝ»

«ቤቲ በመሠረቱ ስሜ ዮሐንስ ነው ከፈረንጆች ጋር ስለምሠራ ጆኒ ይሉኛል። በእርግጥ ስሜ ነው።»

«ከፈረንጆች ጋር የምትሠራው የት ነው እውነቱን ንገረኝ» ብላ አስጨነቀችው።

«በኋላ እነግርሻለሁ» ብሎ ሌላ ድራፍት እንዲጨመርላቸው ላሳላፊው አዘዘ።

በአጭር ጊዜ ብዙ ጊዜ እንደሚተዋወቁ ሰዎች ሆኑ። ጆኒ በእድሜ ቢበልጣትም አንቱታውን ትታ «አንተ» እያለች ስለጠራችው ደስ አለው።

«ለመሆኑ ቤቲ ማንን እየጠበቅሽ ነበር?»

«እንዳንተ ያለ ከባህር ዳር የመጣ የአበሻ ቱሪስት»

«ያልገባኝ ቤቲ ምንድነው የአበሻ ቱሪስት?»

«አ! ጆኒ እንዳንተ ያለ ከውጪ የመጣ»

«እሺ ቤቲ እኔስ እንዳልሽው ቱሪስት ልሁን አንቺ ምንድነሽ?»



«እኔማ የቱሪስት አስተናጋጅ አጫዋች ነኝ። 12ኛ ክፍል ጨርሼ ሥራ አጣሁ ምን ላድርግ» ብላ እንደበፊቱ ተከዘች። ትካዜዋን ለመለወጥ ጆኒ የቀረበውን ድራፍት አንስቶ ሰጣት። ሁለቱም ብርጭቆቻቸውን አጋጭተው በድጋሚ ተጐነጩ። ቤቲ ፈገግ ብትልም ውስጧ ችግር ሀዘን እንዳለባት ይነበባል። ገና 23 ዓመት ወጣት ነች። ጆኒ «እራት ልጋብዝሽ» ቢላት ቤቲ «ሌላ ቦታ ይሻላል» ብላው ተያይዘው ወጡ።

ጆኒ የሀገሩን ያፋንጋ ቋንቋ በደቂቃ ተዋውቆ «እራትሽ እራቴ ውሃሽ ውሃዬ» ብሏት ከጐኑ ልክክ ብላ ስትወጣ ለ15 የፈረንጅ ክረምት ያለመውን ስዕል አፊቱ ወርዶ ተነጠፈ።

የፒኮክ በራፍ በመኪና ተሞልቷል። ብዙ ሰዎች የሚዝናኑት መኪናቸው ውስጥ ሆነው ነው። ጆኒና ቤቲ እጅ ለእጅ ተያይዘው እመኪናቸው እስከሚደርሱ የሱቅ በደረቴዎች ግርግር አወካቸው። «ፋዘር ሳሙና ሶፍት ሲጋራ ኮንዶም ወዘተ.» እያሉ እንባረቁባቸው።

ቤቲ ፈጠን ብላ አንድ ፓኬት ኮንዶም ገዛች። ጆኒ ቤቲን በአድራጐቷ አደነቃት።

«ኮንዶም ለኤድስና ለሌላም በሽታ መከላከያ ብቻ ሳይሆን ለወሊድም መቆጣጠሪያ ይበጃል። አባት ከሌለው ዲቃላ ከመውለድ፤ መድኃኒት ከሌለው በሽታ ከመጠበስ፤ ኮንዶም ጠንካራ የጤና መጠበቂያ ጋሻ ነው» «ታም ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ» ብሏት እቅፍ አርጐ ጉንጪን ስሞ እንደ ወዳጁ ቀጭን ወገቧን ይዞ የመኪናውን በር በቀኝ በኩል ከፍቶ በአክብሮት አስገብቶ ተያይዘው ሄዱ።

ቤቲ በጆኒ አድራጐት አክብራ ወደደችው። በሃሳቧ ግን ጆኒ ለኮንዶም ማስታወቂያ ከውጪ ሀገር ተልኮ የመጣ ሳይሆን አይቀርም ብላ ጠረጠረች።

ትንሽ ተጉዘው ወደ ወሎ ሰፈር ታጥፈው የተባለው ቦታ ደረሱ። ልኳንዳ ቤት ነው። ከውስጡ ግን እንደነገሩ የሆነ ምግብ ቤት አለ። ጆኒ ለመግባት ተግደረደረ። ቤቲ አደፋፍራው ሁለቱም ገብተው ጥጉ ስፍራ ተሰጣቸው።

አንድ ኪሎ ሥጋ አስቆርጠው ግማሹ ጥሬ ግማሹ ጥብስ ተደርጐ በትልቅ ትሪ ከአዋዜና ሚጥሚጣ ጋራ ቀረበላቸው። ጆኒን ሚጥሚጣው

ቢፈጀውም ፈረንጅ ሀገር ሆኖ የተመኘውን የሀገሩን ምግብ በማግኘቱ ደስ ብሎት ቤቲንም እያጐረሳት አብረው በሉ። በላዩ ላይ የበደሌን ቢራ ደጋግመው አወራረዱበት። ሆድ ሲሞላ እራስ ባዶ ወኔ ንቁ ስለሚሆን የበለጠ ተቀራረቡ። ሎጋው ሽቦም ቀስ ቀስ አለና መተሻሸት ጀመሩ።

ጆኒ በእለቱ ከዚች ትንሽ ልጅ ጋር ቀርቶ ከሌላም ቢሆን የመዳራት እቅድና ወኔ አልነበረውም። ግን ግንኙነታቸው ስለጠነከረ ስሜቱ ተነካ። በዝና የሚያውቃትን እመቤትን ሳያገኝ እንዲህ ያለውን ወራዳ ሥራ መሥራት አሳፈረው። ሞራሉ እንቢ ብሎ ታገለው።

ጆኒ በስሜት ተቁነጠነጠ። የሆነ የአዋቂ ጥቅስ በሃሳቡ ትዝ አለው። «ሀብታም ማለት በቃኝን የሚያውቅ፣ ኃይለኛ ማለት ስሜቱን የሚቆጣጠር» ሰው ነው ብሎ ከአጠገቧ ፍንጥር ብሎ ተነስቶ ሰዓቱን ተመለከተ። ከምሽቱ ሦስት ሰዓት አልፏል። አጐቱ «ሀገሩ ድሮ አንተ እንደምታውቀው አይደለም ተበላሽቷል ወንበዴው በርክቷልና በጊዜ እንድትገባ» ብለው ስላስጠነቀቁት ከቤቲ ጋር ሌላ ቀጠሮ ወስዶ ብቻውን ቤቱ መግባት መረጠ።

ቤቲ «በቃ ጥለኸኝ ልትሄድ ነው?» አለችው በሚያሳዝን ድምፅ።

«አልጥልሽም አይዞሽ ቤትሽ ወይም የቅድሙ ሰፍራ አደርስሻለሁ» አላት አብሮ የመሆንን ጥያቄ በማደናገር አፅናንቶ።

«ለመሆኑ የትኛው ሆቴል ነው ያረፍከው?»

«ሆቴል አይደለም አጐቴ ቤት ነው» አላት።

«ውይ እድሌ» ብላ ተከዘች።

«ምነው»

«ጆኒ ማነሴን አትይ የማስተዳድራቸው ብዙ ቤተሰቦች አሉኝ» አለች እንባ እየተናነቃት። ጆኒ ሁኔታውን አይቶ ከልብ አዘነላት። ኪሱ ውስጥ የነበረውን ገንዘብ አውጥቶ ሰጥቶ እቤቷ አደረሳት። ቤቲ ጆኒ ሳይነካት ይሄን በማድረጉ እየቆጫት ተገርማ ከልቧ አመሰገነችው።

ጆኒ በቤቲ ሁኔታ ቅር ቢለውም በሞራል ይዞቱ ስሜቱን በኃይሉ ስለ ገታው ተደስቶ እንደ አርበኛ እየፎከረ መኪናውን ጠምዝዞ የቦሌን መንገድ ይዞ ወደ አሎምፒያ አመራ።

ለወትሮ ጠጥቶ መንዳት አይወድም እንደ አውሮፓ ችግር ስለሌለው ግን ተላምዶታል። ለጤና ያድርግለት እንጂ ትራፊክ ከሌለ እንደሌሎቹ



ቀይ መብራት እየጣሰ ይነዳል። አልፎ አልፎ ደንቡን ለማስከበር ቢሞክርም ከኋላው ያሉት መኪናዎች በክላክስ ጡሩንባ አያስቆሙትም። ከትራፊክ ቀይ ማብራት የቡና ቤት ቀይ ሰገነት ውስጥ ለመግባት ይጣደፋሉ። ሰውም ካላያቸው የገጩትን ገጭተው ያመልጣሉ። ቢያዙም በገንዘባቸው ጉርሻ ይገላገላሉ።

ደግነቱ የለሊቱ ትራፊክ እንደቀኑ አይደለም። ፀጥታው ያስፈራል። በቦሌ መንገድ ግራና ቀኝ አልፎ አልፎ «የለሊት እርግቦች» የሚባሉ ወጣት ልጅአገረዶች በአጭሩ ለብሰው መንገድ ላይ ቆመዋል። መኪና ባለፈ ቁጥር እጃቸውን እያራገቡ አብረው ይሮጣሉ። ጆኒ በሀዘን እነሱን አልፎ በቅሎ ቤትን አቆራርጦ አጐቱ ቤት ደረሰ።

ሮዚ አሁንም ያለችው አሜሪካን ነው። ከአዲሱ ፍቅረኛዋ ከአሮን ጋር ሆና ጉብኝቷን ቀጥላለች። አሮን ሮዚን ወዶ ከልቡ ይጨነቅላታል። የተሟላ መስተንግዶ ለመስጠት የዓመት ፍቃድ ወስዷል። ውሎና አዳራቸው አብሮ ነው። ልክ በቅርቡ እንደተጋቡ ሙሽሮች ተያይዘው ይሳሳማሉ። ፍቅራቸው አብቦ በየአንዳንዳቸው ልብ ውስጥ መፈንዳት ጀምሯል።

ሮዚና አሮን ባይጋቡም ለፍቅራቸው የትዝታ መሠረት ለመጣል እንደሙሽሮች የሀኒሙን ጊዜያቸውን በታላላቅ ቦታዎች አብረው አሳልፈዋል።

ዳላስ የቶክሳስ ባርኔጣ አድርገው ፈረስ ጋልበዋል።

ላስቬጋስ ቁማር ተጫውተው ሳይከስሩ እድላቸውን ሞክረዋል።

ፍሎሪዳ የሚገኘውን የቫልድ ዲስኒን የሚደነቅ ትንሽ ከተማ ሁለት ቀን ሙሉ ተዘዋውረው ጐብኝተዋል



ኒውዮርክ ትልቁ ከተማ ሄደው የሳት ፋና ከያዘችው የሊበርቲ ሐውልት ጋር ፎቶ ተቀርጸዋል። በከፍተኛነቱ በዓለም የታወቁ ትን ሰማይ ጠቀስ መንትያ ፎቆች ላይ በሊ ፍት አብረው ወጥተዋል።

ሮዚ ታች እንደ ጉንዳን የሚርመሰመ ሱትን ፍጥረቶችና ተሽከርካሪዎች አይታ አደነቀች። ገና ጀርመን እንደመጣች ብሎክ ዲክ ከሚባ ለው ሠፈር 20ኛ ፎቅ ላይ ሆና ያየችውን ከዚህ ጋር በማወዳደር «ዓባይን ያላየ» ብላ ተርታለች።

በመጨረሻም የሆሊውድን ትልቅ የፊልም መሥሪያ ኢንዱስትሪ ጐብኝተው ከአንዳንድ የፊልም ባለሙያዎችም ጋር ተዋውቀዋል። ሮዚ ከዚህ ጉብኝት በኋላ ስሜቷ ተለዋወጠ። ጥብቅናውን ትታ የፊልም አክተር መሆን አማራት። ይህንንም አጠገቧ ላለው የልብ ወዳጇ አማከረችው። አሮን በሮዚ ተለዋዋጭ ስሜት አልተከፋም። ለዚህም የኪነት ሙያ ችሎታ ይኑራት አይኑራት ጨርሶ ስለማያውቅ የሆነ ታሪክ አስታውሶ አጫወታት።

«አሜሪካን ውስጥ የሚገኝ አንድ የፊልም ካምፓኒ በየዓመቱ ለፊልም ሥራ የሚበጅ የኪነት ችሎታ ያላቸውን ሰዎች ጋብዞ በማወዳደር ይመርጣል።

አንድ ገጠሬ ኤልቪስን በፊልም አይቶ በማድነቅ እንደሱ ለመሆን ጊታር ገዝቶ እየዘፈነ በመጫወት ለረዥም ጊዜ ሲለማመድ ቆይቷል። ታዲያ ይህን ማስታወቂያ እንደሰማ ጊታሩን አንግቶ በፈረስ ተቀምጦ እየጋለበ እውድድሩ ቦታ ደረሰ። ችሎታውን እንዲያሳይ ተጠይቆ በጥሩ ሁኔታ ጊታሩን እየመታ ዘፈነ። ያሳየው ትርዒትና ችሎታ ውድድሩን ባለመመጠኑ አልተቀበሉትም።

ገጠሬው ተበሳጭቶ ጊታሩን አንግቶ በመጣበት ሁኔታ ፈረሱ ላይ ጡብ በማለት በሃይለኛ ፍጥነት እየጋለበ እቤቱ ተመለሰ። በመኪና ተከትሎት የነበረ የፊልም ኩባንያው የመራጭ አንዱ ኮሚቴ «በችሎታህ ለፊልም ሥራ እንፈልግሃለን» አለው።

ገጠሬው ተገርሞ «በምን ችሎታዬ በድምጼ ወይስ በጊታር አመታቴ?»

«በሁለቱም አይደለም የመረጥንህ የፈረስ ላይ አወጣጥህና የሽምጥ ግልቢያህ እጅግ የሚያስደስት ነው። በእሱ ችሎታህ ነው የመረጥንህ» ሲባል ገጠሬው ከት ብሎ ሳቀ። እንደ ችሎታ ያልቆጠረው የዘወትር ተራ ልማዱ ለፊልም የጥበብ ሥራ በመመረጡ ተገርሞ ፈዘዘ።»

«ስለዚህ ማንኛውም የአክተርነትን ጥበብ ባለሙያ ለመሆን የሚሻ ሰው ሁሉ አስቀድሞ አንገቱን ዞር አድርጐ ከላዩ ያሉትን ወይም ከጐኑ ጐልተው የሚታዩትን የእሱነቱን ተሰጥኦና ችሎታ ፈልጐ መድረስ አለበት» ብሎ ሮዚን መከራት።



በርግጥ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ብዙ ታዳጊ ሀገሮች የልጆቻቸውን የተፈጥሮ ችሎታ መዝነው አያዩም። ሁሉም የሚመሯቸው የጥበብን ፈለግ በሚያስከትል ጐዳና ሳይሆን ገንዘብን በሚያስገኝበት ሙያ ይሆናል። ሮዚ በመጀመሪያ ሆስተስ ቀጥሎም ፓይለት ለመሆን ተመኝታ ሳታውቀው የታክሲ ሹፌር የምድሯ ጥቁር ፓይለት ሆናለች። ቀጥላም የሕግ ጠበቃ ወይም የተዋጣለት የፊልም አክተር ተዋናይ ለመሆን ከጅላለች። ችሎታዋን መዝና በዓላማዋ ፀንታ ጥረት ካደረገች ከሁለቱ አንዱን ሙያ እንደምትይዝ ጥርጥር የለውም።

የሮዚና የአሮን የዓመት እረፍት ጊዜ በዚሁ ጉብኝት ተገባደደ። የገንዘባቸውም ቦርሳ እያደር ከስቶ መነመነ። ግንኙነታቸው ግን መውደድን አልፎ ፍቅርን መሠረተ። ልባቸው በስሜት በልጽጐ አበበ።

ሁለቱም ባይጋቡም አብሮ የመሆን የሀኒሙን ጊዜያቸውን ጨርሰው ወደመጡበት ቦታ ተመልሰው አሮን መኖሪያ ቤት ተያይዘው ገቡ። መላ አካላቸው በረዥሙ ጉዞና ጉብኝት ዝሎ አልደከመም። የፍቅር ሀብታም ልባቸው በልጽጐ ብርታት አግኝተዋል።

ገና እቤት እንደደረሱ እርስ በእርሳቸው ተያይዘው ተቃቀፉ። የሞቀ ትኩስ ደማቸው በመላ አካላቸው ተዘዋውሮ ተንሸራሸረ። የወሲብ ስሜታቸው ተቅበጥብጦ ቀነዘረ። ሰውነታቸው በፍቅር ወላፈን ወበቀ። ጥቁር ገላ ከጥቁር ገላ፣ ነጭ ላብ ከወዛ ነጭ ላብ ጋር አብሮ ተቀባብቶ ተወሃደ። ዓይኖቻቸው ተስለመለሙ። ከንፈር ለከንፈር ገጥመው በመሳሳም ተገማመጡ። የሞቀ ትንፋሽ ተለዋወጡ። በወሲብ የፍቅር ፈረስ ላይ ወጥተው በፍራሽ ሜዳ አብረው ጋለቡ። ድምጻቸው ከአልጋው ስጢታ ጋር ሆኖ አብሮ የወሲብ ፉጨት አፏጩ።

የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ የንጋቱ አየር እንደ አሜሪካኑ ካሊፎርኒያ አይሞቅም። የጠዋቷ ጀንበር በምሥራቅ በኩል ብቅ ብላ ወጥታለች። ሙቀቷ ገና ከለብታ አላለፈም። ወደላይ አንጋጦ ያያት ባይኖርም ውበቷ ከወትሮ አልተለወጠም። በእጅ የያዙት ወርቅ ሆኖ የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ አንጋጦ ወይም አተኩሮ በማየት ስለተፈጥሮ ያለው አድናቆት እጅግም ነው።

ጆኒ የሆነ ቀጠሮ ስላለበት በዚህ ወቅት የተነሳው ማልዶ ነው። ቢጃማውን እንደለበሰ በረንዳ ወጥቶ እጆቹን ዘርግቶ ተንጠራራ። የጠራውን አየር ተንፍሶ ተዝናና። የናፈቀውን የሀገሩን ማእዛ ደጋግሞ

በማሽተት ስሜቱ ጠገበ። የንጋቷን ጀንበር ተመልክቶ ተፈጥሮን አድንቆ ተመልሶ ገባ። ቁርሱን እንፍርፍር በልቶ፣ ሽክ ያለ ልብስ ለብሶ ያቺን የኪራይ መኪና ይዞ ከአጐቱ ግቢ በቀስታ እየነዳ ወጣ።

መንገዱ በትራፊክ ብዛት ጥቅጥቅ ብሏል። ተስማምቶ በመኪና ጥሩንባ ተደነቋቁሮ ሹልክ ጥምዝዝ ቆም ለቀቅ እያደረጉ የሚጓዙበት ጉዞ ነበር። በዚህ ማለዳ ጠዋት አህያው ከብቱ ውሻው እግረኛው መሐል ለመሐል ገብቶ ስለሚያቋርጥ እንደ ጆኒ ከውጪ ለመጣ ሹፌር እስከሚለመድ ያደናግራል። ጆኒ ግን በዚህ ሁኔታ አልተደናገጠም። የሀገሩ ሁኔታ መልክ ስለሆነ ረካበት። «አጤ ያሳመሩት አስፋልት ከእሳቸው ጋር የውሃ ሽታ ሆኗል» ብሎ በድፍረት መንዳቱን ቀጠለ።

ዋናው መንገድ አልፎ አልፎ ገደልና ጐርባጣ ስለሆነ እየመረጡ መሄድ አስፈላጊ ነበር። ለቪዛ ጉዳይ ከአክስቱ ልጅ ጋር ጀርመን ኢንባሲ ቀጠሮ ስላለው በሰዓቱ ለመድረስ ተጠራጠረ። የመንገዶች እድሳት እንደመኪናዎች ብዛት ተጠንቶ አልተሠራም። አንድ የግል መኪና አሽከርካሪ ለመንገድ መጠቀሚያ ግብር በዓመት የሚከፍለው ከ42 ብር አይበልጥም ይባላል።

«ሩቅ ሀሳቢ ቅርብ አዳሪ» እንደሚባለው የከተማው ከንቲባና የሀገሪቱ መሪዎች ለስልጣንና ሹመት በመወዳደር «እሾም ያለ ታግሶ አፀድቅ ያለ መልኩሶ» ስለሆነ ለሀገር የሚያስብ ጨርሶ የለም። ይህ ባይሆንማ ባለመኪና ነኝ ብሎ ለመኪናው መጠለያ ጋራዥ በግቢው የጠለለ ሁሉ ቢያንስ በዓመት 420 ብር የመንገድ መገልገያ ኪራይ ቢጠየቅ መክፈል ያቅተው ይሆን? በእርግጥ ችግሩ ገንዘብ ብቻ እንዳልሆነ ጆኒ ነገሩን ገምቶ ብቻውን እያሰላሰለ መሿለኪያን አልፎ ስታዲዩም አጠገብ ደረሰ።

ጆኒ በሆነ የትራፊክ ግጭት የሚሄድበት አቅጣጫ ስለተዘጋ መኪናውን አቁሞ የአካባቢውን ትርኢት ተመለከተ። ብዙ ታክሲዎች ሚኒ ባስና ውይይት አፍንጫና ጐናቸው የጐበጠ ኋላቸው የተገጨና የተጣመመ መብራታቸው ተሰባብሮ በፕላስቲክ የተጣበቀ ነው። ሹፌሮቹም ሲነዱ አንዱ አንደኛውን ተከትሎ ሲቆም ቆሞ መኪናውን



እያንፏቀቀ ወደፊት ይሄዳል። እርስ በእርሳቸው ባይጋጩም እንደሁነኛ ፍቅረኛ እየተሻሹና እየተነካኩ ይተላለፋሉ።

የታክሲዎቹ ደላላ ማለት ወያላዎች መኪናው ሞላ አልሞላ በልማድ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው «መርካቶ፣ ጣሪስ፣ መሳለሚያ፣ ካሣንቺስ፣ ቀበና፣ ፒያሳ፣ ቦሌ፣ ማዞሪያ» ወዘተ እያሉ ይጮሃሉ።

ታክሲ በቆመ ቁጥር ግር ብለው የሚመጡ የጋዜጣ የሲጋራ የሎተሪና የሌላም ቁሳቁስ ነጋዴዎች አሉ። ገና በአፍላ ወቅታቸው የሥራ አጥ ኢንዱስትሪያቸውን ለማስፋፋት ይጣደፋሉ። ይሻማሉ።

ዓይኖቻቸው የጠፉ ሕፃናት የተጐሳቆሉ ሽማግሌና አሮጊቶች ሌላም ችግረኞች ወጪ ወራጁን «ተዘከረን» ብለው ይማፀናሉ። የውስጡን እንጃ እንጂ ብዙዎቹ የታክሲ ተሳፋሪዎች ሁኔታቸው ከለማኞቹ የተሻለ አልነበረም።

ጆኒ በሌላ ቀን ይሄን የአበሻ ቱሪስት ያሰኘውን ልብስ ቀይሮ እነሱን መስሎ በታክሲ ለመዟዟር አቀደ። ድካሙ ምናልባት ለድርሰቱ ይጠቅም እንጂ የሕዝቡን ችግር አይፈታም። ሰሚ ካለ ግን የተሟላ ጥቆማ መስጠት ይቻላል ብሎ ገመተ።

ጆኒ በሰዓቱ ባይሆንም አርፍዶ ጀርመን ኢምባሲ ደረሰ። ዋናው ግቢ ተዘግቶ ብዙ ሰዎች አካባቢውን እንደ አንበጣ ወረውታል። የአክስቱን ልጅ አግኝቶ እሱም እንደ ሌሎቹ ደጅ ጥናቱን ተያያዘው። ሕዝቡ ቢዛ አግኝቶ ባሕር ማዶ አውሮፓ ደርሶ ጀርመንን ለማየት ጓጉቷል። የቻለው በጉቦ ያልቻለው በደጅ ጥናት ሳይታክት ይመላለሳል። የባእድ ሀገር ኑሮ የመረረው ጆኒ የነዚህን ሕዝቦች ድካምና እዛ ደርሰው የሚያገኙትን ደስታ ለመጨበጥ ያላቸውን ምኞትና ሕልም ገምቶ አእምሮው ባዘነ። ተራው ደርሶ ቢሮ ገብቶ የመጣበት ጉዳይ ሳይሳካ አዝኖ ከግቢው ወጣ።

የጠቋቆረ ደመና በአዲስ አበባ ሰማይ ላይ ረብቧል። አልፎ አልፎ ቦታ እየለየ ይዘንባል። የቀትሩ አየር ነፋሻማ ነው። የሰው ብዛትና ትርምስ የትራፊክ ጭንቅንቅ በጣም ከበዛበት መርካቶ አካባቢ ግን ይወብቃል።

ጆኒ የአክስቱን ልጅ ቤት አድርሶ የመጣው ወደዚሁ አካባቢ ነበር። እቃ ለመግዛት ሳይሆን የሀገሩን የተለያዩ ባህሎች ሊመለከት ነበር። የሰውን ልጅ ባህሪ ልማድና የራስ ወዳድነትን ጠባይ ለማየት ከተፈለገ

መርካቶ ትልቅ ኮሌጅ ነው። ጆኒ እንደ ጨረባ ተዝካር እንደዋርካ ወፎች የሚብላላና የሚንጫጫው ሕዝብ መሐል ገብቶ ተደባለቀ። የእርሻው ምርቱ ከአካባቢው ገበሬ ተዋጥቶ፣ የፋብሪካው ውጤት በመርከብ መአበል ታግሎ የሚደርስበት አውድማ መርካቶ እንደ ፈረንጆቹ መደብር ፀጥታ አልዋጠውም።

«የኡኡታው፣ የጡሩንባው የጩኸቱ የፌሽካው ሣግ የሰው የመኪና የከብት የፍግ የቁሳቁስ ትንፍግ ሲገፋተር ሲመዝርጥ ላቦት ለላቦት ሲላላግ ትንፋሽ ለትንፋሽ ሲማማግ...» የሚለው የፀጋዬ ድርሰት ጆኒን ትዝ አለው። አሁንም መርካቶ አልተለወጠም። ከሕዝቡ ብዛት በስተቀር አሁንም ያው ነው። ጆኒ የፈረንጅ ሀገር ኑሮ አዘናግቶት እንጂ መርካቶ እንደሆን ጥንትም ቢሆን ይኼው ነው። ጦም አዳሪው ካላቸው ሰዎች ቀምቶ የነፍሱን ማቆያ የሚቦጫቅበት የድሃ መስተዳደሪያ የሕዝቡ መገበያያ የባህል ቅይጥ ትርዒት የሚታይበት መድረክ፣ ልዩ ቦታ። መርካቶ በዓለም ከታወቁ ጣራ አልባ የደጅ ገበያዎች የመጀመሪያውን ሥፍራ የያዘ ትልቁ ሰፊ ሜዳ ነው።

ጆኒ የአበሻ ቁሪስትነቱን ተመልካች ሳያውቅበት ከሥፍራው እርቆ ቸርችል ጐዳና ደረሰ። ሜክሲኮ አደባባይ ከሚገኘው ሞቢል ቤንዚን ሞልቶ አደባባዩን ሳይዞር ባጭሩ ታጥፎ ወደለገሀር ሲያመራ በትራፊክ ፖሊስ ተያዘ። የጀርመን መንጃ ፍቃዱን ቢያሳይ መለወጥ እንደሚገባው ተነገረው። ባደረገውም ጥፋት ሠላሳ ብር ያለደረሰኝ ተቀጣ። ገቢው ለመንግሥት ሳይሆን ለፖሊሱ ኪስ መሆኑን አውቆ አልተከራከረም። እንኳን ከእሱ ከአበሻ ቁሪስት ከተራም ጋዜጣ ነጋዴ የፈለጉትን ያህል ቀጥተው ስለሚወስዱ በሠላሳ ብር በመገላገሉ አልገረመውም።

ጆኒ መሿለኪያን አልፎ፣ ወደ ግራ ታጥፎ በግ ለመግዛት ከመኪናው ወረደ። ሽማግሌ አጐቱ ጥርሳቸው እንደቀድሞ አጥንት ባይቆረጥምም ሙክክ ብሎ የበሰለ ሥጋ ይወዳሉ። «ፋዘር! ፋዘር! እኔጋ ይምጡ የአዳል የሰባ ጥቦት፣ ከፈለጉ ሌላ ሙክት አማርጠው ይውሰዱ» እያሉ የበግ ነጋዴዎች ከበቡት። በአራት መቶ የተገመተውን በሁለት መቶ ሃምሣ ገዝቶ እቤቱ ገባ። መቼም ይሄን ዋጋ በደህና ጊዜ በሰላም ያረፉት አባቱ ይህን ዛሬ ቢሰሙ ተመልሰው ይተኙ ነበር።

ጊዜው ከሰዓት በኋላ እረፋዱ ላይ ነበር። ጆኒ ቤት ገብቶ ተጣጥቦ ትንሽ አረፈ። የአዲስ አበባን ምሽት ለመጐብኘት ወስኖ ብቸኝነቱ



አስጠላው። በዝና የሚያውቃት እመቤት ከክፍለ ሀገር መመለሷን ለማወቅ ፈልጐ ስልክ ደውሎ አገኛት። ልቡ በደስታ ጮቤ እረግጦ አፉ ተሳሰረ። ድምጿ ደስ የሚል ቅላጼ አለው። ዓይን ለዓይን ለማየት ሁለቱም ተቻኲለው እራስ ሆቴል በዚሁ እለት ምሽት ለመገናኘት ተቀጣጠሩ።

ጆኒ ሰዓቱ እንደኤሊ ተንቀረፈፈበት። ቀኑ አልመሽ ብሎ ነጋበት። አከላቱን በድጋሚ ታጥቦ ልብሱን ቀየረ። የዛሬ አለባበሱ እንደ አበሻ ቁሪስት ሳይሆን እንደ አንድ ሚኒስቴር ነበር። ለወትሮ ለሌላ ቁም ነገር ቢዘገይም በዚህ እለት ግን ቀደም ብሎ እራስ ሆቴል ደረሰ። መኪናውን የሆነ ቦታ አቁሞ ያንን ተሽከርካሪ በር አሽከርክሮ ከአዳራሹ ሰገነት ጥልቅ አለ።

ለእራት ማባያ አፐሬቲቭ በኋላም ለትውውቅ ድፍረት ውስኪ አዞ የሆነ ቦታ ምቹ ጠረጴዛ ይዞ ተቀመጠ። ሰዓቱን ደጋግሞ ቢመለከት ልጅቱ አልመጣችም። የአበሻ ቀጠሮ በሴቶች ይሉኝታ ጋር ስለሚጨመር ልቡ ተጨነቀ እንጂ በመቤት ማርፈድ እንብዛም አልገረመውም። ዓይኖቹ ወደበራፉ አፍጥጠው «ለምን እሷን አልሆንችም» ብለው አማረሩ።

ከትንሽ ቆይታ በኋላ በአለባበሷ ያሸበረቀች ቀይ ካፖርት የደረበች ፈገግታ የተመላባት ውብ፣ ረዥም ዞማ ጠጉሯ በትከሻዋ የወረደ ኮረዳ ከየት መጣች ሳይባል እፊቱ ደማቅ ሙሉ ጨረቃ መስላ ከች አለች።

«ይቅርታ ዮሐንስ ነህ?» አለችው በለሰለሰ አንደበት።

«ነኝ» ብሎ ከመቀመጫው ተነሳ ሁለቱም ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳሙ። ልባቸው ቶሎ ቶሎ በመምታት በሁለመናቸው የሆነ ስሜት እንደኤሌትሪክ ተሰራጭቶ ነዘረ። ዓይን ለዓይን ተያይተው ተፋፈሩ። የቀረበላቸውን መጠጥ ብርጭቆአቸውን አጋጭተው ተጐነጩ። በብእራቸው ትውውቅ የጫሩትን መልክ በውን ተያይተው ተሳሳቁ። ጆኒ እድሜውን ወጣት አድርጐ ስለጻፈላት እሷም እንደሱ እራሷን ለየት አድርጋ ስለጻፈችለት አሁን ሲተያዩ ተፈራሩ። ግን ወይን አስታራቂዋ እውነትን እናግራቸው ተስማሙ።

መጀመሪያ እራት ለመብላት የቦሌን አቅጣጫ ይዘው ትንሽ እንደተጓዙ ወደቀኝ ታጥፈው ጋዜቦ ቡና ቤት ደረሱ። በራፉ አካባቢ ፓጄሮ ላንድ ክሩዘር፣ ፓትሮል ፎር ባይፎር ሌላም አዳዲስ መኪናዎች

ቆመዋል። ገና በቅጡ ሳይመሽ የእንግዶቹ ብዛት ለጆኒ ገረመው። እመቤትማ እንዲህ ያለውን ቦታ ጨርሶ አታውቀውም። አሮጌ ማርቼዲሳቸውን ዘበኛው ባሳየው ሥፍራ አቁመው ተያይዘው ገቡ። ጆኒ ባለቤቱን ስለሚያውቀው በደንብ ተቀብሎ አስተናገዳቸው።

ግቢ ውስጥ ገና ሲገቡ ጋዝ እየተጉነጨ የሚነድ የእሳት ምድጃ ስላለ አካባቢውን በማድመቅና በማሞቅ የደመራ ቦታ አስመስሎታል። እራታቸውን የዶሮ አሮስቶ የአሳ ጥብስና ፒሳ ከሰላጣ ጋር ቀርቦላቸው በደንብ ጣፍጧቸው በሉ። በላዩ ላይ የቀዘቀዘ ወይን ጠጅ ተጨመረበት። በኦርጋን ከሚሰማው ሙዚቃ ጋር አብረው ተዝናንተው ወደሌላ ለመሄድ ተያይዘው ወጡ።

አዲስ አበባ ከችግርዋ በስተቀር በአንድ በኩል ገና እርጥብ ናት። በተለይ አውሮፓ ለከረመ ለአበሻ ቱሪስት አዲስ አበባ የእናት ጓዳ ናት። የአውሮፓ የመንገድ ላይ ሺ ካሜራ እንኳን ያላገባትን ሴት ቀርቶ የሕግ ሚስትን ይዞ በጨለማ መሄድ ደፋር ልብ ይጠይቃል።

የምሽቱ አየር እንብዛም አልቀዘቀዘም። ሰማዩ በሚያማምሩ ከዋክብቶችና ደማቅ ጨረቃ ደምቋል። አካባቢው እንደመኪናው ብዛት ግር ግር የለበትም። ሰዓቱም እረፍዶ ገና እኩለ ለሊት አልሆነም። ጆኒ በዚህ በአንድ ቀን ግንኙነት እመቤትን ከዚህ አልፎ ሊዳፈራት አልፈለገም። ለመተያየት እራት በልተው ለመገባበዝ እንጂ ለሊቱን አብረው ለማሳለፍ እቅድ አልነበራቸውም። ብቻ ሁለቱም ሳይተፋፈሩ ተነጋግረው ለሊቱን አብረው ለማሳለፍ ወስነው ተስማሙ።

መጀመሪያ ፕላዛ ሆቴል ሄደው ልዩ የመኝታ ክፍል ያዙ። ታች ከሚገኘው የእንግዶች መዝናኛ ባር ገብተው ብዙ ነገሮችን አብረው አወሩ። ሁለቱም የፍቅር ጓደኛ የላቸውም። በደብዳቤአቸው መሠረት ግንኙነታቸው ከጓደኝነት አልፎ ለትዳር ምሥረታ መሆኑን በግልጽ ተወያዩ። እርስ በእርሳቸው ተቃቅፈው ተሻሹ። ከንፈር ለከንፈር ገጥመው ለመጀመሪያ ጊዜ የመውደድ የሞቀ ትንፋሽ ተለዋወጡ።

ጊዜ ሳያባክኑ መኪናቸውን አስነስተው ከሆቴላቸው ብዙ ያራቁትን የአዝማሪ ቤቶች ለማየት አቀዱ። መጀመሪያ የሸዋ ጌጥ ቤትን ጐበኙ። ዘፈኑ የደመቀ ቤቱ ያማረ ቢሆንም ብዙ እንግዶች አልነበሩበትም። የሀገር ልብስ የለበሰች ሹርቤ ቆንጆ ዘፋኝ በእንግዶቹ መሐል እየተዘዋወረች ትዘፍናለች። ታሞግሳለች። የፈለገችውን ስባ እስክስታ አብራ ትወርዳለች። ጆኒ እድሉ ደርሶት ከመቤት ጉያ ተነጥቆ ተወሰደ። አብሮም እስክስታ ወረደ። ግን አላወቀበትም። ማንቦ ሩንባ ቻቻ



የሚባሉት የአውሮፓ ዳንሶች ቢሆኑ ኖሮ ያስነካው ነበር። ሳይሆን ቀረ። በሀገሩ በወንዙ ዘፈን መንቃንቅ አቅቶት ፈዘዘ። የአበሻ ቱሪስትነቱ ታውቆ አሳፈረው። ይቅርታ ጠይቆ ጭፈራውን አቋርጦ እመቤትን ተደግፎ ቁጭ አለ። ሙዚቃው አልቆ የቀልድ ፕሮግራም ቀጠለ። ሁለቱም ትንሽ ጫወታውን አድምጠው እየሳቁ ወጡ። ጆኒ ግን የሳቀው በቀልዱ ሳይሆን በራሱ ነበር።

መኪና ውስጥ ገብተው ተቃቅፈው ተሳስመው አቅጣጫቸው ወደ ካሳንቺስ ጠምዝዘው ዮርዳኖስ ሆቴል ፊት ለፊት ጥሩ ምግብ ቤት ከሚባለው አዝማሪ ቤት ገቡ። ሰው ጢም ብሎ ሞልቷል። ሙዚቃው ይደለቃል። ይበላል ይጠጣል ይጨፈራል። ጋዝ የሚጉነጨው ምድጃ ይነዳል። ሁለቱም በሕዝቡ መሐከል አልፈው ተቃቅፈው ተቀመጡ። የሚሰማውን ሙዚቃ ትተው በሕሊናቸው ያለውን ዝማሬ ማዳመጥ ጀመሩ።

ሃይ! ሃይ ሃይ ሎጋ ሆይ
ሃይ ሎጋ ሃይ ሎጋ ሽቦ
የኛ ሙሽራ ቤላ ቤላ
ጣፋጭ ነሽ ከረሜላ።
 አጀባ ሆኗል ደጅሽ
 በየት ልይሽ!
አዱኛሽ ዛሬ ነው ዛሬ
እቴ ሸንኮሬ
ሆማ ሆማቱ ሆማ ሆማቱ
አላንቺ አይነጋም ለሊቱ
የታለ የደሙ ሸማ
እንድንስማማ
ብራንባ ሰበረልዎ
የኛ ልጅዎ...

በአንድ ቀን ግንኙነት ፍቅራቸው ጠንቶ ሕሊናቸው የትዳር የስሜት ሙዚቃ አቃጨለ። ሰውነታቸው በወሲብ ፍቅር ቋመጠ። ከዛ አዝማሪ ቤት በቶሎ ወጥተው ፕላዛ ሆቴል እጫጉላ ክፍላቸው ተያይዘው ገቡ። ልብሳቸውን ከመቅጽበት አወላልቀው ከንፈር ለከንፈር ገጥመው ተማጠጡ። ላብ ለላብ ተቀባብተው እንደነፃ ትግል ተያይዘው ተገለባበጡ። እሱ ከላይ እሷ ከሥር የወሲብ ጥማታቸውን ተካፍለው

እረኩ። በሽቶ ሳይታጠቡ «የራስ ሀገር የተፈጥሮ ጠረኗ ራሱ ከሺ ሽቶ ይበልጣል» አቶ ጆኒ በሀሳቡ ብራንባ ተሰብሮ የቀለመ ነገር ባይታይም አንሶላው በነጭ ላብ እረጥቧል።

እረፋዱ ላይ ሁለቱም ተነስተው ምሳ ለመብላት ወደ አዲስ አበባ የምግብ አዳራሽ አመሩ። ከፕላዛ ሆቴል ማዞሪያ ከማዞሪያ ካሳንቺስ ደረሱ። ይህ የቀጠሮ ቦታ እስካሁን መጠሪያ ስሙ አልተለወጠም። እሱ ብቻ ሳይሆን ፒያሳ መርካቶ ፖፖላሬ ካምቦ አስመራ ሌላም ቦታዎች የሚጠሩት እስካሁን በጣሊያንኛ ስም መሆኑን ጆኒ ገረመው።

እለቱ ቅዳሜ ቢሆንም የትራፊኩ ብዛት እንብዛም ከአዘቦቱ ቀናቶች አያንስም። መንገዱ ሰዎች እንደሚሉት ገበጣ የሚያጫውት ዓይነት ነበር። ቦታ እየመረጡ በትክክል መንዳት ያስፈልጋል። ከኋላ የሆነ መኪና ደጋግሞ ክላስክ አደረገ። ጆኒ በውስጥ መስታወቱ ተመለከተው። ሚኒ ባስ ታክሲ ነበር ወደጐን ቦታ ለቅቆ አሳለፈው። ሹፌሩ በጉንጩ ጫት በእጁ ሲጃራ ይዞ እያጉረመረመ ጥሎት አለፈ። የጫቱ ምርቃና አንቀዥቅዥ ታል። በአውሮፓ የታክሲ ሹፌሮች ለተሳፋሪዎቹ የሚያደርጉት ጥንቃቄና ክብረት ሀገሩ ባለመኖሩ አሳፈረው።

ጠጥቶ ወይም መርቅኖ መኪና ማሽከርከር እጅግ አደገኛ ነው። በዚህ ላይ የሕዝብ ማመላለሻ ታክሲዎች ኢንሹራንስ የላቸውም። «ክፉ አታምጣ» ብሎ ጆኒ እግዜርን ተማፀነ።

ካሳንቺስን አልፈው በፊት በር በኩል አድርገው አራት ኪሎ ደረሱ። የነፃነትን የድል ሐውልት እንደሙሽራ ዞሩት። ባይጋቡም ብራንባ ባይሣበሩም ለመጀመሪያ የፍቅር ግንኙነታቸው ጥሩ መታሰቢያ እንዲሆን ጆኒ አውቆ ያደረገው ነበር። የራስ መኮንን ድልድይ ተሻግረው የሀገር ፍቅርን ቴአትር ቤት ዳገት ሽቅብ ወጥተው ደጃች ውቤ ሠፈር አዲስ አበባ የምግብ አዳራሽ ደረሱ።

የምሳ ሰዓት ቢያልፍም በላተኛው በከፊል ሞልቷል። ገና ከደጅ ሲገቡ የምግብና የጠጅ ቃና ያውዳል። ቤቱ የጥንቱን ባህል ያለቀቀ ጥሩ መስተንግዶ የሚገኝበት አዳራሽ ነው። የአስተናጋጆቹ አለባበስና ፈገግታ «ከፍትፍቱ ፊቱ» ስለሆነ እንኳን እርቦት ጠግቦም ለመጣ ያባላል። ዋጋቸውም የተመጣጠነ ነው። ቀይ ወጣቸው ግን ለቁረስት ይፋጃል። ጆኒ ተለውጧል። ለውጡ ለሀገሩ በርበሬ ብቻ ሳይሆን አስተያየቱና አድራጐቱ ጭምር ምዕራባዊ ቁረስት አስመስሎታል።



የሚበሉትን አዘው ምግቡ እስከሚመጣ ብዙ ነገሮችን ተወያዩ። እመቤት በእርግጥ ጫወታ የምትችል ልጅ ናት። ስለኑሮ ስለፍቅርና ትዳር ስለወሲብ እንኳን ሳታፍር በመጫወቷ ጆኒ ወደዳት። በአጭር ጊዜ ውስጥ እጅግ ከመግባባታቸው የተነሳ አንዳንዴ ያለቋንቋ በጥቅሻና በንክኪ ስሜት መግባባት ቻሉ። በዚህም አብረው እየቀለዱ ሰቀው ተጫወቱ። ምግቡ በትልቅ መሶብ ቀርቦ እየተጐራረሱ በልተው ጠገቡ። እመቤት ጆኒን «ጀርመኖች በሀገራቸው ባህል እንደ ኢትዮጵያ ይጐራረሳሉ?» ብላ ጠየቀችው።

«አዎ ከሆዳቸው ጋር ይጐራረሳሉ በደንብ ይሠራሉ እራሳቸውን ከሌላው አስበልጠው ይወዳሉ ታዲያ ራሳቸውን በራሳቸው ሲያጐርሱ ምግብን በአፍ ብቻ ሳይሆን በባንክ አካውንታቸውም ይቀበላሉ» አላት።

ሁለቱም ተሳስቀው የመጠጥ ብርጭቋቸውን አጋጭተው ተጐነጩ። የዛሬውን ምሽት ከከተማ ወጣ ብለው ደብረዘይት ለማሳለፍ ተስማሙ። ልብስ ቀያይረው የተባለው ቦታ ሄደው እራስ ሆቴል አደሩ። ንጉሥ በሌለበት ሀገር ደብረዘይትን በግላቸው ቁጥጥር ውስጥ ያስገቡ መሰላቸው።

በማግስቱ ሆራ ሄደው በጀልባ ተንሳፈው በግመል ተጉዘው የአበሻ ቁረስትነታቸውን በፎቶ ግራፍ ተቀረጹ። እንደሙሽሮች በፍቅር ተያይዘው የሀኒሙን ሽርሽር በባሕር ዳርቻ አደረጉ። ጆንበሯ የምዕራብን አድማስ ይዛ ተለጥፋለች። ብርሃኗ ባሕሩ ላይ አርፎ እንፀብራቂው እነሱ ላይ አርፎ ወገገ። የተፈጥሮ ውበትን አድንቀው እርስ በርሳቸው ተቃቅፈው ተሳሳሙ። ጆንበር ሳትጠልቅ መኪናቸው ላይ ወጥተው ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ጀመሩ።

ቀዝቃዛው አየር የፍቅር ላባቸውን እንዲጠርግላቸው የመኪና መስኮታቸውን ከፈቱ። የእመቤት ዞማ ፀጉር በንፋሱ ወደላይ ብን ብለው ታየ። የጆኒ ልብ ይቺን የመሰለ ቆንጆ ከጐኑ ተለጥፋ በማየቱ አኮራው። መንገድ በደንብ ተስተካክሎ የተሠራ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ሳያስቡት ድንገት ከራውን ሆቴል ደረሱ።

መክሰስ ብጤ ቀማምሰው የሚጠጡትን ለመጠጣት ብርጭቆ ሲያጋጩ የእመቤት ብርጭቆ ከእጇ አምልጦ ወደቀ «የሸዬ ድረሽ» ብላ ጮኸች። ጆኒ የሴት ስም በመጥራቷ አልቀናም። ማን መሆኗን ጠይቆ አክስቷ መሆኗን ነገረችው። እመቤት በትንሹም በትልቁም የሸዬን ታንሳ እንጂ ለከባድ ቁም ነገር የምትምለው በአባቷ «ተሾመ ይሙት» ብላ ነው። ከታቦት ኡራኤልን ትወዳለች ታምረኛ ታቦት ነው ትላለች። ለእሷ ያደረገላት ባይኖርም ስለታምሩ ተናገረች። ኤድስ ማስለቀቁን፣ እውር

ማብራቱን፣ ሽባ ማስኬዱን፣ ቪዛ ማስጠቱን ወዘተ. ጆኒ ስሜቷ በስሜቱ እምነቷ በእምነቱ ተሠርጾ ሁለቱንም ለትዳር እንዲያበቃቸው በልቡ ለዚሁ ታቦት ተሳለ።

የወደቀው ብርጭቆ ተነስቶ ሌላ ቀረበ። ንጽሕናውን ጆኒ አገላብጦ ሳንሱር አደረገው። የአበሻ ቱሪስትነቱ ለውጪ ቀርቶ ለራሱ ተሰማው። የታጠበ ብርጭቆ መልሶ ያሳጥብ ጀመር። የቀረው እንጀራ በሹካ መብላት ብቻ ሆኖ እራሱን መልሶ ታዘበው። የባህል ቅይጥይጥ የባዕድ ጥራዝ ነጠቅ እውቀት እንዳበላሸው ያወቀው ሀገሩ ከገባ አሁን ነው። በንግግሩም መሐል አልፎ አልፎ የባዕድ ቃላቶች ስለሚያስገባ አሳፈረው። የውስጥ የተከፋ ስሜቱን በውሸት ፈገግታ ለስኖ እመቤት ቅር እንዳይላት አቅፎ ሳማት። ከእመቤት ጋር መለየቱ አስጠላው። ሁለቱም ባለፉት አስደሳች አጭር ጊዜ እረክተው በፍቅር ተቃቀፉ። ለሚቀጥለው ጊዜ እመቤት ከዓመት የሥራ ፍቃዷ የአንድ ሳምንት ጊዜ ወስዳ አብረው ለመሆን ተመካከሩ። እቤቷ አድርሷት ደረት ለደረት ተቃቅፈው በቀጠሮ ተለያዩ።

• • •

ሮዚ ወደ ጀርመን የሚመጣውን አይሮፕላን ላይ ተሳፈረች። ሆዷ ባብቶ ልቧ ተጨነቀ። አንደበቷ የጥንቱን የብዙነሽን ዘፈን በቀስታ አንጐራጐረ።

«ምንም ሳላስበው ውጥን ሳይኖረኝ
የሚያስለቅስ ፍቅር በድንገት ያዘኝ
እያንሰቀሰቀ የሚያስለቅሰኝ
ፍቅር እንደሆነ ጠቢብ ንገሩኝ
ለካስ ፍቅር ሰውን እንዲህ ያደርግ ኖሯል
በዚህ አስተያየት ብዙ ሰው ተጐድቷል»
አሜሪካ ሄጄ በርሬ ድንገት
እህቴን ልጠይቅ ሀገር ጉብኝት
ደረሰብኝ ሕመም የፍቅር ውጋት
ወደነበርኩበት ጀርመን ስመለስ
ሆዴ እየባባብኝ ጀመርኩኝ ማልቀስ

ብላ እየዘፈነች ወደ ብሬመን ተመለሰች።



ጆኒ ያለው ኢትዮጵያ ነው። የአንድ ወር ጊዜውን ጨርሶ ለሁለተኛ ወሩ ኢሚግሬሽን ሄዶ የሚከፈለውን ከፍሎ ቪዛውን አስጨምሯል። በእለቱ የሬዲዮ ፋና «ከጥበባት ዓለም በሚል ፕሮግራም ከአሁን በፊት ስለጻፈው «የተዋናይ መስተዋት» ቃለመጠየቅ ለመስጠት ተጋብዟል። የተባለው መጽሐፍ የትምህርት ቢሆንም በሕትመቱ በኩል መንግሥት አረዳውም። በግል ገንዘቡ አሳትሞ ለሕዝብ በማቅረቡ ደስታውን ገልጿል። ስለ ጀርመን አርቲስቶችም ተጠይቆ አንዳንድ ጠቃሚ ነገሮችን አውግቷል።

የናፈቀው የእመቤት ቀጠሮ ደርሶ ተገናኙ። አብረው ሆነው የኢትዮጵያን ታሪካዊ ቦታዎች ተዘዋውረው ለመጐብኘት በጣና የጉዞ ወኪል ድርጅት ተመዝግበው ተንሸራሸሩ። በጐንደር የአፄ ፋሲልን ግንብን የባህር ዳርን ከተማንና የጣና ሐይቅን፣ በጐጃም የአባይ ፏፏቴን፣ በትግሬ የአክሱምን ሐውልትና የላሊበላን ታሪካዊ ቤተመቅደስ ተመለከቱ። አዋሳና ላንጋኖም ሄደው የፍቅራቸውን መሠረት ፍትወት እስከሚጠግቡ ተወጥተው በሰላም ከነበሩበት የጥንቷ ፊንፊኔ አዲስ አበባ ተመለሱ።

«የኢትዮጵያ የቱሪስት ድርጅት እነዚህን የመሰሉ ታሪካዊ ቦታዎች የዱር አራዊትና አዋፋቶች፣ ወንዝና ጅረቶች በፊልም ቀርጾ ለዓለም ገበያ በበቂ ሁኔታ ቢያቀርብ በርግጥ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ስብራት አንድ ወጌሻ እንዳገኘ ይቆጠር ነበር» ብሎ ጆኒ አሰበ።

ጆኒ የእረፍት ጊዜው አልቆ መነመነ። በመሄጃው ሳምንት አካባቢ የሮዚን ቤተሰቦች ሄዶ ተዋወቀ። እንደ ሥጋ ዘመድ ተቀብለው አስተናገዱት። ጀርመን ለምትገኘውም ልጃቸው ሮዚ የሚያምራትን ሁሉ በስልክ ጠይቀው፣ በደንብ ሰንቀውና አዘጋጅተው ሰጡት።

የእመቤትን ቤተሰቦች ቢተዋወቅም እንደ ሀገሩ ባህልና ደንብ «ልጅዎን ይዳሩልኝ» ብሎ ሽማግሌ አላከም። ከድሮ ባለቤቱ ገና ስላልተፋታ በጋብቻ ላይ ጋብቻ መፈጸም አልቻሉም። ከጠበቃ ጋር ተመካክሮ ባለቤቱ እንደጠፋች በጋዜጣ አውጥቶ ሌላም ሽማግሌዎች ጨምሮ አስመሰከረ። ነገሩ እስከሚያልቅ እመቤት ጀርመን ት/ቤት ገብታ እንድትማር ሆነ።

ጆኒ በጠዋት ተነስቶ አጐቱ ቤት በረንዳ ላይ ሆኖ ተንጠራራ። የሀገር ፍቅር አምሮቱን ባይጨርስም ዛሬ ወደጀርመን የሚመለስበት እለት ነው። ልቡ ተጨነቀ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ያገኛቸው ጥቂት ደስታዎች በትዝታ መሐደር ተቋጠሩ። የደሙ ምንጭ የእንብርቱ አዋይ ለሆነችው ምድር እናት ኢትዮጵያን «እማዬ ደህና ዋይ» ብሎ ዓይኖቹ እንባ እያቀረሩ ተሰናበተ።

ዘመድና አዝማድ ጓደኛና ጐረቤት ሊሸኙት ተሰበሰቡ። ቅመሙ ተደቁሶ በርበሬው ተፈጭቶ ሽሮው ተቋጥሮ ቋንጣና ድርቆሹ በደንብ ተዘጋጅቶ ትኩስ እንጀራና ዶሮወጥ አንድ ላይ ሆኖ ተሰጠው። ከመቤትም የሆነ ስጦታ ተቀብሎ ለቧም ሰጣት። ፍቅራቸውን ጀምረው ገና ሳይጠግቡት ተለያዩ። ተቃቅፈው በመሳሳም ተላቀሱ።

ጆኒ ይህችን ከመሰለች ፍቅረኛውና ከውድ እናት ሀገሩ መለየቱ ሆዱን አባባው። የሀዘን እንባ እያነባ እስከ ቦሌ የአየር ጣቢያ ድረስ እንደታቦት በአጀብ ተሸኘ።

አይሮፕላኑ ላይ ወጥቶ የመጨረሻ ስንብቱን ሁለት እጆቹን እንደምርኮኛ ወደላይ ዘርግቶ በማወዛወዝ ገለጠ። ሞተሩ ሞቆ የጋለው አይሮፕላን መሬትን ለቆ ወደ ላይ አቆበቆበ። የአዲስ አበባን የማይጠገብ አየር ወደኋላ እየገፈተረ ሽቅብ በሮ ከነፈ።

የጆኒ ጉዞ በጭለማ ነበር። አንገቱን ዘንበል አድርጐ በመስኮት በኩል ውድ ሀገሩን ተመለከተ። የሰማይ ኳክብቶች የመሰሉ ማብራቶች ለዓይን ብልጭ ድርግም እያሉ እያነሱና እየራሱ ተሰወሩት። ፊቱን አዙሮ ወንበሩን ወደኋላ ለጠጥ አድርጐ እንባ ያቀረዙትን ዓይኖቹን ጨምቆ አነባቸው። የትካዜ እንጉርጉሮ ሳያስበው ከላንቃው ወጣ።

«እትቱ በረደኝ ብርድ ይበርዳል ወይ
የማያውቁት ሀገር ይናፍቃል ወይ።
ኢትዮጵያን ጥዬ በአየር ስበር
ልቤ ተጨንቀ ቅር ይለኝ ጀመር።
የእመቤት ፍቅር የሀገሬ ትዝታ
በሀሳቤ እየመጣ አልሰጥ አለኝ ፋታ።
ከእረፍት ሲመለሱ የስሜት ቅሬታ
መዝናናቴ ቀርቶ አጣሁኝ ደስታ
ምን ይሁን መድሀኑ የጭንቀት በሽታ
ንገሩኝ እባካችሁ እንዳገኝ እርካታ።
እትቱ በረደኝ አንቀጠቀጠኝ አሰኘኝ ዋይ ዋይ!

ፍቅር ከሞላበት ከሀገሬ ስለይ።» ብሎ ተከዞና አልቅሶ ፍቅር ከጐደለው ሀብት ከተረፈው ከሚኖርበት ብሬመን ከተማ ጀርመን ሀገር ተመልሶ ገባ።





# ክፍል አሥራ ስምንት

«የድንቁርና ሌት ጨለማ አለፈ
የማስተዋል ንጋት ብርሃን ተነጠፈ።
ደመናውን ቀዶ ማስተዋል ፈለቀ
ትምህርት ተፋፋመ ተስፋፋ ደመቀ።»
ከበደ ሚካኤል

ሮዚ በጠዋት ተነስታ የብሬመንን ዩኒቨርስቲ ትልቅ ቅስት በር አልፋ እካንፓሱ ገባች። አለባበሷና የፀጉር አሠራርዋ እንደውትሮ ሽክ ያለ አይ ደለም። ጂንስ ሱሪና ከውስጥ ነጭ ሸሚዝ ከላይ ተለቅ ያለ ኮት ለብሳ ለች። ትክ ብለው ሲያይዋት ዩኒቨርስቲ ውስጥ ብዙ ጊዜ የቆየች ተማሪ እንጂ ፍጹም አዲስ የመጣች የታክሲ ሹፌር አትመስልም።

ሮዚ ያላት ከፍተኛ የትምህርት ፍላጐቷ ለምልሞ ጠይም ፊቷን አፍግጐታል። ልቧ በእንግድነቷ ፍራቻ ቢረበሽም እግሮቿ አልተብ ረከረኩም። ቀጥ ብላ ብዙ ደረጃዎችን ወደላይ ወጥታ ዩኒቨርስቲው አስተዳደር ቢሮ ገባች።

የአስተዳደሩ ኃላፊ ገና ሲያይዋት ፈገግታዋን ከእሷ እንደሰረቁ ሰው ደንገጥ ብለው ሽጋ ጥርሳቸውን ብልጭ አድርገው አሳይዋት። በቀጠሮዋም ቀን በመምጣቷ አመስግነው ወደ ሕግ ፋኩሊቲ የሚያስገባትን የፍቃድ ወረቀት ጽፈው በመስጠትና «በርቺ» በሚል አበርቺ ቃል መርቀው በፈገግታ ሸኟት።

የሕጉ ፋኩሊቲ ትልቅ ሕንፃ ከሌሎች ብዙ ሕንፃዎች ትንሽ ፈንጠር ብሎ ተሠርቶ የራሱ ግቢ አለው። ገና ሲገቡ በስተቀኝ በኩል ባለው ሰፊ ወለል ላይ ትልቅ ሐውልት ቆሟል። ዓይኖቿ የተሸበበ በቀኝ እጇ ሰይፍ በግራ እጇ ሚዛን የያዘች የሴት ምስል ቅርፅ ነው። ትርጉሙም ለትክክለኛ ዳኝነትና ፍርድ መታሰቢያ እንዲሆን ተብሎ የተሠራ ነው።

ይህን አልፈው ሰፊው አዳራሽ ውስጥ የሚገቡት ተማሪዎች አብዛኛዎቹ እንደሮዚ እንግዳ ተማሪዎች ናቸው። የመደናገጥና የመደናገር መልክ ይታይባቸዋል። የእርስ በርስ ሰላምታቸው የተቆጠበ

ሆኖ የሥፍራውን ትክክለኛነት ቢያውቁም ለማረጋገጥ እየተጠያየቁ ገብተው ሥፍራ ስፍራቸውን ይዘው ተቀመጡ።

ሮዚ ያለችው ከመጀመሪያው አምስተኛ እረድፍ ከፕሮፌሰሩ መድረክ 5 ሜትር ይርቃል። አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ጀርመኖች ሲሆኑ ከአፍሪካና ከሌላም ሀገር የመጡ አልፎ አልፎ አሉበት። የሴቶቹ ቁጥር ከወንዶቹ በጣም ጥቂት ነው።

የመጀመሪያው ሴሚስተር በፕሮፌሰሩ የጠራ የመተዋወቂያ ንግግር ተከፍቶ አጠቃላይ የትምህርት ዝርዝር፣

1ኛ. የሕግ አመሠራረትና አመጣጥ ታሪክ

2ኛ. ስለ ሕግ አወጣጥና አፈጻጸም

3ኛ. ስለ ሕዝብ መብትና ግዴታ

4ኛ. ስለ ሕገ መንግሥት አወቃቀር

5ኛ. ስለ ወንጀል ቅጣትና ፍትሀብሔር እንደሚሆን ተነገራቸው። ይህንኑ በመወያየት በመጠያየቅና እርስ በእርሳቸውም በመተዋወቅ የእለቱ ትምህርት ተፈጽሞ ጀንበር ሳትጠልቅ ጊዜው ተገባዶ ተበተኑ።

ሮዚ የሕግ ትምህርቷን ከጀመረች ሳምንት አልፏታል። ትምህርቱን ብትወደውም ከብዷታል። አዕምሮዋ አልሰበሰብ እያለ ልቧ የአሜሪካኑን አሮን አፍቅሮ አስቸግሯታል። የምግብ ፍላጐቷ ተዘግቶ ሰውነቷ ከስቷል። ለሊቱን በደንብ ሳተኛ አድራ በጠዋት የመነሳቱ ጉዳይ አልሆንላትም። በሳምንት አራት ቀኖች ማልዶ መነሳቱ ከትምህርቱ በልጦ ተራራ አክሎባታል። የታክሲውንም የለሊት ሥራ አልተወችም። በሳምንት ሦስት ቀኖች ትሠራለች።

ሮዚና ጆኒ ለእረፍት ከሄዱበት ቦታ ተመልሰው መጥተው ያመጡትን ስጦታና ስንቅ ተለዋውጠዋል። ግን ስለሁኔታው ጊዜ አግኝተው አልተወያዩም። እሷም በትምህርት ውጥረት እሱም በሥራ ድክመት ይባዝናሉ። ዛሬ ግን ሁለቱም የለሊት የታክሲ ሥራ ስላለባቸው እርስ በርስ ተገናኝተው ለመጨዋወት ተቀጣጥረዋል።

ፋጡማና ክላውዝ ፍቅራቸው ጠንቶ የዓመት የእረፍት ፍቃድ ወስደው ወደሆነ ሀገር ኮብልለዋል። ሙራትና ከድር በሮዚ ላይ ያላቸው የሸር ገመዳቸው አሁንም አልተፈታም። ብቻ በዘዴ ቀርበው የውሸት ፈገግታ በማሳየት ሊታረቋት ተመካክረው ወስነዋል።



እንድሪያስ አንዲት ከበርሊን የመጣች ቆንጆዩ ወዶ በፍቅሯ ጦፏል። የአሁኑ ፍቅረኛው እንዲህ የዋዛ ሰው አይደለችም። እንደሌሎቹ አንሶላ ቅብጢርሴ ብቻ አላስለወጠችውም። «ከተፋቀርን እኔ ያለሁበት ቦታ መኖር አለብህ» ብላው ጓዙን ጠቅሎ፣ የታክሲ ሥራውን ትቶ ከብሬመን ለቆ የጀርመን ዋና ከተማ በርሊን ገብቷል።

የምሽቱ አየር አይበርድም። የሰዓት አቆጣጠሩ ግን ተለውጧል። አንድ ሰዓት ወደኋላ ተቀንሶ ስለዞረ ወቅቱ ጭለማ ገና አልወረረውም። በአውሮፓ በየዓመቱ አንድ ሰዓት ወደፊት ወይም ወደኋላ የማድረግ ደንብ አለ። የወሩ መጨረሻ አካባቢ የሳምንቱ ማክተሚያ ስለሆነ ምሽቱ ደመቅመቅ ብሏል።

ጆኒ ትንሽ አርጀት ያለችውን ታክሲ እያንኮራኮረ ወደከተማው እንብርት በረረ። የሆነ ቦታ መኪናውን አቁሞ ማዶ ተመለከተ። ድሮ የሚያውቀው ኢትዮጵያዊ ስደተኛ ከዘራ ይዞ እያነከሰ ሲሄድ አይቶ የተባለውን ሰው ጠርቶ መኪናውን ከፍቶ አስገባው። ስደተኛው ትክክለኛ ስም ቢኖረውም የሚጠራው «ጅመጋ ጠቅል» ተብሎ ነው። በእድሜው የገፋ ለብዙ ጊዜ ጀርመን ውስጥ የኖረ ነው። መሥራትም ሆነ መማርን ጨርሶ አይወድም። ለምን ሲሉት «የፈረንጅ ስሃን አላጥብም በትምህርትም የተፈጥሮ እውቀቴ በቂ ነው» የሚል አዕምሮ በባእድ ኑሮ ችግር የተለከፈ ወፈፌ ነው። ሁልጊዜ ካባ ከትከሻው አይወርድም። ለምን ሲሉት «የንጉሥ ዘር ነኝ» ብሎ ይኩራራል። ያዘነ ገንዘብ ሲሰጠው «አህያ ለፍቶ ላንበሳ» ብሎ ይሳደባል። ሲቸግረውም ይለምናል። አንድ ቀን ጆኒን አግኝቶ ሳንቲም ቢጠይቀው «ካባህን አውልቀህ መኪናዬን ወልውልልኝ» ቢለው አኩርፎ ጥሎት ሄዷል። ብቻ ነገሩ የአሽሙር ቀልድ ስለሆነ አልተቀያየሙም።

ከብዙ ጊዜ በኋላ ዛሬ ተገናኝተው ሰላምታ ከተሰጣጡ በኋላ ጆኒ ጅሙጋን ይዞት በታክሲው ሄደ።

«ምን ሆንክ እግርህን ታነክሳለህ?»

«አረቦች ደብድበውኝ ነው።»

«እንዴት በምን ተገናኛችሁ።»

«በጉርብትና።»

«አልገባኝም እንዴት በጉርብትና?»

«ምናልባት የያዝከው ጠበቃ ሰነፍ ይሆናል እንጂ ነገሩ እስከዚህ ከባድ አይመስለኝም ከፈለግህ እኔ የማውቀው ጥሩ ጠበቃ አለ።»

«መልካም አድራሻውን ንገሪኝ እሞክራለሁ» አላት።

ሮዚ አድራሻውን ልትጽፍለት ብዕር ለመፈለግ መኪናው ፊት ለፊት ያለውን ትንሽ ሳጥን ስትከፍት ትልቅ የጋዝ ሽጉጥ ተጋድሞ አይታ ደነገጠች።

«ይሄ ደግሞ ምን ሊያደርግልህ ነው የያዝከው?»

«አንቺ የለሽም እንዴ? አብዛኛውን ታክሲ ነጂዎች ጩቤ ወይም የጋዝ ሽጉጥ አላቸው። አንቺ እንዴት የለሽም?»

«እኔ የለኝም እሱ ቅዱስ ገብርኤል ይጠብቀኛል።»

ሮዚ በእምነትሽ ጽናት አልከራከርም ግን እምነትሽ የሚረዳሽ አንቺም እራስሽን ለመጠበቅ ጥረት ስታደርጊ ነው። ጀርመኖች ለዚህ ነው ኡንፋል ኢዝት ካይን ሱፋል (Unfall ist kein Zufall ) የሚሉት። አደጋ የአጋጣሚ ክስተት አይደለም። አስፈላጊ ጥንቃቄ ካደረጉ ከአደጋ ማምለጥ ይቻላል ብለው የሚያምኑት» ብሎ ነገራት።

«አሁን ጆኒ መሳሪያ ስለያዝኩ ከመጣብኝ አደጋ ማምለጥ የምችል ይመስልሀል?»

«በርግጥ እንጂ መሣሪያ ያስፈልግሻል። እንኳን ሰው መልአክቶችም ቢሆኑ በሥዕል ላይ ስንመለከት ሰይፍ ወይንም ጦር ይዘው ነው። ቅድስ ሚካኤል ዳቢሎስን እረግጦ በሰይፉ ሲመታው፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ በፈረስ ተቀምጦ ዘንዶውን በጦር ሲወጋው ስእሉን አላየሽም?»

«ኢባክህ ይሄ የሰዓሊዎች ፋንታዚ እንጂ በርግጥ መልአክቶች የጦር መሣሪያ አያስፈልጋቸውም።»

«ያልሽው ሊሆን ይችላል። አንቺ ግን ሰው ነሽና መሣሪያ ያስፈልግሻል» ብሎ ከኪሱ ትንሽ አውቶማቲክ ሴንጢ አውጥቶ ሰጣት። ሮዚ ሴንጢውን ተቀብላ አገላብጣ አየችው። የሆነ ነገር ጫን ስትለው ስለቱ ተፈትልኮ ወጣ። በጣም የሰላና የሾለ ሴንጢ በመሆኑ ሰውነቷ ሰቅጥጥ አለ። መልሳ ዘግታ ያዘችው።

«አየሽ እሮዚ አንዳንድ ጥቁርን የሚጠሉ ዘረኛ የጀርመን ተሳፋሪዎች ሊያጋጥሙሽ ስለሚችሉ አትሊስት ለራስሽ መከላከያ ይጠቅምሻልና ውሰጂው» ብሎ ሸለማት። ሮዚም ስጦታውን አመስግና ተቀብላ ቦርሳዋ ከተተችው።



ወዲያው በፉንክ የታክሲ አገልግሎት በር ደርሷት ወደተባለው ቦታ መኪናዋን አስነስታ ተፈተለከች። ጆኒ ካለበት ቦታ መኪናውን እያንፏቀቀ የመጀመሪያውን ቦታ ያዘ።

ሰዓቱ እረፍዶ ለሊቱ ተገባዶ ሰማዩ እየወገገ ሄዶ ወፎች ተንጫጩ። የለሊት የፈረቃ የታክሲ ሹፌሮች ሥራቸውን ጨርሰው ወደባዝል ተኮለኮሉ።

ሮዚ ከአሜሪካ ከተመለሰች ሁለት ወር አለፈ። የሕግ ትምህርቷን እየተከታተለች በጠዋት መነሳቱንም እየተላመደች ሄደች። ግን አሁንም ትምህርቱ ከብዷታል። በእረፍት ጊዜዋ ታክሲ ስለምትነዳ ለማጥናት በቂ ጊዜ አላገኘችም። በዛ ላይ የአሮን ፍቅር አለቀቃትም። እለት በለት ስልክ ይደዋወላሉ፤ ደብዳቤ ይለዋወጣሉ። እንዳውም አላስችል ብሏት ተዘዋዋሪ ስልክ (ሀንዲ) ገዝታለች። እዳው ቢበዛም ብቸኝነቷን በዚሁ መገናኛ ሸፍና የሩቅ ለሩቅ ፍቅሯ እንዳይቀዘቅዝ ትጥራለች። የጠራ ጥሩ ድምፅ ባይኖራትም ብቻዋን አልጋዋ ላይ ሆና ሀገሯንና ቤተሰቦቿን አሜሪካ ያለውንም ፍቅረኛዋን እያስታወሰች እንዲህ እያለች ታንጎራጉራለች።

ከጥልቅ ሸለቆ ዳርቻ...
ተጋድሜ እኔው ለብቻ
የሀገር ናፍቆት ይዞኝ
ያደግሁበት መንደር ናፍቆኝ
ቢለቀኝ ብዬ እዘፍናለሁ
ተክዤና አዝኜ እያነባሁ።

ከጥልቅ ሸለቆ ዳርቻ...

ነበርኩኝ እኔ ለቤተሰቦቼ ጨረቃ
የፍቅር ጥንስስ ተወዳጅ የቤቱ አለቃ
ዘፈንና ቀልዱን የሀገሬን ጨዋታ
ልዩ ልዩ ምግቦች ሲቀርቡ በገበታ
አልማለሁ ሁል ጊዜ ሆኖብኝ የሰቀቀን ትዝታ።

ከጥልቅ ሸለቆ ዳርቻ...

እርቄ ሄጄ ከውድ ሀገሬ

ጥቁሮችን ማየት ለምዷል። ግን በታክሲ አገልግሎት ሥራ የጥቁር ሹፌር ስላላዩ ሥራውን በጀመርኩ ጊዜ መንጃ ፍቃድ አለህ?። እኔ በጥቁር ሹፌር አልሄድም እያሉ ይመልሱኝ ነበር። ሁኔታውን ችዬ በሥራዬ ብፀናም አንዳንዶቹ ቢንቦ ኩንታ ኪንቴ እያሉ መሳደብ ጀመሩ። በዚህም ጠብ ፈጥሬ ከብዙ ሰዎች ጋር ተጣላሁ። ሲውል ሲያድር ሁኔታውን ሕዝቡ ተለማምዶ በፉንክ የሚያስጠሩኝን ብዙ ወዳጅና ደንበኛ ለማፍራት ቻልኩ» አለው።

ጆኒ «ከአሠሪህና ከሌላም የሥራ ባልደረቦችህ በቆዳህ ቀለም የደረሰብህስ ምን አለ?»

«እንደምታውቀው በዚህ ድርጅት ውስጥ የተለያዩ ዜጎች ቢኖሩም ቆዳቸው እንደ ጀርመኖች ቀይ ነው። እኛን ጥቁሮች ደደቦች በማለት ይንቁናል። መኪናዬ እንኳን የሆነ ቦታ ተበላሽቶ እርዳታ በፉንክ ስጠይቅ በቶሎ የሚመጣልኝ አልነበረም። ቱርኩ ለቱርኩ፣ ኢራኑ ለኢራኑ፣ ጀርመኑ ለጀርመኑ ወዘተ. በመሆኑ ሁሉን ታዝቤ ኖሬአለሁ። የፉንክ ተናጋሪዎችም ያዳላሉ። የድርጅቱ ኃላፊ አቶ ሀሮልድም ቢሆኑ በጥቁሮች ላይ እምነት የላቸውም። አዳዲስ መኪናዎችና S-ክላስ ታክሲዎችን እስካሁን ለአንዳችም ጥቁር አስነክተው አያውቁም።»

«በቀለምህ ሳይሆን በሥራህ እለታዊ ገጠሞች ያለህ ትዝታ ምንድነው?»

«አንድ ጊዜ በፉንክ አንዲት በሽተኛ ከወደቀችበት ወለል አንስቼ አልጋ ላይ ደግፌ እንዳስተኛ በር ደረሰኝ።» ብሬመን ውስጥ አርባይት ሴሜተር የሚባል የበሽተኞች ማገገሚያ ድርጅት አለ። በሽተኞች ችግር ሲገጥማቸው ለድርጅቱ በሚጫኑት ጥሪ ያስታውቃሉ። ድርጅቱ ለታክሲ ሴንተራል ደውሎ የሆነ ሹፌር ሲመጣ አድራሻና ቁልፍ ተሰጥቶት እርዳታ ያደርጋል። አልበርት ይሄው አገልግሎት ደርሶት በሩን ከፍቶ ሲገባ የወደቀችው በሽተኛ በጣም ወፍራም ስለነበረች እሷን ለማንሳት ያደረገውን ትግል ነበር ለጆኒ ያጫወተው። በነገሩ ሁለቱም ተሳስቀው ሥራ ጀመሩ።

ሮዚ ከአሜሪካ ተመልሳ እንደመጣች ሰሞን የሮላንድ የታክሲ ድርጅት ባለቤት የሆኑት አቶ ሀሮልድ «በመሥሪያ ቤቴ የተቀያየሙ ሠራተኞች እንዲኖሩ አልፈልግም» ብለው ሮዚንና ሙራትን አስታርቀዋቸዋል። የውስጣቸውን እንጃ እንጂ እላይ ላዩን በፈገግታ



የሩቅ ሰላምታ እየተለዋወጡ መቀራረብ ጀምረዋል። ሮዚ አታርገው እንጂ ሙራት አልፎ አልፎ ሮዚ መኪና ውስጥ እየገባ መጫዋወት ጀምሯል። ሁኔታው ሮዚን ቢከፋትም አቶ ሀሮልድን ላለማስቀየም ስትል ሁሉን ችለዋለች።

ይሄው ነገር እየተለመደ ሄዶ እለት በእለት ግንኙነታቸው መልሶ ተጠናከረ። አብረው እራት መብላት ቡና መጠጣትም ጀመሩ። ሙራት ለሮዚ ያለው ፍቅር መልሶ ለመለመ። ከክላውዝ ጋር መጣላቷን ወዶ ብቸኝነት እንዳይሰማት «አለሁልሽ» በሚል የሞኝ ተስፋ እያጽናና ምኞቱን በቅዠት ሕልም ተወጣ።

ሮዚ እንዲህ በቀላሉ የምትፈታ የዋዛ ሰው አይደለችም። ባለፈው ጊዜ የደረሰባት የመኪና አደጋ በዚሁ ሰውና በከድር የሸር ወጥመድ መሆኑን ጠርጥራለች። ግን ቂጭቷንና በቀሏን ለመወጣት ጥሩ ዘዴና አጋጣሚ መርጣ የዲፕሎማሲ ፈገግታዋን የእለት በለት ጭውውቷን እስካሁን አልነፈገችውም።

ሁሉም የለሊቱን የታክሲ ሥራ ጨርሰው ወደየቤታቸው ሄዱ። ጆኒ እቤቱ እንደገባ የመጽሐፉ እትመት ሥራ እምን እንደደረሰ ለማወቅ ፈልጎ አዲስ አበባ ላለው ወዳጁና የመጽሐፉ እትመት ወኪል ለአቶ ደበበ ስልክ ደወለ።

«ሃሎ አቶ ደበበ፣ እኔ ነኝ ዮሐንስ ከጀርመን።»

«ጤና ይስጥልኝ ጋሼ ዮሐንስ እንደምን አለህ?»

«ደህና ነኝ አናንተስ?»

«እኛማ እንዳለን አለን።»

«ሥራህን ቋሚ አደረጉልህ?»

«ገና ነው እስካሁን ማገር ነኝ።»

«ምን ማለትህ ነው አልገባኝም?»

«ማገር በቋሚዎች መሐከል የሚተላለፍ ልጥ ነዋ!»

«አንተ ባለድግሪ አይደለህም እንዴ? እንዴት የልጥ ማገር ያረጉሃል?»

«አዬ ጋሼ ዮሐንስ በአሁኑ ጊዜ የሚፈለገው ድግሪ ሳይሆን ጉሳ ነው።»

«ታዲያ ከነሱ ዘርና ጉሳ ጋር መጋባት ነዋ!»

«እኔስ ባለትዳር ነኝ፤ ባልሆንም አላደርገውም፤ የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል። የነሱ ዝምድና ባፍንጫዬ ይውጣ!»

«እውነትክን ነው፤ ጉመን በጤና ይሻላል። አሁን የደወልኩልህ የመጽሐፌ ጉዳይ እምን እንደ ደረሰ ለማወቅ ፈልጌ ነው።»

«አዬ ጋሼ ዮሐንስ የላከው ገንዘብ በቂ አልሆነም።»

«እንዴት?»

«የወረቀት ውድነት የአንባቢ እጥረት እትመቱን አስወድዶት ገንዘብ ካልተጨመረ ብለው ሥራውን አልጀመሩትም።»

«የወረቀት መወደድስ ይሁን የአንባቢን እጥረት ምን አመጣው?»

«እባክህ ሕዝቡ እንደበፊቱ አይምሰልህ አንድ መጽሐፍ በአሥር ብር ከመግዛት ይልቅ ቢጠጣበት ወይም ክትፎ ቢበላበት ይመርጣል።»

«ለምን እባክህ?»

«እኔ እንጃ ምናልባት በአሁኑ ጊዜ የሚጻፉት መጽሐፍቶች አላረካው ይሆናል ማን ያውቃል።»

«ጥሩ ደራሲያኖች የሉም ማለትህ ነው?»

«እሱማ አሉ በምን ጉናቸው ያሳትሙት።»

«ሕዝቡስ የመንፈስ ጥሙን በምን ይወጣል?»

«በጋዜጣ በመጽሔትና አልፎ አልፎ በውጪ ድርሰቶች።»

«ሰላምና እርጋታ በሌለበት ኅብረተሰብ ያለ ጉዳይ ነውና በሕዝቡ አልፈርድም ያልከውን ተጨማሪ ገንዘብ በቅርቡ እልካለሁ። ድሮ መጽሐፉን ስጽፍ ለጥቅም ስላልሆነ አይቆጨኝም። መጽሐፉ ከታተመ በተቻለ መጠን በቀላል ዋጋ ለሕዝብ እንዲደርስ ይሁን።»

«እንዲህማ ከሆን መክሰርህ ነው።»

«ልክሠር። በገንዘብ ብጐዳም ድርሰቴ ደካማም ሆነ ብርቱ ሕዝቡ አንብቦ ትችቱና ምስጋናው ሲደርሰኝ መንፈሴን ያበለጽገዋል።» ብሎ ጆኒ ስልኩን ዘጋው።

ሮዚ እቤት እንደገባች ከአሮን ጋር በስልክ ተጫዋውታ መኝታዋ ውስጥ ከገባች ቆይቷል። ግን እንቅልፍ አሊዝ ብሎ ያወራጫታል። አልፎ አልፎ ትንሽ ሽለብ ሲያደርጋት የምታየው ሕልምና ቅዠት እያስደነገጣት ከመኝታዋ ደንግጣ ትባንናለች። ብቸኝነቷ ይሁን



የቤተሰቦቿ ናፍቆት የአሮንም ፍቅር ተጨማምሮ መንፈሷ ሰላም አጣ። የሞቀ አልጋዋ በረዳት። ሰውነቷን ቀፈፋት «አምላኬ የዘመዶቼን ክፉ ነገር አታሰማኝ» ብላ የሕሊና ጸሎት አደረገች። ሮዚ እንዲህ ያለ ስሜት ሲሰማት የሆን መጥፎ አጋጣሚ ስለሚደርስባት ሁኔታውን በጸሎት ለመለወጥ ከመኝታዋ ተነስታ መጽሐፍ ቅዱስ በእቅፏ ይዛ ግንባሯን አስንክታ ተንበርክካ ጸለየች። ሁኔታው አላስችል ብሏት ኢትዮጵያ ስልክ ደውላ የዘመዶቿን ደህና መሆን አረጋግጣ ደስ ብሏት ተመልሳ ተኛች።

ሙራት ባለቤቱንና ልጆቹን እቱርክ ሀገር ካዛወረ ወዲህ ብቸኝነቱን ስለሚጠላ አልፎ አልፎ ሥራ ሲጨርስ በቀጥታ ቤቱ አይገባም። የሆነ እቁባቶቹ ጋ ደርሶ የወሲብ ጥማቱን ጨርሶ ወይም የቱርኮች የቁማር መደብር ሄዶ ትንሽ ካርታ ተጫውቶ ነበር የሚያረፍደው። ሰሞኑን ከሮዚ ጋር ያለው ግንኙነት ስለሰመረ ሁሉን እርግፍ አርጐ ትቶ እሷን ተመኝቶ እያለመ መተኛቱን መርጦ በጊዜ ገብቶ ተኝቷል። ነጭ አረቄ በውሃ ደባልቆ መጠጣቱንም ካቆመ ቆይቷል። ያም በመሆኑ ዘወትር የሰላም እንቅልፍ ይተኛል። ግን ዛሬ እሱም እንደሮዚ እንቅልፍ እንቢ ብሎት የውን ቅዠት እየቃዠ ሲገላበጥ አደረ።

ጆኒ ድርሰቱን ከጨረሰ ወዲህ ሲተኛ የደረቀ ነጭ ወይን ጠጅ ከሶዳ ውሃ ጋር እየደባለቀ ስለሚጠጣ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወስዶት እረፋዱ ላይ ነቅቶ ተነሳ። ያለውን ቀማምሶ እባንክ ሄዶ ለመጽሐፍቱ እትመት የሚሆነውን ተጨማሪ ገንዘብ አውጥቶ ኢትዮጵያ ላከ።

ጊዜው ቢመሽም የበጋዋ ፀሐይ አልጠልቅ ብላ ትቁለጨለጫለች። በደንብ የተኛም ሆነ ያልተኛው የእለት ኑሮውን የሕይወት ግዴታውን ለማከናወን በሥራ ተሰማርተዋል። የሮላንድ ታክሲ ሹፌሮች መኪናቸውን ይዘው በከተማ ተሰራጭተዋል።

እለቱ የወር አጋማሽ በመሆኑ የእለቱ የታክሲ ገበያ እስከዚህም አልደራ። ሮዚ በቅጡ ባትተኛም በእለቱ ሥራ ገብታለች። ሰውነቱ ግን እንደወትሮ የደስታ ስሜት አላገኘም። ቢሆንም የሀገሯን ሙዚቃ ከፍታ ስሜቷን በዘፈን አባብላ ያዘችው። ጊዜው ሮጦ ለሊቱ ተገባደደ። ሮዚ ስለራባት ከጆኒ ጋር እራት ለመብላት ፈልጋ በፉንክ ጥሪ ልታገኘው ባለመቻሏ ብቻዋን ኪስሜት ምግብ ቤት ገባች። ምግብ አዛ ስትበላ ሙራት ተከትሎ ገብቶ አጠገቧ ተቀመጠ። ሁለቱም አብረው እያወሩ እራታቸውን በልተው ጨረሱ።

ሮዚ እራት ስትበላ መኪናዋን ያቆመችው ሽታይንቶር ከፈርፌልድ የታክሲዎች ማቆሚያ አካባቢ የሆነ ሰዋራ ስፍራ ነበር። መኪናዋን ከፍታ ስትገባ ሙራትም ተከትሏት አብሮ ከእሷ ጋር ቁጭ አለ። ተራቸውን ለመጠበቅ የመጨረሻው ቦታ ለማግኘት እዛው ኮርነሩ ሥፍራ ቆዩ። አብረው እያወጉ ወሬአቸው ደርቶ መሳሳቅ ጀመሩ። ወዲያው የሆነ ነገር ተፈጥሮ ሙራት ከመኪና ውስጥ እየጮኸ እሪታውን ለቀቀው። ተራ የሚጠብቁት ሹፌሮች አንድ ላይ ተሰብስበው ሁኔታውን ተመለከቱ። ሙራት ሰውነቱ በደም ተለውሶ እንደታረደ በሬ ያጓራል። ሮዚ ያዙኝ ልቀቁኝ እያለች ትሳደባለች፣ ትጮሀለች። አንቡላንስና የፖሊስ መኪናዎች ደርሰው ሮዚንና ሙራትን ይዘው ሆስፒታል ሄዱ።

ሮዚ ሙራትን በሴንጢ ወግታ በአካሉ ላይ ከፍተኛ የማቁሰል ጉዳት በማድረሷ ተከሳ ለምርመራ እሥር ቤት እንድትቆይ ተደረገ።

ጆኒ የሮዚን መታሠር ሰምቶ በመደንገጥ እቤቱ ሳይገባ እዛው እጣቢያ ቁጭ ብሎ አደረ። የጠቡን ሁኔታ የሚነግረው አጥቶ ተጨነቀ። ሮዚን የግድ ማግኘት አለብኝ ብሎ ፖሊሶችን ቢጨቀጭቅ እንቢ ብለው ከጣቢያ ገፍትረው አስወጡት።

በማግስቱ የሕግ ጠበቃውን አነጋግሮ በሮዚና በሙራት መካከል ያለውን ጠብና ወንጀል አጣርቶ እንዲያሰማውና በተለይ ለሮዚ ጥብቅና እንዲቆምላት ውክልናውን ፈርሞ ሰጠው። የነገሩ ሁኔታ እንዲህ ነው።

ሙራት እሮዚ መኪና ውስጥ እንዳለ ድንገት ብልጭ ብሎበት ሰውነቷን ጨምቆ እላይዋ ላይ ጉብ ይላል። ጭኖቿን በርግዶ በግድ የወሲብ ግንኙነት ለማድረግ ይታገላል። እሮዚ እንደምንም ተፍጨርጭራ ከእቅፉ ትወጣለች። እጆቿ እንደምንም ታግለው ቦርሳዋን ጨበጡ። ጆኒ የሰጣትን አውቶማቲክ ሴንጢ ላጥ አርጋ አውጥታ ብልቱን በመጠኑ ትሸረክተዋለች። ሙራት በዚሁ ሁኔታ በአካሉ ላይ ከፍተኛ የመቁሰል አደጋ ደርሶበት ሆስፒታል ስቴንሲፍ ስታሲዎን ተኝቷል።

ጆኒ ይሄን ወሬ ሰምቶ «ደግ አደረገች የኔ ባትሆን ይቆጨኝ ነበር ለእንደዚህ ያለ ስድ ባለጌ ሲያንሰው ነው። አንገቱን ቆርጣ መጣል ነበረባት» ብሎ ጭፍን ውሳኔውን በእልህ ተናግሮ ፎከረ። ሮዚ በመታሠሯ ግን ቅር ብሎት አዘነ።

የትላንቱ የሮዚና የሙራት ጠብ በጋዜጣ በይፋ ወጥቶ ብዙ ሕዝብ አነበበው። ትንሹ ወሬ ተጋኖ እየተስፋፋ ከተማውን አልፎ በየመንደሩ



ተወራ። በተለይ ጀርመኖች በጉዳዩ እስከዚህም አልተገረሙም። የተጣሉት ሁለት የውጪ ሀገር ዜጎች በመሆናቸው «አህያ ላህያ ቢራገጥ...የራሳቸው ጉዳይ» በሚል ችላ ብለውታል።

የብሬመን የታክሲ ሹፌሮች ግን ጠቡን ልዩ ልዩ መልክ በመስጠት ያናፍሳሉ። የጥቁር ጥላቻ ያለባቸው ሮዚን ሲረግሙ ሌሎች ሙራትን «ምን አቅብጦት ደፈራት» ይላሉ። ግን ሁሉም በሙራት የብልት መቁሰል ሱሪውን አውልቆ ባይዳፈራት ልታገኘው አትችልም·በሚል በእለቱ የተደረገው ወንጀል አስገድዶ ሴትን ለወሲብ መድፈር መሆኑን አውቀውታል።

ይህ በንዲህ እንዳለ ሁለት ወር አለፈ። ጆኒ በጠበቃው አማካይነት ሮዚን ደጋግሞ እሥር ቤት ጉብኝቷታል። ሮዚ ወሬው ለቤተሰቦቿ እንዳይሰማ ጆኒን አደራ ብላ የሚደርሳትን ልዩ ልዩ ደብዳቤዎች እንዲቀበልላት የቤቷን ቁልፍ ሰጠችው። እሱም የሚያምራትን ምግብ እያዘጋጀ ደብዳቤውንም ጭምር ለፖሊስ አስመርምሮ በፍቃድ ማስተላለፍ ጀመረ።

ወንጀሉ በዳኞች ታይቶ ጥፋተኛው ማን መሆኑ ገና አልተረጋገጠም። ሙራት በደረሰበት ጉዳት ሆስፒታል በመተኛቱ አገግሞ እስከሚወጣ ድረስ አራት ወር ፈጀ። ሮዚ በዚሁ ቀጠሮ ያለአንዳች ፍርድ በምርመራ እሥር ቤት ቆየች።

የብሬመን የኢትዮጵያ የስደተኞች መሐበር በጉዳዩ ተመካክሮ ሌላ ምርጥ የሆነ ጠበቃ እንዲቆምላት አደረገ።

በፈረንሳይ የሚካሄደው የ98 የአለም የእግር ኳስ ዋንጫ ውድድር የታክሲ የምሽት ገበያውን ሰሞኑን አቀዝቅዞት ሰንብቷል።

በዚህ ሳምንት ግን የጀርመን ካንስለር አስተዳዳር ፓርቲ (CDU-Christlisch Demokratisch Union) የሦስት ቀን ስብሰባ ብሬመን ከተማ ውስጥ ስለሚያደርግ ምሽቱ ሞቅ ሞቅ ብሎ የታክሲዎች ገበያ ደርቷል።

ጆኒ በሮዚ መታሠር ቢያዝንም የለሊት የታክሲ ሥራውን አልተወም። ከወዲያ ወዲህ እያለ ሲዘዋወር አንድ በአለባበሱ ያማረ ሰው አስቁሞት ጉዞ ጀመሩ። እርስ በእርሳቸው እየተወያዩ ወሬው ከእስፖርት አልፎ ስለሰሞኑ የፖለቲካ ስብሰባ ሆኖ ጆኒ ከተሳፋሪው ብዙ ነገሮች አወቀ።

የጀርመን የአስተዳደር ፓርላማ በሁለት ይከፈላል። ቡንደስታግና ቡንደስ ራት ይባላል ቡንደስ ታግ ውስጥ የሚቀመጡ 656 የፓርላማ አባሎች በሕዝቡ የዲሞክራሲ ምርጫ አሸናፊ የሆኑት ናቸው። በጀርመን

ውስጥ አራት ቋሚ ሁለት ጥገኛ ፓርቲዎች አሉ እነሱም CDU,SPD,Die Grünen,PDS ቋሚ ጥገኞቹ CSU እና FDP ናቸው ።

ጀርመን ውስጥ የፖለቲካ አስተዳደሩ የሚመራው በቻንስለር ነው። የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ቢኖርም በፖለቲካ አመራር ኃይል የለውም። ምርጫው በየአራት ዓመቱ በዲሞክራሲ መንገድ ይፈጸማል። በአሁኑ ጊዜ የጀርመንን አስተዳደር የሚመራው CDU የሚባለው ሲሆን በመጪው የሴፕተንበር ምርጫ ውድድር SPD የተባለው ፓርቲ ያሸንፋል ተብሎ ይገመታል። ቢሆንም የሰሞኑ ብሬመን ውስጥ የሚደረገው የCDU ብሰባ ይህንኑ ስጋት ቀንሶ በምርጫው ውድድር ድል ለማድረግ የታቀደ መሆኑን እንግዳው የታክሲ ተሳፋሪና የCDU አባል ለጆኒ አጫውተውታል።

ጆኒ ዜግነቱ ጀርመን ስለሆነ የመምረጥና የመመረጥ መብት አለው። ሕጉ እንዲህ ይሁን እንጂ እስከዛሬ ድረስ አንድም ጥቁር በፖለቲካ መድረክ ውስጥ መመረጥ ቀርቶ ተወዳድሮ አያውቅም። ብዙ የተማረ አዋቂ ቢሆንም በጀርመን ውስጥ ጥቁር ታምኖ ቁልፍ ቦታ የተሰጠው እስካሁን የለም። እንኳን ለአስተዳደር ሥራ ቀርቶ ለእግር ኳስ ጫወታ ብሔራዊ ቡድን ውስጥ እንደእንግሊዝ ወይም ፈረንሳይ ጥቁር ተጫዋች ተመርጦ አይገባም። ይህን ጠንቅቆ የሚያውቀው ጆኒ «የዝንጀሮ ቆንጆ» ሆኖበት ነገሩ በዚህ የፖለቲካ ምርጫ ተሳትፎ አያውቅም።

ፋጡማና ክላውዝ የዓመት የረፍት ፍቃዳቸውን ጨርሰው ተመልሰዋል። በእለቱ ክላውዝ ሥራ ገብቶ ከጆኒ ጋር ተገናኝቷል። የሮዚንም መታሠር ሰምቶ ከልቡ አዝኗል። ፋጡማ ግን እርግዝናዋ እየገፋ በመሄዱ አስፈቅዳ ለተወሰነ ጊዜ ሥራ ትታለች። የሮዚ ባላንጣ የድሮ ወዳጅ የቅርብ ጠበኛ ብትሆንም በጉዳዩ አዝና ልትጠይቃት ሙከራ አድርጋለች። ግን በወንጀሉ የተጐዳው ሙራት የሀገሯ ልጅ በመሆኑ ይሉኝታ ይዟት ትተዋለች።

ጆኒ የለሊቱን የታክሲ ሥራ አገባዶ ቀኑን ተኝቶ እረፋዱ ላይ ተነስቷል። እራቱን ለማዘጋጀት ማድቤት ገብቶ ሲንጐዳጐድ የቤቱ ስልክ ተደወለ።

«ሃሎ ዮሐንስ ነኝ ማን ልበል?»

«ሊንዳ ነኝ ጋሼ ዮሐንስ አወቅኸኝ።»

«የማ ሊንዳ አላወቅሁሽም?»

«የባለቤትህ ታናሽ እህት ሊንዳ ገ/ሕይወት።»

«አ! አወቅሁሽ ከየት ነው የምትደውይልኝ።»



«ከዚሁ ከጀርመን ነው። በርሊን ያ ያልኩህ ሰውዬ የቴክኒክ ኢንጂነሩ እዛ መሥሪያ ቤት የተዋወቅሁት ጀርመናዊ ሁሉን ነገር ጨርሶ ይዞኝ መጣ እልሀለሁ።»

«እንኳን ደስ ያለሽ መቼ መጣሽ?»

«ሦስት ቀን አለፈኝ ስልክ ብቀጠቅጥ ላገኝህ አልቻልኩም። ትንሽ ሽሮና በርበሬ ይዤልህ መጥቻለሁ።»

«አመሰግናለሁ።»

«ቋንጣም አዘጋጅቼ ነበር ብቻ ስንገናኝ አጫውትሃለሁ።»

«ታዲያ መቼ ትመጫለሽ?»

«ከሰሞኑ ሰውየው እንደለቀቀኝ።»

«ታሥረሻል እንዴ።»

«አይ ማለቴ...ፍቃድ መጠየቅ ያስፈልጋል።»

«ደግ እቀበልሻለሁ» ብሎ ጆኒ ስልኩን ዘጋው።

ቤቱ ጭር ስላለበት የሆነ የአማርኛ ዘፈን ካሴት አድርጐ ያዘጋጀውን ምግብ አቀረበ። የይሁኔ በላይ የዘፈን እንጉርጉሮ ቅላጼና ግጥም ክፍሉን ሞልተው በጆኒ ሕሊና ተንቆረቆሩ።

«ፈረንጅ ሀገር ኖሮ ሰውን የሚያይ የለው፣
እንግባ ሀገራችን ሳይኖረው የሚያምረው
እንጀራና ሽሮ እንደልቤ ባገኝ
ቅቤና በርበሬ እንዳሰብኩት ባገኝ
ገንዘብና ወርቁ ሁሉም ቢሟላልኝ
የልቤ አልሞላ አለ ሀገሬ ጐድላብኝ»

ጆኒ ዘፈኑን ሰምቶ መንፈሱ ተረበሸ። እራቱን መብላት አቃተው። የጀርመን ኑሮ መሮት ሀገሩን ወዶ ናፈቀ። እዛ ያሉት ያገሩ ልጆች «ፈረንጅ ሀገር» ሲሉ እዚህ ያሉት ደግሞ «እምዬ ኢትዮጵያ» ብለው ናፍቀው ይጨነቃሉ። ጆኒ– የሕይወት እንቆቅልሽ አልገባ ብሎት ትቸገረ።

ሙዚቃውን ለውጦ የጥላዬ ገብሬን የሳክሶፎን ክላሲካል "Endless Dream" «ውሳኔ ያጣ ሕልም» የሚለውን ቅኝት እንጉርጉሮ እያዳመጠ እንቅልፍ እንደ ዋዛ ይዞት ጠረጴዛውን ተደግፎ አሸለበ።



# ክፍል አሥራ ዘጠኝ

የብሬመን የወረዳው ፍርድ ቤት የሚገኘው ዶምሳይደ ከሚባለው አካባቢ ነው። አሮጌው ሕንፃ ከአዲሱ ጋር ተገጣጥሞ ሲታይ ውበት የለውም። ቢሆንም ሥፍራው በሰው ስለተሞላ ትንሽ ደመቅመቅ ብሏል።

ዛሬ የሮዚና የሙራት ግጭት ወንጀል በዳኞች ታይቶ ለሚቀጥለው የፍርድ ውሳኔ የመጀመሪያው ችሎት ነው። ፊት ለፊት በትልቁ መድረክ ላይ ሦስት ዳኞች የሚቀመጡበት ትላልቅ ወንበሮች ሰፊውን ጠረጴዛ ይዘው ይታያሉ። ከጐን ግራና ቀኝ የከተማው አቃቤ ሕግና የፍርድ ቤቱ ዋና ፀሐፊ ተቀምጠዋል። ከመድረኩ ወረድ ባለው ወለል ላይ ከግራ ሮዚ አሥራትና የሕግ ጠበቃዋ፣ ከቀኝ ሙራትና የሕግ ጠበቃው ፊት ለፊት ይታያያሉ።

ከዚህ አለፍ ብሎ የሚገኘው ሰፊ አዳራሽ ችሎቱን ለማየት በመጡ ጥቂት ጋዜጠኞችና ልዩ ልዩ ሰዎች ጢም ብሏል። የፀጥታ አስከባሪ ፖሊሶች በሕዝቡ መሐከልና ዳርቻ ቆመው ያስተናግዳሉ። በርከት ያሉ የሮላንድ ታክሲ ሹፌሮች የኢትዮጵያ ስደተኛ መሐበር አባሎች ሌላም ብዙ ሰዎች በዚሁ አዳራሽ ተገኝተዋል። ፋጡማና ክላውዝ እንኳን አልቀሩም።

ጃኒ ለሮዚ በሰጣት ሴንጢ ምክንያትና በሁለቱ መሐከል ስለነበረው ወዳጅነትና ጠብ ለምስክርነት ተጋብዞ ያለው ሌላ ክፍል ነው። ሕዝቡ እርስ በእርሱ እያወካ አዳራሹ በጩኸት ተሞልቷል።

በእድሜያቸው ጠና ያሉ ሦስት ዳኞች ጥቁር ካባ ለብሰው ተከታትለው አዳራሽ ውስጥ ሲገቡ ሕዝቡ ብድግ ብሎ ተቀበላቸው። የመሐል ዳኛው ጠረጴዛውን በእንጨት መዶሻ ሦስቴ ደብድበው ሕዝቡ ፀጥ ሲል እንዲቀመጥ ፈቅደው ሦስቱም ዳኞች አንድ ላይ ሆነው በቀረበላቸው ወንበር ላይ ተሰየሙ።



በእለቱ ችሎት በቀረበው ወንጀል ከሳሽ ሙራት ሲሆን ተከሳሽ ጥቁሯ ፓይለት ሮዚ ነበረች። የመሐል ዳኛው የቀረበላቸውን ፋይል ተመልከተው ሮዚን የጠቡን ሁኔታ እንድታስረዳ ጋበዟት በውነት ለመናገር ወንጌል ጨብጣ ማለች። በደረሰባት ሁኔታ ሀዘን ቢሰማትም የሕግ ትምህርቷና የጥብቅና ምኞቷ አደፋፍሯት አፏ ሳይተሳሠር እንደበቷ ጐልቶ አዳራሹን ሞልቶ ተሰማ።

«ክቡራን ዳኞች፤

የከተማው አቃቢ ሕግ ጠበቃና የተከበራችሁ እንግዶች በዛሬው ችሎት እኔ ተከሳሽ ሌላው ከሳሽ ሆኖ በመቅረቡ አዝናለሁ። በአካል ተጐድቼና ደምቼ ባልገኝም በመንፈስ ቆስዬ ሕመሙ እስከመቼም በማይድን ደዌ ተለክፌአለሁ። የኔ ጉዳት ከከሳሼ ጉዳት ይበልጥ እንጂ አያንስም። ከሳሹ የሴትነት ክብሬን አዋርዶ ጉሮሮዬን አንቆ አለፍቃዴ ወሲብ ለማድረግ የመድፈር ሙከራ አድርጐብኛል። በዚህም እራሴን ለመከላከል ያደረግሁት ጥረት እንደወንጀለኛ ሊያስቆጥረኝ ፈጽሞ አይችልም። ይህ ሰው ባይገናኘኝም አድራጐቱ መንፈሴን አቁስሎታል። ይህ የሳይኮለጂ ሕመም ወንዶች በተጠጉኝ ቁጥር እያባነነ የሚያስጨንቅ ለፍቅረኛዬ የወሲብ ስሜቴን የሚገታ እስከመቼም የማይድን ከፍተኛ ስቃይ ያደርስብኛል ብዬ እሰጋለሁ። ስለዚህ ክቡራን ዳኞች እሱ ከሳሽ እኔ ተከሳሽ ሆኜ በዛሬው እለት መቅረቤን እቃወማለሁ» ብላ ቁጭ አለች። አዳራሹ በጩኸት በጭብጨባና በሁካታ ተሞላ። የመሐል ዳኛው መዶሻቸውን ከጠረጴዛው አገናኝተው መልሰው ሕዝቡን ፀጥ አደረጉት። «የጠየቅንሽ ያንቺን ጉዳት የሱን ከሳሽነት ያንቺን ተከሳሽነት ሳይሆን በእለቱ በሁለታችሁ መሐከል የነበረውን ግንኙነትና ጠብ በዝርዝር እንድታስረጂን ብቻ ነው» ብለው በድጋሚ ጠየቋት።

ሮዚ እንደ ገና ብድግ ብላ የመሐል ዳኛው የጠየቋትን በእለቱ ከሙራት ጋር የተፈጸመውን ወንጀል ከመግለጿ በፊት ከእሱ ጋር የነበራትን የሥራ ጓደኝነትና መቀራረብ ከዛም አልፎ ተቀያይሞ መጣላት አወካች።

የከተማው አቃቢ ሕግ ንግግሯን አቋርጠው ቀደም ሲል የነበረውን የሁለቱን ጠብና ግጭት እንድታብራራ ጠየቋት።

ሮዚ ድምጿን ከፍ አርጋ።

«አዎ ሙራት በታክሲ ሥራ ላይ ብዙ ጊዜ የቆየ በእድሜም የበሰለ ጨዋ ሰው ስለመሰለኝ ለሥራዬ እንዲረዳኝ ብዬ ቀርቤ ተጓድኘዋለሁ።

ምክሩና ጫወታው ደስ ስለሚለኝ አብዛኛውን ጊዜ እራት እምንበላው አብረን ነበር። ሲውል ሲያድር ግን ሁኔታው እየተለወጠብኝ ሄደ። ይህ ብዙ ዓመት በእድሜ የሚበልጠኝ ባለትዳር የልጆች አባት እኔን ለፍቅር መከጀሉ ቅስሜን ሰበረው። ይህን ስሜቱን በዘዴ ለመለወጥ ሚስትና ልጆቹን እንዲያስተዋውቀኝ ጠይቄው አደረገ። ግን ስሜቱ አልተለወጠም። ብሽሽውም እየተከታተለና አማላጅ እየላከ መልሶ ታረቀኝ። በመጨረሻ የፓርኖ ስዕሎችን አምጥቶ አሳየኝ። ስድቤ ከዚያ ወዲያ አጠገቤ እንዳይደርስ አምርሬ ከለከልኩት። የመጀመሪያ ጠባችን ሁኔታ ይሄው ነው።»

አቃቤ ሕጉ «በዚህ ሁኔታ ተጣልታችሁ ካልተቀራረባችሁ እንዴት አቶ ሙራት እርሶ መኪና ውስጥ ገብቶ ወንጀሉ ሊፈጸም ቻለ? ወንጀል የፈጸሙበትም ሴንጢ በእለቱ እንዴት ሊይዙት ቻሉ?»

ሮዚ ለጥያቄው መልስ ሰጠች። በመሐሉ ለእረፍት አሜሪካ ደርሳ መመለሷን የሮላንድ ታክሲ ድርጅት ባለቤት ሁለቱን ማስታረቃቸውንና ከሙራት ጋር እንደ በፊቱ ባይሆንም ሰላምታ የመሰጣጣትና ቀርቦ የመገናኘት ሁኔታ በመፈጠሩ በዚህ ሁኔታ ነው ሙራት መኪናዋ ውስጥ የገባው። ስለ ሴንጢውም ጆኒ እራሷን ከወንበዴዎች እንድትከላከልበት የሰጣት መሆኑን አብራርታ ቁጭ አለች። የመሐል ዳኛው ከሳሽ የሆነውን አቶ ሙራትን በእለቱ የተፈጸመውን ወንጀል እንዲያብራራ ጠየቁት።

ሙራት ጀርመን ውስጥ ሲኖር ብዙ ጊዜ ቢሆነውም የጀርመንኛ ቋንቋ በደንብ አጣርቶ ስለማይናገር በቅድሚያ ታውቆ የቱርክ አስተርጓሚ ቀርቦለታል። እውነቱን ለመናገር ቁራን ጨብጦ ማለ።

የቀድሞ ግንኙነታቸውንና ጠባቸውን ገልጦ «በእለቱ አጠገቧ ሆኜ እመኪና ውስጥ ስንጫዋወት ምንም ሳልነካት በድንገት ከቦርሳዋ ውስጥ ሴንጢ አውጥታ ብልቴን ጉድታ ሆዴን ወጋችው እንጂ እኔ እሷን አስገድጄ ወሲብ ለማድረግ ጨርሶ አልሞከርኩም። እሱ ሁሉን የሚያይ አላህ ይፍረድብኝ! እኔ ሮዚን እንደልጆቼ የማያት የምወዳትና የማከብራት ስለሆነች ፈጽሞ በዚህ ዓይነት እሷን ልደፍራት ቀርቶ ሀሳብ የለኝም» ብሎ ቁጭ አለ።

የሮዚ ጠበቃ «አንተ የማስገደድ ሙከራ ካላደረግህ ሱሪህ ወልቆ ብልትህ ካልታየ እንዴት ልታገኝህ ቻለች?



«ነገሩ አሳፋሪ በመሆኑ ልናገረው አልፈለግሁም እንጂ ሁኔታው እንዲህ ነው። በጫወታ ጫወታ ሮዚ እናንተ ቱርኮች እንደ ክርስቲያኖች ትገረዛላችሁ ወይ ብላ ጥያቄ አቀረበችልኝ። አዎ እንገረዛለን ብላት ብልትህን ካላሳየኸኝ አላምንም ብላ ወተወተችኝ። ስፈራ ስቸር የሱሪዬን ዚፕ ከፍቼ ቀስ ብዬ ወጣ ሳደርገው ሲንጢዋን መዘዝ አድርጋ ብልቴን ስታስነካኝ እጆቿን ጨብጬ ታገልኳት ድንገት ስለቱ ሆዴን ወግቶ አቆሰለኝ። ከዛ በደም ፍላት ያደረጉትን አላውቅም» ብሎ ለተጠየቀው መልስ ሰጠ።´ነገሩ እውነት ቢሆንም ሮዚ ከወዲህ «ፍጹም ሀሰት ነው ይሄ የራሱ ልቦለድ ታሪክ ነው ፈጽሞ ውሸት ነው ውሸት» ብላ ጮኸች። ሕዝቡም ከእሷ ጋር ሆኖ ተንጫጫ። የመሐል ዳኛው ፀጥታውን አስከብረው የወንጀሉን ሁኔታ ለማጣራት በሮዚ በኩል የቀረበውን መስካሪ ጆኒን እንዲቀርብ አደረጉ።

ጆኒ ካለበት ልዩ ክፍል ለምስክርነት ተጠርቶ እችሎቱ አዳራሽ ገባ። ቃለ መሐላ አድርጎ ከሮዚ ጋር በሀገር ተወላጅነት እንጂ የሥጋ ዝምድና እንደሌላቸው በቅድሚያ ተናግሮ ቁጭ አለ።

የመሐል ዳኛው «በሁለቱ መሐከል የነበረውን ወዳጅነትና ጠብ የሚያውቀው ካለ ተናግሮ ሴንጢውን ለምን ለሮዚ እንደሰጣት ተጠየቀ።

ጆኒ ብድግ ብሎ ሮዚን የረዳት መስሎት ያልተጠየቀውን ቀባጠረ።

«ሮዚ እንደ ልጁ የማያት የምወዳት የሀገሬ ልጅ ናት። የሷን ጥቃት ጨርሶ አልወድም። ከሙራት ጋር የነበራቸውን የሥራ ግንኙነትና ጓደኝነት አውቃለሁ። በመጨረሻም ሮዚ ሙራት በፍቅር ዓይን ተመልክቶ ለወሲብ መከጀሉን ነግራኛለች። በሁኔታው ተቆጥቼ ሁለተኛ አጠገቧ እንዳይደርስም አስጠንቅቄዋለሁ እሱም ከብጤዎቹ ጋር በመሆን ሁለታችንንም ለማጥቃት ዝቶ በሮዚ ላይ የመኪና አደጋ ለማድረስ የተንኮል ሙከራ ከብጤዎቹ ጋር ሆኖ አድርጓል።»

ሦስቱም ዳኞች በነገሩ ተገርመው ዓይናቸውን ተከሉበት። ከግራ አቃቤ ሕጉ የተደረገው የመኪና አደጋ እንዴት እንደሆነ እንዲያብራራና ሙራትና ባልደረቦቹ መሆኑን ከበቂ ማስረጃ ጋር እንዲናገር ተጠየቀ። ጆኒ ባለፈው ጊዜ በሮዚ ላይ የደረሰው የመኪና አደጋ በፖሊስ ተመርምሮ ለተንኮል የተሠራ ወንጀል መሆኑ ተመዝግቧል። ግን ወንጀለኛው ማን እንደሆነ ተመርምሮ የተገለጸ ነገር ባለመሆኑ ጆኒ በጉዳዩ መልሶ

ተጠየቀ። ፋጡማ ሁስማን በጊዜው የሱ ወዳጅ ስለነበረች የሙራትና የብጤዎቹ ተንኮል መሆኑን ሰምታ አስምላ ምስጢሩን መንገሯን ሳይደብቅ ገልጦላቸዋል። ሴንጢውን ለሮዚ የሰጣት ግን እንዲህ ያለውን በቀል እንድትወጣበት ሳይሆን ከልዩ ልዩ ወንበዴዎች እራሷን እንድትከላከልበት መሆኑን ጭምር ገልጦ ተናገረ። የወንጀሉ ሁኔታ ዳኞቹ ከገመቱት ውጪ በመሆኑና የፋጡማም ምስክርነት ስለሚያስፈልግ ሌላ ቀጠሮ ተሰጥቶ ሕዝቡ ተበተነ።

የጆኒ የሕግ ባለቤቱ ታናሽ እህት ሊንዳ ገ/ሕይወት ጆኒን ለመጠየቅ ከበርሊን ከተማ በባቡር ተሳፍራ ብሬመን ገባች። የሰዓቱን ፕሮግራም ከጆኒ ጋር ቀደም ብለው በስልክ ተነጋግረው ስለተቃጠሩ ዋናው ባቡር ጣቢያ በሰላም ተገናኝተው መኖሪያ ቤቱ ወሰዳት።

ሊንዳ ሰውነቷ ቢከሳም የሰላምና የብሩህ ተስፋ ገጽታ ይታይባታል። የጆኒ ቤት ካመጣት ጀርመናዊ ቤት የተሻለ በመሆኑ ደስ አላት። ጓዞቿን ፈታትታ ለጆኒ ያመጣችለትን ሽሮና በርበሬ ድርቆሽና ሌላም የስጦታ ጌጣ ጌጥ እቃዎችን ሰጠችው። ጆኒ ስጦታውን አመስግኖ ተቀበለ። የታላቅ እህቷን ማለት የድሮ የሕግ ባለቤቱን አድራሻ የሰማችው ነገር እንዳለ ጠየቃት። አድራሻዋ በትክክል ባይታወቅም ለታላቅ ወንድሟ ስልክ ደውላ ናይጄሪያ የሚባል ሀገር መኖሯን ነገረችው። የልጆቹን ጉዳይ ቢጠይቃት እሷም ደህና እነሱም ደህና መሆናቸውንና የሱንም አድራሻ ማወቃቸውን፣ ያገባችው ሰው ሆላንዳዊ የሆነ በነዳጅ አውጪ ድርጅት ውስጥ የሚሠራና በዚሁ ጉዳይ ቀድሞ ከሚኖሩበት ከአረብ ሀገር ተዛውረው መሄዳቸውን ጭምር አጫወተችው። የጆኒ ዓይኖች ፊት ለፊት የሚያዩትን እንግዳ ትተው በሀሳብ ትዝታ የጥንት ሚስቱን ትንንሽ ልጆቹን ስለተመለከተ ጆኒ በትካዜ ፈዞ ቆመ። ናይጄሪያ ከጀርመን ብዙ ይርቃል። ስንትና ስንት ሚሊዮን ሕዝብ ከሚኖርበት የጥቁር ከተማ እሷን ፈልጐ ማግኘትና የልጆቹን ናፍቆት መወጣት እጅግ አስቸጋሪ ነው። ልጆቹን እንጂ ከእንግዲህ እሷን ማግኘት ምን ይጠቅማል? የሌላ ሆናለች። የነበራቸው የትዳር ፍቅር በመለያየት መቀስ ተቆርጦ በጊዜ እርዝማኔ ተውጦ ተረስቷል።

ለእንግድነት የተዘጋጀው ልዩ ልዩ ምግቦች ቀርቦ አብረው ተቋደሱ። ከኢትዮጵያ ያመጣችውም ጥሬ ቡና ተቆልቶ ቤቱ በጥሩ ቃና ተሞልቶ ሸተተ። ሊንዳ እንግዳም ብትሆንም የጆኒን የትዝታ ቀዝቃዛ ስሜት



ለመለወጥ ተደፋፍራ ቡና አፍልታ እረከቦት አቅርባ እጣን አጭሳ በኢትዮጵያ ወግና ባህል ያለውን ልማድ አሳየችው። አብረው ቡና ጠጥተው ከፍሉ የብቸኝነት የፈረንጅ ሀገር ጠረኑን ለቆ በምትኩ ሰው ሰው የሚሸት የአንድነት የሞቀ የሀገር ቤትን መአዛ አገኘ።

ጆኒ የቀረበለትን አቦል ቡና ጠጥቶ ከኢትዮጵያ የመጣውን የገብስ ቆሎ እየቆረጠመ ቋንጣ አምጥታ እንደሆነ እንድታቀርብለት ሊንዳን ጠየቃት።

«ውይ ጋሼ ዮሐንስ የቋንጣውስ ነገር የሚገርም ነው»

«እንዴት?»

«እውነት እግዜር ይወድሃል»

«ምን ማለትሽ ነው አልገባኝም?»

«ይሄውልህ ጋሼ ዮሐንስ ወደዚህ መምጫዬ ሲቀርብ ጥሩ ሥጋ ገዝቼ በደንብ ተዘልዝሎ ገመድ ተወጥሮ ተሰቅሎ ሰነበተ። ታዲያ እኔ ለቪዛ ጉዳይ ወዲያ ወዲህ ስል የቤቱ ሠራተኛ ቋንጣውን ዝንብ ሲወረው ታይና የሆነ የሚረጭ ፍሊት አንስታ ትረጭበታለች። መሄጃዬ ሲቃረብ ቋንጣውን ሰብስቤ በላስኪት አስሬ ጠረጴዛ ላይ አኖርኩት። ከጓዳ ጓዳ ስዘዋወር የመንደር ውሻ እቤት ገብቶ የተቀመጠውን ቋንጣ ወስዶ በላው። እየጮኩ ውሻው ወዳለበት ብሄድ ውሻው ወድቆ አረፋ ደፍቆ ሲፈራገጥ አገኘሁት። በነገሩ ሁኔታ እኔም ጐረቤትም ተደናግጠን የተረፈውን ቋንጣ ብናስመረምረው መርዝ ያለበት ሆኖ ተገኘ። ለዚህ ነው ጋሼ ዮሐንስ እግዜር ይወድሃል ያልኩት። የሚገርምህ እኛም እንኳን ለቅምሻ አለመብላታችን ነው።»

«እንኳን እግዜር እናንተንም አተረፋችሁ። በዚህ አኳኋንማ ያመጣሽውም ሌላው ነገር ያጠራጥራል?» ብሎ የጐረሰውን ቆሎ ሳይውጥ መታጠቢያ ቤት ሄዶ ተጉመጠመጠ።

«አይ በሌላውስ አትጠራጠር በንጽህና ቤት ተቀምሶ የተዘጋጀ ነው በዚህ ላይ የእርሻ የጤና ምርምር አይቶታል» ብላ ያመጣችውንም ሽሮና በርበሬ ፈታትታ እየቀመሰች በየማኖሪያው ከፋፍላ ስታስቀምጥ አስነጥሶ አሳላት።

ጆኒ ደንግጦ «ይማርሽ! ብሎ አጽናናት። ሊንዳ ሳሉ አልቆም ብሎ አስጨነቃት። ሰውነቷ ግሎ አላባት። ጆኒ የመጣለትን የምግብ ስጦታ ጠቅሎ ጣለው። በርግጥ ምግቡ የተመረዘ አልነበረም። ሊንዳን

ያስነጠሳት የበርበሬው ብናኝ ይሁን እንጂ ጉንፋኑና ሳሉ የሰነበቅ ነበር። የሚጠጣ ለስላሳ መጠጥ አቅርቦላት ለጊዜው ሳልና ትኩሳቱ በረድ ብሎ ጤናማ መልክ ታየባት።

ሊንዳ ጀርመን ለመቆየት የተሰጣት ቪዛ የሦስት ወር ሆኖ አሁን የቀራት አንድ ወር ብቻ ነው። ጋብዞ ያመጣት ጀርመናዊ ሰው ልጆች ያሉት ባለትዳር ብመሆኑ ሊንዳን አምጥቶ ያስቀመጣት በርሊን የሆነ ጓደኛው ቤት ነበር። ይሄም አድራጎት ከሰውየው ፍጹም ያልጠበቀችው አድራጎት በመሆኑ የወደፊት እድሏ ጨልሞ አጠራጠራት። ቪዛዋ ከማለቁ በፊት እንዲያድሱላት ብትጠይቅ እንቢ አሻፈረኝ ብለው መለሷት። ነገሩን ለጆኒ ብታጫውተው «ያለሽ እድል ፓስፖርትሽን ጥለሽ የፖለቲካ ጥገኝነት መጠየቅ ወይም ቪዛው ከማለቁ በፊት የጀርመን ዜግነት ያለው ሰው ፈልጎ ማግባት» እንደሆነ ነገራት።

ሊንዳ በዚህ አጭር ጊዜ በርሊንም ብሬመንም እየተመላለሰች የተባለውን ሙከራ አደረገች። እሷን ወድዶ እሷም እሱን ወድዳ እውነተኛ ትዳር ለመመሥረት ባለመቻሉ በገንዘብ ኃይል የወረቀት ጋብቻ የሚያደርግ ሰው ተፈልጎ ታጣ። የቀራትም የአንድ ወር የመቆያ ቪዛ አለቀ። ያላት እድል ስሟን ለውጣ የፖለቲካ ጥገኝነት ጠይቃ እጇን መስጠት ብቻ ሆኖ ተገኘ።

በጊዜውም የጀርመን የውስጥ አስተዳደር በዚህ ጉዳይ ጠንካራ ግንዛቤ ወስዶ ትክክለኛ የፖለቲካ ሰው ያልሆኑትን እየመረመረ ከሀገር ውስጥ የሚያስወጣበት ወቅት ነበር። ሊንዳ እንኳን የፖለቲካ ተሳታፊነት ቀርቶ ስለሀገሯ አስተዳደር ጨርሶ የማታውቅ ምስኪን ሰው ነበረች።

ቢሆንም ጆኒ ያላት እድል ይሄው ብቻ ስለሆነ ያለ የሌለውን የሀገር ቤት የፖለቲካ ችግር አትቶ ያለውን መንግሥት የምትቃወምና በዚህም ለእሥርና ለግድያ ስትፈለግ በአሰብ በኩል አምልጣ በኢትዮጵያ መርከብ ተደብቃ ጀርመን መግባቷን የሚያትት ልብ ወለድ ጽፎ ሰጣት።

ሊንዳ ገ/ሕይወት በሌላ ስም ተመዝግባ የእጆቿ አሻራ ተወስደው፣ በግራና በቀኝ ፎቶግራፍ ተነስታ የፖለቲካ ስደተኛ በመሆን ተመዘገበች። ጉዳይዋ በዳኞች ታይቶ ፍርድ እስኪሚሰጣት ድረስ ፍራንክፈርት ጊስን በሚገኘው የስደተኞች መኖሪያ ካምፕ እንድትቀመጥ ተደረገ። ይህ ቦታ የተለያየ ዜግነትና ጠባይ ያላቸው ብዙ ስደተኞች ስለሚኖሩበት ትንሽ ሥርዓት ይጐለዋል። የተመጣጠነ ምግብና የኪስ ገንዘብ ግን ስለሚሰጥ ሁኔታው ከሥር ቤት ለየት ይላል። ሊንዳ ሀገሯ ሆና የናፈቀችው የፈረንጅ



ሀገር ኑሮ እንዲህ ሆኖ ስለጠበቃት እድሏን አማራ በተሰፋ ጭላንጭል ተውጣ እዚሁ ቆየች።

የጆኒ የመኖሪያ ቤት መሰንበቻውን የነበረውን የሀገር ቤት መአዛና ጠረን ለቀው ከሊንዳ ጋር አብረው ኮበለሉ። ጆኒ በጊዜ ከመኝታው ተነስቶ የሳሎኑን መስኮቶች ከፍቶ የቀዘቀዘ የአየር ትንፋሽ ተነፈሰ። አፍንጫው ግን በአበሻ ጉንፋን ተዘግቶ የቤቱን ጠረን ማሽተት አቃተው። ጠጥቶ ስላደረ ትናንሽ ዓይኖቹ ቀልተው ሞጭሙጨዋል። የደከመ ሰውነቱን ለማዝናናት እጆቹን ወደላይ ወጥሮ እያዛጋ ተንጠራራ። ጭር ያለ ክፍሉ በቀኪ ሳሉ ጨኸት ተስተጋባ።

ጆኒ ያ የብቸኝነት ኑሮው መልሰው ወረሩት። ለዚህም ያለውን ጊዜያዊ ማከላከያ ሙዚቃ ከፍቶ ሀገር ቤት ያለችውን የትዳሩን እጮኛ እመቤትን አስታውሶ የምትመጣበትን ቀን ናፍቆ ተከዘ። እጅ እጅ የሚለው የበአድ ሀገር ኑሮ አስጠላው። ጽሕፈት ጠረጴዛው ላይ ተቀምጦ እድሉን እያማረረ የሕይወትን ውጣ ውረድ ጐዳና በመመልከት በግል ፍልስፍና ምርምሩ ተዋጠ።

ጆኒ የሰዎች ሕይወት በሦስት የአስተሳሰብ ቁራኛ ክስተት የተወጠረ መሆኑን አስቦ አገናዘበ። የዛሬውን ሁኔታ በውድም ሆነ በግድ ተቀብለው ለእለት ኑሮአቸው የሚፍጨረጨሩ፣ ወይም የነገን ሁኔታ በብሩህ ተስፋና ምኞት የሚጠብቁ፣ አለዛም መጪውን ጊዜ በስሜት አደብዝዘውና አጨልመው የሚመለከቱ፣ ፍጡራን። ጆኒ ከነዚህ ክፍልና መደቦች የየትኛው ወገን መሆኑን እስካሁን አያውቅም። የእያንዳንዱ ሰው የሕይወት ኑሮ ልዩ እጣ እድል አለው። «ሰው ያስባል እግዜር ይፈጽማል» የሚባለውም ለዚህ ነው። በዚህ ጉዳይ እስካሁን በሳይንስ የተገኘ መላ ምት እንጂ የተጨበጠ ማስረጃ የለም። በስሉ ከተቀቀለ ንፍሮ አንድ ሁለት ጥሬ ፍሬ፣ ከከባድ አደጋ የተረፈ ጥቂት ሕይወት፣ በየጊዜው ይገኛል። ለምን ሲባል የአርባ ቀን እድል የእግዜር ፍቃድ ቢሆነው ተብሎ ይታመናል። ጆኒ የግል ኑሮውን ከአርባ ቀን እድሉና ጥረቱ ጋር እያወዳደረ ሕይወትን መርምሮ መልሶ አጣ።

በብሬመን የሚገኘው የወረዳው ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዳራሽ ችሎት ካለፈው ጊዜ በሰው ታምቋል። የሰው ትርምስና ጨኸት ትንፋሽና ሁካታ አዳራሹን አምቆታል።

የሮዚና የሙራት የጠብ ወንጀል በአንደኛና በሁለተኛ ችሎት ነገሩ ተመርምሮ ፍርድ ለመስጠት እስካሁን አልተቻለም። ይህንኑ ለማጣራት ከሕግ ጠበቃዎቻቸውና ምስክሮቻቸው ጋር ቀርበው በእለቱ የሦስተኛ ዙር የመጨረሻ መወሰኛ ችሎት ተከፈተ።

የመሐል ሰብሳቢ ዳኛ የቀረበላቸውን ፋይል መርምረው የከሳሽ ጠበቃ ያለውን አስተያየት ለፍርድ ቤቱ እንዲገለጽ ጠየቁት።

«ክቡራን የወረዳ ከፍተኛ ፍርድቤት ዳኞች»
ክቡር የከተማው ሐቃቢ ሕግና
ክብራትና ክቡራን» ብለው የሙራት የሕግ ጠበቃ ንግግራቸውን ጀመሩ።

«ባለፉት ሁለት ተከታታይ ችሎቶች ምስክሮች ቀርበው ቃላቸውን ሰጥተዋል። ተከሳሿም ወይዘሪት ሮዚ አሥራት ከሳሹ አቶ ሙራት ለወሲብ ብሎ በማስገደዱ ያደረጉት ወንጀል መሆኑን አምነዋል። ደንበኛዬ የሆነው ከሳሽ አቶ ሙራት ሁኔታው በወሲብ ድፍረት ሙከራ ሳይሆን በቂም በቀል በዘዴና በተንኮል የተፈጸመ መሆኑን ለዚሁ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አስረድቷል። በርግጥ ወንጀሉ ሲፈጸም ከሁለቱ ሰዎች ሌላ የዓይን ምስክር ባለመኖሩ ነገሩን ለማጣራት እስካሁን ቆይቷል። ወንጀሉ ከተፈጸመ በኋላ ግን በአካባቢው የነበሩ ፖሊሶችና የሕክምና ባልደረቦች የነበረውን ሁኔታ ባለፈው ችሎት ተጠይቀው ቃላቸውን መስጠታቸው ይታወሳል።

በዚህም ደንበኛዬ አቶ ሙራት ከወይዘሪት ሮዚ አሥራት ጋር ምንም የወሲብ ግንኙነት እንዳላደረገ በሕክምና ምርምር ተረጋግጧል።» ብሎ ንግግሩን ሲቀጥል የሮዚ የሕግ ጠበቃ ንግግሩን አቋርጦ «እቃወማለሁ» ብሎ ጮኸ። የመሐል ሰብሳቢ ዳኛ ቅዋሜውን እንዲያሰማ ፈቀዱለት።

«የወንጀሉ ክስ ወሲብ አደረገ ሳይሆን ለወሲብ ሥራ ማስገደድ ነው። እንዲህ ያለው አድራጐት በሕክምና ውጤት ስላላገኘ ወንጀሉን አይቀንሰውም። ደንበኛዬ ወይዘሪት ሮዚ ለዚህም ነው እራሷን ተከላክላ ከወሲብ አድራጐቱ የፀዳችው።» ብሎ ቁጭ አለ።

የአቶ ሙራት ተከላካይ ጠበቃ ንግግሩን በመቀጠል ደንበኛዬ አቶ ሙራት ወይዘሪት ሮዚን በወሲብ ለመገናኘት ያደረገው ሙከራና ትግል እንደሌለ የተከሳሿን ጭኖችና ሌላ አካል በእጅ ተጨብጦ ስላልበለዘ በመሐላቸው ትግል እንዳልነበረ ሐኪሞች አረጋግጠዋል።



ሮዚ በንዴት ብስጭት ብላ «እቃወማለሁ» ብላ ጮኸች። ዳኛው ፈቀዱላት። «በእለቱ በኔ ላይ የተደረገ የሕክምና ምርምር አልነበረም። እሥር ቤት ቆይቼ በሦስተኛው ቀን ነበር የተመረመርኩት። ይህም ለበለዘ አካሌ እጋዜ ስለሰጠው ምርምሩ በቂ ማስረጃ ሊሆን አይችልም። እንዳውም በጠባችን መሐከል የቆሰለው ወንጀለኛ ደም ሰውነቴን ስለነካካው የኤድስ በሽታ አጋብቶብኝ እንደሆን ወንጀለኛው እንዲመረመር ፍርድቤቱን እጠይቃለሁ» ብላ ቁጭ አለች። ሕዝቡ ከዳር እስከዳር ተንጫጫ የሙራት ተከላካይ ጠበቃ «ይህ ጉዳይ ከቀረበው የወንጀል አፈጻጸም ጋር የማይገናኝ በመሆኑ ተቃወመ። የሮዚ ጠበቃ «ያገናኘዋል» በማለት ተከራከረ። ዳኞቹ አብሮ ለመመካከር የአንድ ሰዓት እረፍት ተደርጐ ችሎቱ ቀጠለ።

ፋጡማ ዑስማን ለምስክርነት ተጠርታ እችሎቱ አዳራሽ ገባች። አለባበሷ እንደወትሮ ሱሪ ሳይሆን እርግዝናዋን እንዲሸፍንላት ሰፋ ያለ ቀሚስ ነበር። እውነቱን ለመመስከር ቁራን ጨብጣ ብትምልም ሙራትና ግብረ አበሮቹ በሮዚ ላይ የሆነ ሸር ለመፈጸም መዘጋጀታቸውንና ባለፈውም ጊዜ በሮዚ ላይ የደረሰው የመኪና አደጋ የነሱ መሆኑን ተጠይቃ ካደች። ይህንንም ለጆኒ ጨርሶ እንዳልነገረችው በመሃላ ዋሽታ አረጋገጠች።

ጆኒ በድጋሚ ለምስክርነት ተጠርቶ ቃሉን ሳይለውጥ በመጀመሪያ ችሎት የተናገረውን ሳይሳሳት በግልጽ አስረዳ። የከተማው አቃቢ ሕግ በልዩ ልዩ መስቀለኛ ጥያቄ ቢያጣድፈውም የነበረውን ሁኔታና አሚታ የሰማውን አሉባልታና ሀቅ ጥርጣሬና መላምት ደርድሮ መልሱን ሰጠ። የአቶ ሙራት ጠበቃ ጆኒን ይህን ጉዳይ እንደሰማ ለሮዚ ጥንቃቄ እንድትወስድ መንገሩን ጠየቁት። ሳያመነታ ጉዳዩን ለሮዚ እንደነገራት በዚህም ፍራቻ ነገሩ በረድ እስኪል የዓመት እረፍቷን ወስዳ አሜሪካን መሄዷን ጭምር መሰከረ።

የአቶ ሙራት ጠበቃ ፊቱ በደስታ ፈካ። በዚሁ የምስክርነት ቃል በእለቱ ያደረገው ወንጀል በአጋጣሚ የተደረገ ሳይሆን በቂም በቀል መሆኑን ከበቂ ማስረጃ ጋር አቀረቡ። ለዚህም አድራጐት ብዙ አንቀጾች ጠቃቅሰው ለወረዳው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች ለከተማው አቃቢ ሕግና በእለቱ ችሎት ለተሰበሰቡ ሰዎች ልዩ ልዩ ጥቅሶችንና ምሳሌዎችን አስገብተው የሮዚን ጥፋተኛነት አረጋግጠው ለዚህ የቂም በቀል ወንጀል ትክክለኛውን ፍርድ ዳኞቹ እንዲሰጡ በአክብሮት ጠየቁ።

ዳኞቹ በማይሰማ ድምፅ እርስ በርሳቸው ተንሾካሽከው የተከሳሽ ጠበቃ በጉዳዩ ያላቸውን አስተያየት እንዲናገሩ ፈቀዱላቸው። የሮዚ ጠበቃ ከወንበራቸው ብድግ ብለው።

«የከሳሹ ጠበቃ በአንድ በተዛባ የምስክርነት ቃል ተወስነው ወንጀሉ የቂም በቀል ድርጊት ነው ብለው ያቀረቡትን አባባል እቃወማለሁ። አንደኛ ጆኒ የሰማውን ወይም የጠረጠረውን ለተከሳሿ ሮዚ ፈጽሞ አልነገራቸውም። ይህንንም ሀቅ ተከሳሿን ጠይቆ መረዳት ይቻላል። ሁለተኛ ከሳሹ አቶ ሙራት የደረሰባቸው ጉዳት ለሕይወታቸው የማያሰጋ የቀዶ ጥገና ሕክምና ተደርጐ መዳናቸው ሐኪሞች ያቀረቡት ማስረጃ ያረጋግጣል። ተከሳሿ የሆኑት ደንበኛዬ ወይዘሪት ሮዚ አሥራት ግን በእለቱ በተፈጸመው የወሲብ ድፍረት ወንጀል አዕምሯቸው ቆስሎ የዘላለም ደዌ እንደሚያሳድርባቸው አልጠራጠርም። ስለዚህ ክብር ፍርድ ቤቱ ይህን ጉዳይ አጣርቶ ትክክለኛውን ፍርድ እንዲሰጠን በአክብሮት እጠይቃለሁ።» ብለው ቁጭ አሉ። ዳኞቹ አሁንም ተጠጋግተው አፍ ለአፍ ገጥመው ተንሾካሾኩ።

የከተማው ዐቃቢ ሕግ ሮዚ ከአሁን በፊት ያደረገችው ወንጀል እንዳለና እንደሌለ የአእምሮ ሕመምም እንደሌለባቸው የቀረበላቸውን የወንጀልና የሕክምና ማስረጃ ፋይል አገላብጠው ከተመለከቱ በኋላ ለፍርድ ቤቱ የመጨረሻ ሀሳብ ወይም አስተሳሰብ እንዳላቸው ጠየቁ።

አዳራሹ በሰው ትንፋሽ ተሞልቶ ቢሞቅም ሮዚን ከብቸኝነት የሚመጣ ቅዝቃዜ ተሰማት። ያ እንደመስከረም ጮራ የፈካ ያማረ ጠይም ፊቷ አኩርፎ አዘነ። የፍርዱ አካሄድ ምን አቅጣጫ እንደያዘ ልቧ አውቆ በፍርሃት ተጨነቀ። መቆም አቅቷት እግሮቿ ተብረከረኩ። ሆዷን ባር ባር ብሏት «የምናገረው የለኝም» ብላ ጠረጴዛው ላይ ተደፍታ ተንሰቅስቃ አለቀሰች።

የተሰየሙት ሦስት ዳኞች የመጨረሻውን ፍርድ ለመስጠት ከአዳራሹ ወጥተው ሌላ ክፍል በመሆን እርስ በእርሳቸው ተመካከሩ።

ከትንሽ ቆይታ በኋላ ሦስቱም ዳኞች ተመልሰው እችሎቱ አዳራሽ ሲገቡ ሕዝቡ ቆሞ ተቀበላቸው። የመሃል ሰብሳቢ ዳኛ ከወንበራቸው ተነሥተው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው፣ «አገርንና ሕዝብን ወክለን እንድንሠራ በተሰጠን ኃላፊነትና አደራ መሠረት ጉዳዩን ከተመለከትንና ከመረመርን በኋላ በተከሳሽ በወይዘሪት ጤናዬ አሥራት ማለት በሮዚ ላይ የሁለት ዓመት እሥራት በመፍረድ ጉዳዩን በዚሁ ዘግተናል» በማለት ለሕዝቡ አሰምተው ሦስቱም ዳኞች ከአዳራሹ ተያይዘው ወጡ።





# ክፍል ሃያ

ሰማዩ በሮዚ መታሰር አዝኖ ያኮረፈ ይመስል ጠቋቁሯል። ንፋሱም አይሉ እሷን ከፖሊሶች ጥበቃ ነጥቆ ለመውሰድ ከጅሎ በኃይል ይነፍሳል። አየሩም ቢሆን እንደሷ አካል ቀዝቅዞ ይበርዳል። የጊዜው ወቅት ገና ሳይገባደድ ጀንበሯ እሰማዩ የአድማስ አፎት ውስጥ ሳትከተት እንደ ሮዚ ፊት ጨፍግጋለች።

ሰው ነፃነቱ ሲገፈፍ፣ መብቱ ሲደፈር፣ ፍትህ አጥቶ ሲበደል፣ የዛሬ ሕልውናው እንደ በረዶ ሟሙቶ ሲቀልጥና የነገ ተስፋው ሲሟጠጥ ምን ጊዜም የተፈጥሮን የውበት ክስተት ማየት አይችልም። ምናልባትም ለዚህ ይሆናል የእለቱ የጊዜ ወቅት ለሮዚ ጨፍግጐና ጨልሞ የታያት።

እጆቿ በሰንሠለት ታሥሮ ከወረዳው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፖሊሶች ታጅባ በቀረበላት መኪና ውስጥ ገባች። አንገቷን ወደታች ደፍታ ወደማታውቀው አቅጣጫ ወደ ትልቁ እሥር ቤት ነጐደች።

ይህ በብሬመን የሚገኘው ትልቁ እሥር ቤት ጀርመኖች (Der Knast in Oslebshausen) ይሉታል። በአጠቃላይ ከርቸሌ ማለት ነው። የተቋቋመው በጥንት ጊዜ ቢሆንም እሥረኞችን ለመቆጣጠር ልዩ ልዩ ዘመናዊ ኤሌትሮኒክ የቴክኒክ መሣሪያዎች አሉበት። ግቢው በጣም ሰፊ ሆኖ የሴቶችና የወንዶች ድንበር ቦታ በጠንካራ የሽቦ አጥር ተከልሎ ተለይቷል። በአጠቃላይ ከልሉ ከ800 እስከ 1200 የሚደርሱ እሥረኞችን መያዝ ይችላል።

ይህ ታላቅ እሥር ቤት በውስጡ አንድ ቤተክርስቲያን በደንብ የተደራጀ ክሊኒክና የተለያዩ የሥራ ማከናወኛ ልዩ ልዩ የጐጆ እንዱስትሪዎች ይገኙበታል። እስረኞቹም የሚዝናኑበት ትልቅ የስፖርት

እንጂ ሌላ አታውቁም። ለቅሶሽን ትተሽ ዝፈኚ። ሀገርሽ ያልነበረሽን አዲስ አንሶላና ንጹህ ብርድልብስ አግኝተሻል። ምን ጐደለሽ? ቢንቦ! ምናልባት የቸገረሽ ሴክስ (Sex) ከሆነ እሱም እዚህ ሞልቷል። ግን አንቺን በሴክስ የሚፈልግ ማን አለ?»

ሮዚ ተቆጥታ ምንም ሳትናገር ከመኝታዋ ፍንጥር ብላ ጉሮሮዋን አንቀቻት። ወንዲላዋ እጆቿን ከጉሮሮዋ በግድ አስለቅቃ ፀጉሯን ጨምዳ አልጋዋ ላይ ገፍትራ ጣለቻት። አሁንም ሁለቱ ሌላ እሥረኞች እመሐል ገብተው ገላገሉ። የእራት ሰዓት ደርሶ የስር ቤቱ ክፍል ተከፍቶ ሦስቱም እሥረኞች ተከታትለው ወደምግብ አዳራሽ ገቡ። ሮዚ ብቻዋን እክፍል ውስጥ ቀረች። እራት ለመብላት ወስፋቷ ተዘጋ። መተኛትም አቅቷት ለሊቱን ስትገላበጥ አድራ እንቅልፍ በአይኖቿ ሳይዞር ነጋ።

ማልዳ የተነሳችው የሮዚ ጠበኛ ወንዲላ የሮዚን ብርድልብስ ገፋ ቀሰቀሰቻት።

«ያለሽው ሆቴል ሳይሆን እሥር ቤት ነው። እዚህ ሲነጋ መጋደም የለም። ተነስተሽ ክፍሉን ጠርገሽ ወልውይ» ብላ መጥረጊያ አቀበለቻት።

ሮዚ ከመኝታዋ ፍንጥር ብላ ተነስታ መጥረጊያውን ተቀብላ ወደዛ ወረወረችው።

«እኔ የናንተ ገረድ አይደለሁም። ብጤያችሁን ፈልጉ» ብላ ጮኸችባቸው።

ሌላዋ እሥረኛ ከመኝታዋ ቀና ብላ «ጽዳት ግርድና ሳይሆን ጤንነት ነው። አንቺ ተግማምተሽ እኛን ማግማማት የለብሽም» ብላ ተቆጣቻት።

ሮዚ ሁሉም በሷ ላይ ስላደሙ ትዕግሥት አድርጋ በለሰለሰ ድምፅ «ሁላችንም ካጸዳን ለሥራው ታዛዥ ነኝ። ግን እናንተ ተጋድማችሁ እኔ የማጸዳበት ምክንያት የለም» ብላ ተከራከረች። ነጮችን ንቃ በጥቁረቷ እየኮራች።

ወንዲላዋ እሥረኛ «አዲስ መጥ እሥረኛ ለኛ ለነባሮቹ መታዘዝና ማገልገል ያለ ደንብ ነው። ገባሽ?» አለቻት።

ሮዚ «እንዲህ ያለ ደንብ ጨርሶ አይገባኝም» ብላ አሻፈረኝ አለች። ወንዲላዋ እሥረኛ «እባክሽ አትጨማለቂ ትጠርጊ እንደሆን ጥረጊ» ብላ መጥረጊያውን ሰጠቻት። ሮዚ መጥረጊያውን ተቀብላ ግንባሯን ፈንክታ ሆዷን በርግጫ ብላ ጣለቻት። ልትነሳ ስትወራጭ ደገመቻት። የቀሩት



ሁለት እሥረኞች ተደራርበው ሊመቷት ሲመጡ ሮዚ በመጥረጊያው እየተከላከለች እሪታዋን አንቧረቀችው። የሥር ቤቱ ዘበኛ ጩኸቱን ሰምታ ክፍሉን ከፍታ ገባች።

በዚህም ጉዳይ የሴቶች የእሥር ቤት ምክትል አስተዳዳሪ ሹም ሮዚን ቢሮአቸው አስጠርተው አነጋገሯት። ችግሯንም አውቀው የእሥር ቤቱ ክፍል እንዲለወጥ ፈቅደው ከሌሎች ተደባለቀች።

ይሄኛው ክፍል ከዛኛው የሰፋ በውስጡም ከአሥር የሚበልጡ እሥረኞች አሉበት። ጥቂት ጀርመኖች ሁለት ጥቁሮችና የተለያየ ዜግነት ያላቸው በመሆኑ በሮዚ ላይ የንቀትም ሆነ ሌላ የተለየ ስሜት አላሳይዋትም። ውሎ ሲያድር አካባቢውን ተላምዳ ሀሳቧን የምታካፍለውም ጓደኛ ማግኘት ቻለች።

በዚሁ ጥቂት ወራቶች መሐከል የቀድሞ የጆኒ የፍቅር ወዳጅ የነበረችው ፋጡማ ዑስማን የመውለጃዋ ጊዜ ተቃርቦ ሆስፒታል ገባች። የቅርብ ወዳጁ ክላውዝ በአባትነቱ ተማምኖ ፋጡማን ሳይጠራጠር የሚወለደው ሕፃን ልጁን ለማየት ጓጉቶ አጠገቧ ሰነበተ። ፋጡማ ያልጠበቀችው ዱብ እዳ ወደቀባት ቀኗ ደርሶ ጆኒን የመሰለ ጠይም ሕፃን ወንድ ልጅ በደህና ተገላገለች።

ይህም የምሥራች ለጆኒ ተነግሮት እቅፍ አበባ ይዞ ሆስፒታል ሄዶ ጠይቋታል። ሕፃኑንም ታቅፎ አገላብጦ ስሞ ባባትነቱ ኮርቶ በደስታ ተዝናንቷል።

ሮዚ በተባለው እሥር ቤት ሆና በዳቦ መጋገሪያ ክፍል ተደልድላ ቀኑን ሙሉ መሥራት ጀምራለች። በጀርመን እሥረኞች ቀኑን ሙሉ እጅና እግራቸውን አጣምረው አይቀመጡም። የተለያየ ሥራ ተሰጥቷቸው እየሠሩ መጠነኛ ደሞዝ ያገኛሉ። ከሚሰጣቸውም ደሞዝ በወር 40% ተከፍሏቸው 60% ተቀማጭ ሆኖ እሥር ቤቱን ለቀው ሲወጡ ያጠራቀሙት ገንዘብ ከነወለዱ ይሰጣቸዋል። የሚፈልጉትም መጽሐፍትም ሆነ ሙዚቃ ደብዳቤ ቴሌቪዥንም ሆነ ሌላ የግል ንብረታቸው ተፈትሾና ተመርምሮ ይሰጣቸዋል። ጠባያቸውም ላማረ በሳምንት ሁለት ቀን የውጪ ጐብኝዎችም እንዲያይዋቸው ይፈቀዳል።

ይህም በመሆኑ ጆኒና የኢትዮጵያ የስደተኞች መገናኛ መሐበር አባላት ሮዚን እንዲጐበኟት ሆኖ በየሳምንቱ እሁድ የሚያምራትን ምግብ አዘጋጅተው ጠይቀዋታል። የመኖሪያ ቤቷም ኪራይ ተጠራቅሞ

እንዳይጐዳት ጠቃሚ ንብረቷ ለጆኒ በአደራ ተሰጥቶ ክፍሏ ከእሥር ቤት እስክምትወጣ የመሐበሩ ቢሮ ሆኖ ተከራይቷል። በዚሁ አድራሻዋ የሚላክላትንም ደብዳቤዎች ጆኒ ሰብስቦ ስለሚሰጣት የእሥር ቤቱ ሀዘንና ምሬት እያደር እየቀለላት ሄዷል።

ሮዚ በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለች አመት አልፎ ወር ተተካ። የተላመደችው እሥር ቤት መልሶ ሰለቻት። የቤተሰቦቿ ናፍቆት የአሜሪካኑ የአሮን የፍቅር ትዝታ ልቧን እየሞረሞረ አስጨነቃት። ያለችበትን ሁኔታ ሳትገልጽ ብዙ የደብዳቤ ልውውጦችን አድርጋ ዋሸታ ከርማለች። ውሸቷ ግን ሞራሏን ነክቶ ወተወታት። እንቅልፍ ነስቶ አወራጫት። በተለይ የስልክ ግንኙነት ካደረገች ወዲህ ናፍቆቷ ብሶ ምግብ አልዋሃዳት ብሎ ወስፋቷ ተዘጋ። ሰውነቷ አተኩሶ ያልታሰበ በሽታ ያዛት። በዚሁ ምክንያት እሥር ቤት ውስጥ ከሚገኘው ክሊኒክ ገብታ ምርመራ ተደርጐላት በሽታዋ ታጣ።

ሮዚ ብቻዋን መነጋገርና መሳቅ አበዛች። አበባ ከየመስኩ እየቀጣጠፉ መሰብሰብ አክርማ እየሰነጠቁ መተከዝ ሆነ ሥራዋ። በዚህም ሁኔታዋ የአዕምሮ ሕመም እንደያዛት ተጠርጥሮ የዳቦ ቤቱን ሥራ እንዳትሠራ ተከለከለች። ሁኔታው እየባሰባት ስለሄደ ጉዳዩ ለሥር ቤቱ አስተዳዳሪ ዋና ዴሬክተር ተነግሮ ቢሮአቸው ተጠርታ ገባች። ሁለቱም ስለሚተዋወቁ ተደናገጡ። ያኔ ሮዚ የታክሲ ሥራ ስትሠራ ነጭ ለባሽ የሆነው ፖሊስ መሆኑን አውቃ ገረማት። እሳቸውም በሁኔታው ተደነቁ። የሁለቱ ግንኙነትና የፍቅር አመለካከት በሌላ ሰዎች ሳይታወቅ ለችግሯ አንድ መፍትሄ እንደሚፈልጉላት ነግረዋት ከቢሮአቸው ወጣች።

ሮዚ አንድ ዓመት ታሥራ በዚሁ ዳሬክተር ዋስትና የሳምንት የሁለት ቀን እረፍት ተፈቀደላት። ይህም ማለት ዓርብ ማታ ከሥር ቤት ወጥታ እሁድ ማታ ትመለሳለች ማለት ነው።

ዳሬክተሩ ይህን ከፍተኛ ውለታ ያደረጉት በደረሰባት የአዕምሮ ሕመም ሳቢያ ትንሽ ፋታ እንድታገኝ የሰጡት ግልጽ ምክንያት ይሁን እንጂ እውነተኛ ነገሩ ከእሷ የሚያገኙትን የፍቅር ገላ ለመዳበስ ከጅለው ያደረጉት ቸርነት ነበር። ያሰቡትም አልቀረ በዚሁ ፍቃድ ምኞታቸው ተሳካ።

ሮዚ እሥር ቤት ሆና የምታከናውነው የዳቦና የፉርኖ ጋገራ ሥራ ተቀይሮ ቤተመጽሐፍት ውስጥ እንድታገለግል ተደረገ። ጤንነቷም ተሽሎ ሰውነቷ ተደላደለ።



ጆኒ ያላሰበው ዱብዳ ወደቀበት። በትራፊክ ወንጀል ተከሶ አምስት ዓመት ተፈርዶበት እዚሁ ሮዚ ያለችበት እሥር ቤት ገባ።

ወንጀሉ በታክሲ አገልግሎት ሥራ ላይ ሆኖ የተፈጸመ ነበር። ጊዜው እኩለሌሊት አልፎ አካባቢው ጭለማ ወርታል። በመንገድ የሚተላለፈው እግረኛ ጥቂት ቢሆንም አልፎ አልፎ ከየመጠጥ ቤቱ እየወጡ ተወላጋግደው እቤታቸው የሚገቡ ሠካራሞች ወይም ጤናማ የለሊት የፋብሪካ የፈረቃ ሠራተኞች ይታያሉ።

ጆኒ በሀይለኛ ፍጥነት ታክሲውን እየነዳ ሲበር ድንገት አንድ ሙሉ ጥቁር ልብስ የለበሰ ሰው መኪና ውስጥ ጥልቅ ይላል። ጆኒ ፍሬን መያዝ አልቻለም። ግጭቱ የመኪናውን የፊት ኮፈን አጉብጦ መስተዋቱን ሰነጣጥቆ ሰውየውን ሰባት ሜትር እርቀት አሽቀንጥሮ ይወረውረዋል።

ጆኒ በድንጋጤ በሁኔታው ግራ ተጋባ። የገጠመው አውሬ ይሁን ሰይጣን ሰው ይሁን የተናደ ድንጋይ ምን እንደሆነ በደንብ ሳያረጋግጥ ለገጨውም ሰው ምንም እርዳታ ሳያደርግ መኪናውን አስነስቶ ከአካባቢው ተፈትልኮ እርቆ የሄዳል።

ግጭቱን የሰሙ የአካባቢው ነዋሪዎች ሁኔታውን ከፎቅ ቤት መኖሪያቸው ወደታች ተመልክተው ኖሮ አንድ የታክሲ ሹፌር የገጨውን ሰው ትቶ ማምለጡን ለፖሊሶች በስልክ ያስታውቃሉ።

ወዲያው የጆኒ መኪና በአምስት የፖሊሶች መኪና ተከቦ ጆኒ ተይዞ ይወሰዳል። ለምርመራ አንድ ሳምንት እሥር ቤት ቆይቶ በዋስ ይፈታል። ሁኔታውን በጠበቃ ተከራክሮ የሰከረው ሰው እራሱን ለመግደል ይሁን ዘሎ መኪና ውስጥ ስለገባ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሎአል። ግን የተገጨው ሰው የሰከረ ወይም እራሱን ለመግደል የሞከረ እንዳልሆነ በሕክምና ምርምር ተረጋግጦ እውነቱ ለዳኞች ቀርቧል።

በዚህም የብሬመን የወረዳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ችሎት የወንጀሉን ሁኔታ መርምሮ:-

1ኛ. ጆኒ ባልተፈቀደ ፍጥነት በኃይል በመብረሩ፣

2ኛ. ሰው ገጭቶ በመግደሉ፣

3ኛ. የገጨውን ሰው እርዳታ ሳያደርግ በማምለጡ።

በጀርመን ትራፊክ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፓራግራፍ 222 እና በፓራግራፍ 142 መሠረት የመንጃ ፍቃዱ ተነጥቆ አምስት ዓመት እንዲታሠር ተፈረደበት።

ጆኒ «በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ» እንደሚባለው ሆነበት። ያን የነፃነት የባእድ ሀገር ኑሮ አልጥም ብሎት ሲያማርር ያልታሰበ ዱብ እዳ

በተስፋ ይዞኛል እኔን አባብሎ
ጋሽዬ ጋሹ ጋግሼ
ጋሽዬ ጋሹ ጋግሼ
የስደት ኑሮ መረረኝ መረረኝ
ብዬ ስከፋ ታሥርኩኝ ታሥርኩኝ
ብዙ አልሜ አንዱን ሳሊዝ
እድሜዬ ገፋ በሰው መዘዝ
አጋግም ብዬ ግግም ብዬ

ከግዞተኛ ስሜወት ውዬ ስሜወት ውዬ» እያለች ሮዚ የሚቀርብላት ሥጋ ወጥ አስጠላት። ቦዘና ሽሮ የድርቆሽ ፍርፍር አማራት። ያለውን ትታ የሌለውን መመኘት ጀመረች። አንድ ቀን በለሊት ተነስታ የሌላ እስረኞችን ኬክ ሰርቃ በላች። ይህም ስርቆት ድሮ ኢትዮጵያ እንዳለች ናዝሬት ት/ቤት ያደረገችውን ትዝታ አስታወሷት የጐረሰችው ብስኩት አቃራት።

ጆኒ በታሠረ ባጭር ጊዜ ውስጥ ሰውነቱ በቶሎ ገረጀፈ። በሲጃራው ሳቢያ ይሁን በሌላ ዘወትር ይስላል። የሥር ቤቱ ክሊኒክ እንብዛም አረዳውም። ሁኔታው ለሌላ ግልጽ አይሁን እንጂ እሱም እንደሮዚ በሀሳብ ጭንቀት ተወጥሮ ቀልቡን መሳት ጀምሯል። አንዳንዴ «እርዱኝ!» እያለ ሲጮኽ ሰዎች ለእርዳታ ሲመጡ ይስቅባቸዋል። ፋጡማ በሱ ሰበብ ጥቁር ልጅ በመውለዷ «ዘር አበላሸች» ተብላ ቤተሰቦቿ ንቀው ስላገለሏት እሥር ቤት ሄዳ፣ የድሮ ወዳጇን ጆኒን ልትጠይቀው «አልደፈረችም» እሱ ብቻ ሳይሆን የነሙራትም ጉዳይ ተጨምሮ ይሉኝታ ይዟት ሁለቱንም ለማየት አልፈለገችም።

ሮዚና ጆኒ አንድ እሥር ቤት ሆነው በቅርብ ባይገናኙም እሩቅ ለሩቅ፣ ማዶ ለማዶ ሆነው በሽቦ አጥር ክልል ተለያይተው በሩቅ ይተያያሉ። አንዳንዴም የሚጠብቋቸው ፖሊሶች ከአጠገባቸው ሲርቁ የእለት ብሶታቸውንና የወደፊት ተስፋቸውን በጩኸት ጥሪ ንግግር ይወያያሉ። ሮዚ የረባ ምግብ ባትመገብም ሰውነቷ እንደ ጆኒ አልከሳም። በሀሳብ ትጨነቅ እንጂ የወደፊት ምኞትና አላማም እንደሱ አልተሟጠጠም። እያደርም የያዛት ቀልብ ስቶ ብቻ የሚያናግርና የሚያዘፍን በሽታ ለቋት



ኮበለለ። ተስፋዋ ለምልሞ በለጸገ። ያም ሆኖ በኑሮዋ ሁኔታ ተማራ ማሰብና ማዘኗ አልቀረም። በተለይ የወር አበባዋ ለሦስት ወር ደርቆ አለመምጣት፣ የምግብ ፈላጐቷ ተቀንሶ ማቅለሽለሽ ያለመደችው ስሜት በመሆኑ «ፅንሼ ይሆናል» በሚል ጥርጣሬ ተውጣ ሰነበተች።

ሮዚ በዚሁ ጥርጣሬ እውነቱን ለማወቅ ደፈረች። እሥር ቤቱ ከሚገኘው ክሊኒክ ምርመራ አድርጋ የሦስት ወር ቅሪት መሆኗ ተነገራት። ሁኔታው «የምበላው ሳጣ ልጄ ጥርስ አወጣ» እንደሚባለው ሆነባት። «ምን ዓይነት ጥሎሽ እግዜር ጣለብኝ» ብላ መልሳ ደጋግማ እድሏን አማረረች። «በጭራሽ እኔ ልጅቷ አላደርገውም አስወጣዋለሁ» ብላ ፎክራ ዶክተሩ እንዲረዷት የመረረ ለቅሶ አንብታ ለመነቻቸው። «ሽሉን ለማስወጣት ጊዜው በማለፉ ለሕይወቷ ስለሚያሰጋ አለመቻላቸውን ነገሯት። እሷ ግን «ልሙት ድብን ልበል በዚህ ሁኔታ ላይ ምንም ልጅ አያስፈልገኝም» ብላ አምራ ወተወተቻቸው። ሐኪም ሐኪም እንጂ ነፍስ ገዳይ ወንጀለኛ አለመሆናቸውን ገልጸው ከአጠገቧ እራቁ።

የዚህ ሁሉ ጉድ ሰበብ የሆኑት የእሥር ቤቱ ዋና ዳሬክተር ነገሩን ሰምተው ከእሷ ጋር ባደረጉት የሚስጢር ግንኙነት ቅሌት እንዳይደርስባቸው ሰጉ። በዚህም ሮዚ የሥር ቤቱን ፍርድ ገና ሳትጨርስ ለማስወጣት የተቻላቸውን ጥረት ሁሉ አድርገው ሳይሳካ ቀረ።

ምንም ሳይደረግ ጊዜው ሮጦ ሄዶ ሮዚ የስድስት ወር ፅንስ የያዘች እርጉዝ ሆነች። ሰውነቷ ፋፍቶ ሆዷ ገፍቶ በይፋ መታየት ጀመረ። በየእለቱ ቤተመጽሐፍት የምትሠራው ሥራ ቀላል ቢሆንም በዚሁ ሳቢያ ተከልክላ በቂ እረፍት እንድታገኝ ተደረገ። ለነፍሰጡሮች የሚሰጠውን የእስፖርት እንቅስቃሴ ጅምናስቲክ ማከናወን ጀመረች። በሕክምናም ምርመራ የእሷም ሆነ የፅንሱ አቀማመጥና ጤንነት የተሟላ መሆኑ ተነግሯት ሲጃራ እንዳታጨስ ከለከሏት። የሥር ቤቱም ክፍል ተለውጦ ሰፊ አልጋ ያለበት አንድ ክፍል ተሰጣት።

ጆኒ እዚሁ እሥር ቤት በህመም ላይ እንዳለ ናይጀሪያ ከምትገኘው የድሮ የሕግ ሚስቱ አብራክ የተወለዱ ሁለት ያደጉ ሴት ልጆቹ አባታቸውን ማየት ፈልገው ጆኒ ያለበትን አድራሻ አፈላልገው ጀርመን መግባታቸውን ሰማ። ልጆቹን ናፍቆ ለማየት ቢጓጓም ያለበት ሁኔታ አሳፍሮት እድሉን እረግሞ አምርሮ አለቀሰ።

ይህ እንዲህ እንዳለ ጀርመን የስደተኞች ካምፕ ውስጥ ያለችው የጆኒ የሕግ ባለቤት ታናሽ እህት ሊንዳ ገ/ሕይወት ያቀረበችው የፖለቲካ

ጥገኝነት ጥያቄ በዳኞች ታይቶ ውድቅ ሆነ። በዚህም ያለውዴታ በግዴታ እጇ ተይዞ ሀገሯ ኢትዮጵያ በአይሮፕላን ተጭና ተመለሰች።

ሮዚ ያ ገና ሲጀምራት አማርሮ ለመኖር ያስጨነቃት እርግዝና ቀስ በቀስ እየገፋ ሄዶ የመውለጃዋ ጊዜ ተቃረበ። ሮዚ ያለፈውን ዘንግታ እያደር ተስፋዋ ለመለመ። በዚህም የናትነት ፍቅሩና ወጉ ደርሷት ከአብራኳ የሚገኘውን ሕፃን አቅፋ ለመሳም ቸኩላ ጓጓች።

«ዛሬን በደስታ እየኖሩ የነገን ብሩህ ተስፋ አልሞ አዲስ ጅምር አቅዶ መዘጋጀት እንድ የሕይወት ማጣፈጫ ቅመም ነው» የሚለውን የፈላስፎች ጥቅስ አስታወሰች። በዚህም እድሏን ሳታማርር ቀሪ ሕይወቷ እንዲጣፍጥ በብሩህ ተስፋ ኳለችው። እራሷና በራሷ መከራ ተጽናናች። ከእሥር ቤትም የምትወጣበትም ጊዜ ተቃረበ። በዚህም የውጪውን የነፃነት ዓለም ቡራኬ መልሳ ለመቅመስ ቸኩላ በተስፋዊ ደስታ ሰውነቷ እረካ። ግን የሆነ ነገር አስታውሳ ሰጋች።

«የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም» ብላ ነፃ ብትሆንም ከእንግዲህ ጀርመን ሀገር ውስጥ በሰላም መኖሩ አስፈራት። እነሙራትና ዘመዶቹ እሷን እንዲህ በዋዛ የሚለቋት አለመሆኑን ተጠራጠረች። በዚህም የወደፊት ኑሮዋ አሜሪካ እንዲሆን አስባ ወሰነች። ለታላቅ እህቷና ለወዳጇ አሮን እንዲቀበሏት እሥር ቤትም ሆና ማርገዟን እንኳን ሳትደብቅ በዝርዝር ሁሉን ገልጻ ደብዳቤ ጻፈችላቸው።

ሮዚ ገና በሚወለደው ሕፃን እናትነቷ ቢያኮራትም ከፈረንጅ አርግዛ ዲቃላ ወልዳ ማሳደጉ አስጠላት። ከዚህም ሌላ ላቀደችውና ለጀመረችው የሕግ ከፍተኛ ትምህርት ትልቅ እንቅፋት እንደሚሆንባት አወቀች። በዚህም ሮዚ ያረገዘችውን ሕፃን በሰላም ተገላግላ ለአባቱ ጥላለት አሜሪካ ብቻዋን መኮብለሉን መርጣ በወሰነችው ጸናች። ግን ይህን ውሳኔ ሞራሏ አልቀበል ብሎ ወተወታት። እንዲህ ያለውን የነጮች ጭካኔ ለመፈጸም የሀገሯ የናትነት ፍቅሩና ወጉ ባህሉና ሰባዊ ሞራሉ እንቢ ብሎ ከለከላት።

ሮዚ በዚህ ሁኔታ በሀሳብ ተወጠረች። የምታደርገው ቸግሯት ስታመነታ ድንገት ሁለት ደብዳቤዎች ከአሜሪካን ደረሷት። የመጀመሪያው ከወዳጇ ከአሮን የተጻፈ የፍቅር መግለጫና ወደፊት ከእሷ ጋር ሆኖ ትዳር ለመመሥረት ሙሉ ፍቃደኛነቷን የሚጠይቅ ሆኖ ለዚህም ከሌላ ያረገዘችውን ሕፃን ወልዳ ይዛው ብትመጣ በደስታ እንደሚቀበላቸው የሚገልጽ ነው። በዚህም ሮዚ የምትወልደውን ሕፃን ይዛ ለመሄድ ድፍረት አገኘች።



ሁለተኛው ደብዳቤ ካሊፎርኒያ የሚገኘው ታላቅ ዩኒቨርስቲ የጻፈላት ሌላ የምሥራች በመሆኑ ሮዚ መልእክቱን ቸኩላ አንብባ በገጠማት እድል ሰውነቷ በደስታ ተሞላ።

ባለፈው ጊዜ ሮዚ ለእረፍት አሜሪካ በነበረችበት ጊዜ ለሕግ ከፍተኛ ትምህርት እስኮላርሽፕ እንዲሰጣት አመልክታ ነበር። ዩኒቨርስቲው በወቅቱ የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን እዛው ሀገር ውስጥ ለሚኖሩ ብቻ ሆኖ ሦስተኛውን ዓመት አውሮፓና ሌላም ሀገሮች ለሚኖሩ አመልካቾች ሆኖ በዚሁ ምክንያት ሁለት ዓመት ዘገየ። ይህም ለሮዚ ጥሩ አጋጣሚ ሆኖ ከስድስት ወር በኋላ የሕግ ትምህርቷን እንድትጀምር ስኮላርሽፖን መፍቀዱን የሚያረጋግጥ የምሥራች ነበር።

ሮዚ ከእሥር ቤት ልትወጣ የቀራት ጊዜ ሁለት ወር ከሃያ ቀን ብቻ ነው። ለዚህም የተሰጣትን እድል አሜሪካ ሄዳ ትምህርቷን ለመከታተል በቂ ጊዜ እንዳላት ገምታ ደስ አላት። ግን እርግዝናዋ ገፍቶ የመውለጃዋ ጊዜ በማለፉ የሕፃኑን ጤንነት ተጠራጥራ ሰጋች። ሰሞኑን ሕፃኑ መሐፀኗ ውስጥ ሆኖ እንደበፊቱ መወራጨትና መገላበጡን አቁሞ ጸጥ ብሏል። ምርመራዋ የሠመረ ቢሆንም የአሁኑ ሁኔታ ሮዚን አስግቶ አስጨነቃት። «ቅዱስ ገብርኤል ክፉ ነገር አታምጣብኝ። እምዬ ማርያም በሰላም አገላግይኝ» ብላ ግንባሯን አማትባ የምታቀርብላቸውን ስለት በልቧ ተስላ ደጋግማ ተማፀነች።

ጆኒ በእርግጥ ስለሮዚ እርግዝናና በቅርቡም መፈታት ከአወቀ ቆይቷል። በቅርቡም ሁለቱ በሽቦ ያጥር ክልል ማዶ ለማዶ ሆነው እየተያዩ ተነፋፍቀው ሰላምታ ተለዋውጠዋል።

በእርግጥ ጆኒ ሮዚ ከዚህ እሥር ቤት በቅርብ እንደምትወጣ አውቆ ቢደሰትም የእሷ ካጠገቡ መራቅ አሳዝኖ ልቡን አስጨንቆታል። ውጪ ሆና እዚህ ጀርመን ውስጥ ብትኖርም እነሙራት ሰላም እንደማይሰጧት ጠርጥሮ እራቅ ወዳለ ቦታ እንድትሄድ መክሮ፣ በሰላም ተገላግላ መልካም እድል እንዲገጥማት ከልቡ ተመኝቶላታል።

ሮዚም በምስጋና ምክሩን ተቀብላ ወንድ ልጅ ከወለደች ክርስትና አባትነቱን ለእሱ እንደምትሰጠው ነግራዋለች። ከዚህም ሌላ ከእሥር ቤት እንደወጣች የጆኒን የትራፊክ ወንጀል የአምስት ዓመት የእሥር ቅጣት እንዲቀነስለት የሚያደርገውን ማሻሻያ ሁኔታዎች ከጠበቃ ጋር በመነጋገር እንደምትረዳው ቃል ገብታለታለች።

ጆኒ ሮዚን በዚህ አስተሳሰቧና ጠንካራ ምኞቷ ከልብ አደነቃት። የእሱ የመኖር ተስፋው መልሶ አቆጠቆጠ። የውጪው ዓለም ከአድማስ ባሻገር ያለው የነፃነት አየር በጥሩ ተስፋ መአበል መጥቶ እየነፈሰ ሸተተው።

ጆኒ በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ እሱም እንደሮዚ የሚያስደስት አንድ የምሥራች ነገር ገጠመው። ለብዙ ጊዜ ደክሞ የጻፈው ድርሰቱ ታትሞ ለህገሩ ሕዝብ መሰራጨቱን ነበር። ከእትመቱም እፍታ ሁለት መጽሐፍ ተልኮለት ደረሰው።

ጆኒ የሀሳቡን ሽል በጭንቅላቱ አርግዞ በብእሩ አምጦ የድካሙን ፍሬ አፍርቶ ዛሬ በማየቱ በደስታ ቦረቀ። እናት የወለደችውን ሕፃን ለመጀመሪያ ጊዜ አይታ የሚሰማት ደስታ ሰውነቱን ወረረው። እናት ሕፃኑን አቅፋ አገላብጣ እንደምትስም ጆኒም መጽሐፉን አገላብጦ ሳመው። የሚያውቀውን ድርሰት መልሶ ደግሞ አነበበው። ያኔ የረካበት የተዋበ መልእክቱ የጥበብ ሥራ ድርሰቱ ዛሬ አልጥምህ አለው። ቢሆንም ጆኒ «ያለውን የወረወረ ፈሪ አይባልም» ብሎ ባደረገው ልማትም ይሁን ስህተት ደስ ብሎት ኮራ።

ይህንንም ድርሰት እንዲጽፍ ሀሳብ ሰጥታ ያደፋፈረችውና የታሪኩም ዋና ገፀባህሪ የተጫወተችው ጥቁሯ ፓይለት ሮዚ ስለሆነች ይህንኑ የምሥራች ሊነግራት ፈልጐ በአንዱ መጽሐፍ ላይ ስሙንም ፈርሞ...ሁለቱንም መጽሐፍቶች ይዞ በጠዋት ከክፍሉ ወጣ። የዓይኖቹ ጨረር ማዶ ሮዚ ያለችበትን ቦታ ማንም ሳይነካቸው በቀጥታ ተወረወሩ። ከብዙ የሴቶች እሥረኛ መሐል ሮዚን ለይቶ ለማውጣት አልቻለም።

በእለቱ ሮዚ በሕፃን ሽል አለመገላበጥ ምክንያት ለምርመራ ክሊኒክ ገብታለች። ዶክተሩ በቂ ምርመራ አድርገው ጤንነቷን አረጋግጠዋል። የሚጠጣም መድኃኒት ሰጥተዋት የሕፃኑ ሽል መገላበጥ ጀምሯል። በዚሁ ምክንያት እንደወትሮ ደጅ ወጥታ ግቢ ውስጥ በይፋ አልታየችም።

ጆኒ ልቡ በስጋት ተጨንቆ የምሥራቹን ለሮዚ ሳይነግራት ቀኑ መሽቶ ተመልሶ እክፍሉ ገባ።

መሬት እራሷን በራሷ አዙራ የፀሐይን ፈለግ ተከትላ በተፈጥሮ የክስተቷ ፍጥነት ተጓዘች። በዚህም ሞላላ ክብ ፊቷ ግማሹ ብርሃን ግማሹ ጨለማ ሆነ።

ጆኒ ጊዜው መሽቶ ለሊቱ አልፎ ሲነጋ የምሥራቹን ለሮዚ ነግሮ ለማብሠር ቸኩሎ ማልዶ ተነሳ። በእለቱ የለበሰው ጥቁር ሸሚዝ ከደረበው ሰማያዊ የሥር ቤቱ ትልቅ ኮት ጋር ተደባልቆ ሲታይ የጠወለገ አበባ አስመስሎታል። ፊቱ ግን በድርሰቱ እትመት ደስታ ተለስኖ ፈክቶ ያምራል። መጽሐፉን እንደ ሕፃን ልጅ በብብቱ ሥር አድርጐ አቅፎ



ይዟል። አንደኛውን ለሮዚ ሊሸልማት አሰናድቶ፣ ሌላውን ደግሞ እያነበበ የሮዚን መምጣት ናፍቆ ብዙ ጠበቀ።

ሮዚ በደንብ ተኝታ ብታድርም በእሥር ቤቱ ደንብ በፖሊስ ተቀስቅሳ ማልዳ አልተነሳችም። በእርግዝናዋ ምክንያት ያገኘችው ልዩ ፍቃድ እያዝናና የምትወደውን የጠዋት እንቅልፍ እንድትጠግብ አድርጓታል። ሰዓቱ ቢረፍድም ተንጠራርታ ከመኝታዋ ተነሳች። ፊቷን ተጣጥባ የቀረበላትን ቀዝቃዛ ቁርስ በምሳ ሰዓት ተቋደሰች። የሰሞኑ ስሜቷ እንደቀድሞው አልጨፈገገም። የወሰነችው ጥሩ ዓላማ ከብሩህ ተስፋዋ ጋር ተዋህዷል። የሕፃኑ መወራጨትና መገላበጥ አስደስቷታል። ጊዜው ቢረፍድም እለቱ እሁድ በመሆኑ ደህና እንድትገላገል ጸሎት ለማድረግ ፈልጋ፣ በዛውም የአሜሪካኑን የምሥራች ለጆኒ ልትነግረው አሰበች። በዚህም ሽንሽኑ ዘርዘር ተደርጐ የተበተነ በፍቃድ የገባላትን የግሏን የአበሻ ቀሚስ ለብሳ የኢትዮጵያ ባንዲራ ያለው ጥለት ነጠላ ተከናንባ ደማቅ ጨረቃ መስላ ከክፍሏ ወጣች።

ወቅቱ የበጋ ወራት ቢሆንም የቀትሯ ፀሐይ በከፊል በጉም ተሸፍናለች። በዚህም ምክንያት የሥር ቤቱ ግቢ ግማሹ ደብዝዞ ሌላው ብርሃን ፈንጥቆበታል።

እለቱ እሁድ ሰዓቱም የምሳ መመገቢያ ወቅት በመሆኑ ከታወር የተጠንቀቅ ዘበኞች በስተቀር አብዛኛዎቹ እሥረኞችና ፖሊሶች እምግብ አዳራሽ ገብተው ግቢው ጭር ብሏል። በዚህም ጥሩ አጋጣሚ ሮዚና ጆኒ ማዶ ለማዶ በሽቦ ክልል አጥር ተያይተው የናፍቆት ሰላምታቸውን በጩኸት ተለዋወጡ።

ሮዚ የአሜሪካኑን የእስኮላርሽፕ ማግኘት የምሥራች ለጆኒ አጫወተ ችው። እሱም የመጽሐፉን መታ ተም ነገራት። ሁለቱም በደስታ እጃቸውን እያራገቡ ማዶ ለማዶ ሆነው ቦረቁ።



ጆኒ አዲስ እትመት መጽሐፉን ይዞ ለሮዚ እንዲደርሳት በመሐከላቸው የተዘረ ጋውን የሽቦ አጥር አሻግሮ አሽቀንጥሮ ወረወረላት። ሮዚ መጽሐፉን ከወደቀበት ቦታ ለማንሳት ካለ ችበት ተንደርድራ እየሮጠች ስትመጣ መሬቱ አንሸ ራትቷት ወደቀች። ድንገትም ምጥ አጣድ ፏት ስላመማት እሪታዋን በጩኸት አቀለጠችው።

ጆኒ በድንጋጤ ክው አለ። የሚያደርገው ቸገረው መርዝ እንደበላች ውሻ ከወዲያ ወዲህ ተቅበዘበዘ። እርዳታ የሚያደርጉለትን ሰዎች እየጮኸ ተጣራ። ከማዶ ያዩት ጥቂት እሥረኞች ቢኖሩም ወፌፌነቱ መስሏቸው ለእርዳታው አልተባበሩትም። ሮዚ አሁንም ከማዶ በምጥ ጩኸት ታቃስታለች ትጮሃለች። ጆኒ ቢቸግረው እየሮጠ ሄዶ የቤተክርስቲያኑን የኤሌትሪክ ደወል ለኩሶ ድው! ድም ሲል ወደሮዚ ተመለሰ።

ከማዶ እሪታ ከወዲህ ጭንቀት ጆኒ የሚያደርገው ቢያጣ በድፍረት በመሐከላቸው የተዘረጋው የሽቦ አጥር ላይ ዘሎ ለእርዳታ ወደላይ ወጣ። የታወር ዘበኛ ፖሊስ «ውረድ!» ብሎ ሦስቴ ጮኸበት። ጆኒ በድንጋጤ የተባለውን ጨርሶ አልሰማም። የአጥሩ ጫፍ ደርሶ ሮዚ ወዳለችበት እንገቱን አሾልኮ ለማለፍ ተፍጨረጨረ።

ታወር ላይ ያቆመው ሦስት ጊዜ ማስጠንቀቂያ የሰጠው ፖሊስ የሚያመልጥ መስሎት በተሰጠውም ትእዛዝ መሠረት ተገዶ በያዘው ጠመንጃ አነጣጥሮ ሦስት ጊዜ ተኩሶ ጀርባውን መታው።

ሮዚ ከማዶ እያቃሰተች አምጣ ብቻዋን እሚዳ ላይ ወድቃ ያለአንዳች እርዳታ ሴት ልጅ ወለደች። ወዲያው የእሥር ቤቱ ክሊኒክ ዶክተር ተጠርተው ከረዳቶቻቸው ጋር ሆነው ሮዚን ከበቧት። የተወለደችውንም የሕፃን እትብት ቆርጠው ሮዚ ደረት ላይ አድርገው አስታቀፏት። የሮዚ የጥቁሯ ፓይለት ፊት ፈገግ ብሎ ታየ። ቦታው የብርሃን ጮራ ፈንጥቆበት የደስታ አየር ተጉናጸፈ።

ወዲህ ጆኒ ጀርባው በጥይት ቆስሎ ሰውነቱ በደም ተለውሶ አጥሩ ሥር ወድቋል። በሁኔታው የተደናገጡ እሥረኞችና ፖሊሶች ዙሪያውን ከበውታል። ጆኒ ትንፋሹ ቆሞ አካሉ ቀዝቅዞ ዓይኖቹን ወደሰማይ አፍጥጦ በጀርባው ተጋድሚል። ቦታው የጉም ጥላ አጥልቶበት በሀዘን ተውጧል።

የእሥር ቤቱ የቤተክርስቲያን ደውሎች አሁንም መደወላቸውን አላቋረጡም። ከወዲያ የልደትን የፀጋን ፍሬ እያበሠሩ ጮሁ።

ከወዲህ የሕይወትን የማይቀር ቅስፈት ፍጻሜ ዜማ አንጐዳጐዱ። ግቢው በጩኸት ተስተጋብቶ ከአድማስ ባሻገር አልፎ ለሁሉም ተሰማ። የደወል ድምፃቸው ቃና የልደትን ቡራኬ ብሥራትና የሞትን የሀዘን ፍትሃት ደጋግመው እያሰሙ ድው! ድም! ቅው! ቂል! ድው! ድም! ቅው! ቂል! ድው! ድው! ደውውውውው!

ተፈጸመ



ደራሲው ብሩክ ከበደ

1ኛ. ኢትዮጵያውንም ሆኑ የተለያዩ የአፍሪቃ አገር ዜጎች፣ የቀለም ልዩነትና ዘረኛነት በገነነበት ባሕር ማዶ በስደትም ሆነ በልዩ ልዩ ምክንያቶች መኖራቸው ግልጽ ነው።

በዚህም ኑሮ በየዕለቱ የሚደርስባቸውን ውርደትና መገፋት ችለው፣ ለሕልውናቸው፣ እንዲሁም ለመብታቸው ጥበቃ ሲሉ ከነጮች ጋር የሚያደርጉትን የዘወትር ትግልና በመቻቻል የመኖር ጥረት በምሳሌ ትገልጻለች። እነዚህ ለአገሩ ባዳ ለሰዉ እንግዳ የሆኑ ዜጎች፣ የሀገራቸው ናፍቆት ምን ያህል እንደሚያስጨንቃቸውም ታሳያለች።

2ኛ. ወሲብ በአገራችንም ሆነ በአብዛኛው የአፍሪቃ አገሮች ባህላዊ ደንብ መሠረት በምስጢር የሚያዝ የውስጥ ገመና ነው። ይህም በመሆኑ፣ የወሲብ ምስጢራዊነት በትዳር፣ በጤና፣ በሌላም ማኅበራዊ ግንኙነት ላይ ብዙ ችግሮችን አስከትሏል።

ስለዚህ፣ ደራሲው እንዲህ ያለውን ልማድ ቀስ በቀስ ለማስቀረት በማሰብ የወሲብን ድብቅ መጋረጃ በጥቂቱ ገልጦ በማሳየት፣ የብዙኀኑን የውስጥ የባህል ገመና በመዳሰስና ከውጪዎቹ ጋር በማዋሐድ ለማቅረብ ሞክሯል። በዚህ ሙከራው የተሳሳተባቸው ነጥቦች ካሉ አንባብያንን በቅድሚያ ይቅርታ ይጠይቃል።

ንግድ ማተሚያ ድርጅት

ዋጋው ብር 25.00